
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

### የመምህር መምሪያ መጽሐፍ



## ፫ ክፍል

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አማርኛ

እንደመጀመሪያ ቋንቋ

የመምህር መምሪያ

፭ኛ (5) ክፍል


**አዘጋጆች**

መላኩ ጌቶ መኮንን

መስፍን ተካ በርሔ

ውብቱ በዛብህ የሱፍ

**ገምጋሚዎች**

ትንቢት ግርማ ኃይሉ

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድህን

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

**ጥራት ተቆጣጣሪ**

ፍሬሕይወት አሰፋ ከበደ

**አስተባባሪ**

ጌታቸው ታለማ

ምስል (illustration) እና አቀማመጥ (layout)

እንጦጦ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ (TMS)

© መብቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተጠበቀ ነው::
2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለሥራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

## ማውጫ

| | |
|---|---|
| ምዕራፍ አንድ<br>ጓደኝነት | 1 |
| ምዕራፍ ሁለት<br>ጽዳትና ንጽህና | 15 |
| ምዕራፍ ሶስት<br>ልማድ | 25 |
| ምዕራፍ አራት<br>የትራፊክ ደህንነት | 40 |
| ምዕራፍ አምስት<br>አካባቢ ጥበቃ | 52 |
| ምዕራፍ ስድስት<br>ጸረ አደንዛዥ እጽና ንጥረ ነገሮች | 67 |
| ምዕራፍ ሰባት<br>ምግብ | 83 |
| ምዕራፍ ስምንት<br>በኢትዮጵያ የሚገኙ የዱር እንስሳት | 102 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ<br>ባህላዊ ጨዋታዎች | 118 |
| ምዕራፍ አስር<br>ስነ ቃል | 133 |

## መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያና ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄደው የ5ኛ ክፍል የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ አማርኛን በመጀመሪያ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ፤ በተጨማሪም የቃላትና የሠዋስው እውቀት እንዲገኙ ለማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት አካል ነው፡፡

የመምህር መምሪያው በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ በመመሥረት በአዳዲሶቹ የመማሪያ-ማስተማሪያ መሣሪያዎች ውስጥ በጥቅም ላይ ስለዋሉት የማስተማር አቀራረቦችና ስለአዲሱ መርሃትምህርት (ሥርዓተ ትምህርት) መነሻ ሀሳቦች መሠረታዊ መረጃ ይሰጣል፡፡ በአንድ ምዕራፍ ሥርም ለቀረቡት የትምህርት ይዘቶች ግልጽ መመሪያ ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ለመከታተልና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ተገቢውን ድጋፍና ማጠናከሪያ ለመስጠት ተከታታይ ምዘናን መተግበር የሚቻልበትን መርሕ ይዟል፡፡ በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሥርዓተፆታንና የአካቶ ትምህርትን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚገባ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

በመጨረሻ ላይም ለ5ኛ ክፍል የተዘጋጀው አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ) መርሃት ምህርት ተያይዟል፡፡ ይህ መርሃ ትምህርትም በየደረጃው በእያንዳንዱ ወሰነ ትምህርት ተማሪዎች ሊያዳብሯቸው ስለሚገቡ የቋንቋ ብቃቶች ያሳያል፡፡

## የማስተማር መርሆዎች

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በሁሉም ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) እንዲሁም ቃላትና ሰዋስው የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች የማንበብንና የመጻፍን ችሎታዎች በሚያዳብሩበት መልክ ተደራጅተዋል፡፡

አዳምጦ/አንብቦ መረዳት የሚዳብረው በቅድመ ማዳመጥ/ማንበብ፣ በማዳመጥ/በማንበብ ሂደትና በድኅረ ማዳመጥ/ማንበብ ተግባራት ነው፡፡ ተማሪዎች ስለጽሑፉ (በቅድመ ማዳመጥ/ማንበብና በማዳመጥ/ በማንበብ ሂደት ወቅት) እንዴት መገመት እንደሚችሉ፣ መረዳታቸውን በራሳቸው እንዴት መቆጣጠር እንደሚችሉና ያዳመጡትን ወይም ያነበቡትን እንዴት መገምገም እንደሚችሉ መማር አለባቸው፡፡

መናገርና መጻፍ በተገቢ ሁኔታ ራስን መግለጽን ይመለከታል፡፡ ይኸውም ቋንቋውን በትክክል መጠቀምንና ሀሳብን ለሌላ አካል በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በግልጽ ማስተላለፍን ይጨምራል፡፡ በመሆኑም የንግግርና የጽሑፍ ክሂል የሚዳብረው ተማሪዎች በተቻለ መጠን ራሳቸውን እንዲገልጹ በርካታ ዕድሎች ሲመቻቹላቸውና ወቅታዊ ግብረመልሶችም ሲያገኙ ነው፡፡

የቃላት ዕውቀት፡- ቃላትን የመለየት/የመረዳትና ፍቻቸውን የመገንዘብ ችሎታ ነው፡፡ የተገደበ የቃላት ዕውቀት ያላቸው ተማሪዎች የሚያነቡትንም ሆነ የሚያዳምጡትን ጽሁፍ መልእክት ለመረዳት የቃላት እውቀት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የቃላት ዕውቀት የሚዳብረው አዳዲስ ቃላትን ከነፍቻቸው በማስተማር፣ ተማሪዎች እነዚህን ቃላት በንግግርም ሆነ በጽሑፍ እንዲጠቀሙባቸው በማበረታታትና ከሚያነቡት ወይም ከሚያዳምጡት ጽሑፍ ውስጥ የቃላትን ፍቺ የሚያገኙበትን ብልሃት (ስትራተጂ) በማስተማር ነው፡፡

ሰዋስው፡- በመርሃ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ ለደረጃው በተዘጋጀው የትምህርት ወሰንና ተለጣጥቆ መሠረት የተለያዩ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በመማርና በትክክል በመጠቀም ላይ ያተኩራል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የዘረዘርናቸው የትምህርት ይዘቶች ማዕከል ያደረጉት በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ዓላማዎች ነው፡፡

# አማርኛ (፫) ክፍል

# ምዕራፍ አንድ ጓደኝነት

(18 ክፍለ ጊዜ)

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ ስለጓደኝነት ያላቸውን አመለካከት አዳምጠው ያንጸባርቃሉ፡፡
- ✓ ጽሑፉን አንብበው መልእክቱን ይገልጻሉ፡፡
- ✓ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዴት ጊዜ እንደሚሳልፉ በቀላል ዓ/ነገር አንቀጽ ይጽፋሉ፡
- ✓ ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡
- ✓ ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- ✓ የወልና የተጸውዖ ስሞችን ይለያሉ፡፡

ይዘት

- ✓ አዳምጠው የተሰማቸውን መግለጽ
- ✓ በለሆሳስ ንባብ ዋና ዋና ሀሳቦች መለየት
- ✓ ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መስጠት
- ✓ የአንቀጽ አጻጻፍ ስልቶችን መለየት
- ✓ የተጸውኦና የወል ስሞችን መለየት

## ክፍል አንድ፦ ማዳመጥና መናገር

### የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር፦

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ማዳመጥና መናገርን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማስተማር ይረዳዎት ዘንድ ቀጥሎ ‹‹የንጉሱ ልጆች›› የሚል ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም ትምህርቱን ለማቅረብ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ይከተሉ፡፡

### ቅድመ ማዳመጥ

- ✓ ምንባቡን ከማንበብዎት በፊት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡትን ሁለት ተግባራት በሰሌዳ ላይ ይጻፏቸው፤ ከጻፏቸው በኋላም ለተማሪዎች በቃል ያሰሯቸው፡፡

**ተግባር 1፦**

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ከምንባቡ የወጡ ቃላት ይገኛሉ፡፡ ቃላቱን በሰሌዳው ላይ ከጻፉ በኋላ ተማሪዎቹ ፍችዎቻቸውን እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ይህንን ማድረግዎ የሚነበብላቸው ምንባብ ውስጥ ያሉት ቃላት እንግዳ ሆነውባቸው ያዳመጡትን እንዳይረዱ የሚያደርጉ እንቅፋቶች እንዳይፈጠሩ ያደርጋቸዋል፡፡

**ተግባር 2፦**

- ✓ በዚህ ተግባር ስር አንድ ጥያቄ የቀረበ ሲሆን ጥያቄውም የሚያደምጡት ሀሰብ ስለምን እንደሚያወሳ መንደርደሪያ ይሆናቸዋል፡፡
- ✓ በመሆኑም ጥያቄውን ሰሌዳው ላይ ከጻፉ በኋላ ለተወሰኑ ተማሪዎች እድል በመስጠት በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ምንባቡን በጥሞና እንዲያዳምጡ በማሳሰብ ማንበብዎን ይጀምሩ፡፡
- ✓ የማድመጥ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ፣ ፊት ለፊት ባሉት መቀመጫዎች ላይ እንዲቀመጡ በማድረግና በሌሎች መንገዶች ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

### የማዳመጥ ሒደት

- ✓ ምንባቡን ለሁሉም ተማሪዎች ሊሰማ በሚችል ድመጸት ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ ምንባቡን በማንበብ ላይ እንዳሉ ተማሪዎች እያዳምጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይረዳዎት ዘንድ ማንበብዎን ገታ በማድረግ በምንባቡ መካከል ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ጠይቀው መልስ ከተቀበሉ በኋላ ማንበብዎን እንደገና ይቀጥሉ፡፡

### አዳምጦ መረዳት

- ✓ ተማሪዎች ምንባቡን አዳምጠው ከጨረሱ በኋላ የሚሰሯቸው ሁለት ተግባራት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ቀርበዋል፡፡ ተግባራቱን በሚከተለው መልኩ ያሰሯቸው፡፡

### ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ምንባቡን መሰረት ያደረጉ የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡
- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ መልስ የሚሰጡት የምንባቡን ሀሳብ ተመርኩዘው ሲሆን መልስ ሲሰጡዎት ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ ለጥያቄዎቹ መልስ ሰጥተው ከጨረሱ በኋላ የማስተካከያ እርማት በመስጠት ወደ ሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

### ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ሰባት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን የሚሰጡት ምላሾችም በሁለት መንገዶች ይቀርባሉ፡፡

- ✓ የመጀመሪያዎቹ ሶስት ጥያቄዎች (ሀ፣ ለ፣ ሐ) ቀጥታ ከምንባቡ የሚመሱ ሲሆኑ ቀሪዎቹ አራት ጥያቄዎች (መ፣ ሠ፣ ረ፣ ሰ) ደግሞ አንድምታዊ ምላሽ የሚፈልጉ ናቸው፡፡
- ✓ ለጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ መልስ ከሰጡ በኋላ የማስተካከያ እርማ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

## የንጉሱ ልጆች

‹‹በድሮ ጊዜ...›› አለ እረጋ ብሎ፡፡ በድሮ ጊዜ ዓለም እንደ አሁኑ በአህጉር ተቀምራ፣ በሀገራት ተከፋፍላ ብዙ ከመሆኗ በፊት በአራት ንጉሰ ነገስታት ትመራ ነበር፡፡ የምዕራቡ ንጉስ፣ የምስራቁ ንጉስ፣ የሰሜኑ ንጉስ እና የደቡቡ ንጉስ እየተባለ ትመራ ነበር፡፡ አሁን የማወራው በምዕራቡ ንጉስና በምስራቁ ንጉስ የተፈጸመ አንድ ገራሚ ታሪክ ነው፡፡

ይገርማል! የምዕራቡ ንጉስ እጅግ ሲበዛ ልጅ ይወድ ነበር፡፡ መንግስቱ የተደላደለ፣ ሀገሩ በልምላሜ የተሞላ፣ ሕዝቡም በሰላም የሚኖር ነው፤ ቢባልም፣ ይህ ሰው ግን የልጅ ፍቅር ያንገበግበው ነበር፡፡ ከህግ ሚስቱ አንድ ወንድ ልጅ ብቻ የወለደ ሲሆን፣ በዚያ ሀብቱና በዚያ ሁሉ ግዛቱ ግን ብዙ ልጆች ሊኖሩት ሲችል፣ አንድ ልጅ ብቻ ወልዶ በመቅረቱ ሁልጊዜ በጣም ያዝን ነበር፡፡ ይህንንም ልጅ ወደኋላ በእድሜው መጨረሻ እንደወለደው ይነገራል፡፡ አንድ ቀን በሰረገላ ተጭኖ በወታደርና በመኳንንት ታጅቦ ሲሄድ፣ አንዲት የኔ ቢጤ ሴት መንገድ ዳር ቁጭ ብላ ስትለምን ያያል፡፡ ይህች ሴት ከእርሱ ልጅ በእድሜ እኩያ የሆነ ወንድ ልጅ ከጎኗ ቁጭ አድርጋለች፡፡ የሴትየዋ ልጅ የእርሱ ልጅ እኩያ በመሆኑ፣ንጉሱ የሆነ ነገር ልቡን ነካውና፤ ከሰረገላ ወርዶ፤ ከአጀቡ ተለይቶ፤ ወደ ሴቷ ጠጋ ብሎ

‹‹የምትልፈጊውን ዋጋ እከፍልሻለሁ፤ ይኸንን ልጅ እንደ አባት አድርጌ በአባትነት ፍቅር ላሳድገው፤ እባክሽ ስጭኝ?›› ይላታል፡፡

ሴትዮዋም ‹‹እዚህ ጎዳና ከእኔ ጋር በችግር ከሚጠበስ፣ በንጉስ እልፍኝ የንጉስ ልጅ አምሳል ይዞ ቢያድግ ምን ከፍቶኝ›› አለችው፡፡ ንጉሱም ለዚች ሴት ብዙ ብርና ወርቅ ከሰጣት በኋላ ልጁን ወደ ቤተ መንግስት ይዞ ሄደ፡፡

ንጉሱ ሁለቱንም ልጆቹን በእኩል ዓይን እያየ በቤተ መንግስት በልዩ ፍቅር፣ በባለሟልነት፣ በክብር አሳደጋቸው፡፡ እንደሀገሩ ወግና ልማድ፣ እንደንጉስ ልጅነታቸው በፈረስ ጉግስ፣ በጦር ውርወራ፣ በአደን፣ በውሀ ዋና… በተለያዩ ትምህርቶች ተኮትኩተውና ሰልጥነው አደጉ፡፡

እኩል ስልጠናና እኩል እንክብካቤ ቢያገኙም መቸም እኩል ስጦታ፣ እኩል ችሎታ አይኖርምና፤ የደሀይቱ ልጅ አንድ የተለየ ችሎታ ነበረው፡፡ ይኸውም የሚደንቅ የስዕል ችሎታ ነው፡፡ ያየውን ልክ የፎቶግራፍ ያህል በስእል የማስቀረት አቅም አለው፡፡ ይህንን ችሎታውን አባቱ እያበረታታው፣ የበለጠ እያዳበረው ሄደ፡፡ በሌላውም ሙያ ቢሆን የተዋጣለት ነበር፡፡

በወንድማማቾች መካከል ሁሌም እንደሚኖረው ከወንድሙ ጋር በአደን ፉክክር ገጠሙ፡፡ ሁልጊዜ አደን ሲወጡ አደጋ ጣዮች አደጋ እንዳያደርሱባቸው በብዙ አጃቢዎች ተከበው ቢሆንም፣ አልፎ አልፎ የገደሉትን እያነሱ ‹‹እኔ ብዙ ገድያለሁ፤ አይ እኔ ነኝ ብዙ የገደልኩት›› በሚል ይፎካከራሉ፡፡ ነገር ግን አጃቢዎቹም ወታሮቹም ስለሚተኩሱና አብረው አደኑ ላይ ስለሚካፈሉ በትክክል የእነሱ የስራ ውጤት ብቻ አለመሆኑን፣ ያውቁታል፡፡

አንድ ቀን የንግስቲቱ ልጅ ‹‹በትክክል ጥሩ ተኳሽና ጥሩ አዳኝ መሆናችንን፣ ከእኔና ከአንተ ማን እንደሚበልጥም ለማወቅ ለምን ተደብቀን፣ ማንም ሳይከተለን ወደ ጫካ አንሄድም? ከዚያ ግዳያችንን ይዘን ወደ ማታ እንገናኛለን፡፡ ብዙ የገደለ አሸናፊ ይባላል›› የሚል የፉክክር ጥያቄ ያቀረባል፡፡

በሀሳብ ይስማሙና በጧት አጃቢ ሳያስከትሉ ከቤተ መንግስት ሹልክ ብለው መሳሪያዎቻቸውንና ፈረሶቻቸውን ይዘው፣ ማለቂያ ወደሌለው የሀገራቸው ጫካ ገቡ፡፡ ከዚያም አንድ ቦታ ጀመሩና ‹‹አንተ በዚህ አቅጣጫ ሂድ፤ እኔ ደግሞ በዚህ አቅጣጫ እሄዳለሁ፤ ተመልሰን እዚህ ቦታ እንድንገናኝ›› በሚል ተቀጣጥረው ተለያዩ፡፡

**ሁለቱ ልጆች አጃቢ ሳያስከትሉ፣ ከቤተ መንግስት ሹልክ ብለው የወጡት ለምንድን ነው?**

**ከዚህ በኋላ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?**

የደሀይቱ ልጅ ብዙ አውሬዎችን እየገደለ፣ ከሚገለውም ለምልክት ይሆን ዘንድ ከአካላቸው ትንሽ እየቆረጠ በኮሮጆው እየከተተ፣ በስሜትና በጀግንነት ወደፊት ነጎደ፡ ፡ በሙሉ ትኩረቱ የነበረው አውሬዎችን አነጣጥሮ መግደል እና የገደለውን ቆርጦ መያዝ ስለነበረ፣ እረጅም ጉዞ እንኳን እንደተጓዘ አልታወቀውም ነበር፡፡ ተመልሶ ለመሄድ፣የመጣበትን አቅጣጫ እንኳን በሚገባ አላገናዘበም ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ ብዙ ከገደለ በኋላ ቀኑ እየመሸ ሲሄድ ድንገት ቀና ብሎ ጀምበርን ሲያይ የተቀጣጠሩበት ሰአት መድረሱን አወቀ፡፡ ነገር ግን እንዴት እደሚመለስ ምልክት ባለመያዙ፣ በዚያ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ መንገድ ጠፋበት፡፡ ጫካ ውስጥ ያለ ሰው በጥንቃቄ ምልክት ካላደረገ፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አቅጣጫ መሳቱ የተለመደ በመሆኑ፣ ይህ ልጅ የሄደበትን አቅጣጫ ትቶ፣ በተቃራኒው የባሰ እየራቀ መሄድ ጀመረ፡፡ አንድ ቀን ሙሉ የመጣበትን መንገድ በተቃራኒ አቅጣጫ ስለሄደ፣ ጨርሶ መመለስ እንደማይችል ሲያውቅ ከአንድ ዛፍ ላይ ወጥቶ ምሽቱን ለማለፍ ተገደደ፡፡

(አለማየሁ ዋሴ እሸቴ፡፡ 2012፤ ሰበዝ፤ ገጽ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)

ምዘና

- ✓ ያዳመጡትን ሲገልጹ መከታተል

የተመረጠ ተግባር መልስ

ተግባር አንድ፡-

ሀ. እውነት ለ. ሀሰት ሐ. ሀሰት መ. እውነት ሠ.ሀሰት

ክፍል ሁለት፡- ንባብ

## የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ ‹‹ጓደኛ መሆን›› የሚል ምንባብ በመማሪያ መጽሐፉ ቀርቧል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም ቀጥሎ ባለው ቅደም ተከተል የመማር ማስተማር ተግባሩን ያከናውኑ፡፡

ቅድመ ንባብ፡-

- ✓ በመጀመሪያ በመማሪያ መጽሐፉ ከምንባቡ በፊት ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በቃል ያሰሯቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎቹን ምላሽ ከተቀበሉ በኋላ በየግላቸው በለሆሳስ እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡

የንባብ ሒደት፡-

- ✓ ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ወቅት በሚገባ እያነበቡ መሆናቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፡፡
- ✓ ቀድመው በነገሯቸው መሰረት በሚያነቡበት ወቅት የየአንቀጾቹን ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦች እየለዩ ማስታዎሻ እንዲይዙ ያድርጓቸው፡፡

- በምንባቡ መካከል የሚገኙ ሁለት ጥያቄዎችን ለራሳቸው እየመለሱ ማንበባቸው እንዲቀጥሉ ያሳስቧቸው፡፡

## አንብቦ መረዳት

አንብበው እንደጨረሱም የአንብቦ መረዳት ተግባራቱን ያሰሯቸው፡፡ በዚህ ክፍል ሶስት ተግባራት ያሉ ሲሆን እንደየተግባራቱ ትእዛዞች በሚከተለውመንገድ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

### ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር አራት የማዛመድ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በምንባቡ የቀረቡት አንቀጾች የያዟቸውን ሀሳቦች ከአንቀጽ ቁጥራቸው ጋር በማዛመድ የሚሰሩ ናቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን በደብተራው ላይ በመጻፍ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡

### ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ምርጫ ሲሆኑ በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ትክክለኛውን አማራጭ በመምረጥ እንዲመልሱ ይጠይቃሉ፡፡
- ✓ በጥያቄዎቹ መሰረትም ጥያቄዎቹንና መልሶቻቸውን በደብተራቸው ላይ እንዲጽፏቸው ያድርጓቸው፡፡

### ተግባር 3፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የአጭር መልስ መስጠት ጥያቄዎች ሲሆኑ አንድምታዊ ምላሾችን የሚጠይቁ ናቸው፡፡
- ✓ በዚህም መሰረት ያነበቡትን ምንባብ ከቀደመ እውቀታቸው ጋር በማጣመር ለጥያቄዎቹ አንድምታዊ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ከላይ የቀረቡትን ሶስት ተግባራት አሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልስ ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች ምለሽ ከሰጡ በኋላ የመልስ እርማትና አጠቃላይ አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

ምዘና፡-

✓ ጽሑፎችን አንብበው የተገነዘቡትን እንዲገልጹ ማድረግ

የተግባራት መልሶች

ተግባር አንድ፡-

ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ረድፍ የየአንቀጾቹ ዋና ዋና ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ በ‹‹ለ›› ረድፍ ደግሞ በምንባቡ ውስጥ አንቀጾቹ የሚገኙባቸው ተራ ቁጥሮች ቀርበዋል፡፡ አንቀጾቹ የያዟቸውን ዋና ሀሳቦች ከአንቀጽ ቁጥሩ ጋር በማዛመድ መልሱ፡፡

1. ለ 2. ሀ 3. ሐ 4. መ

ተግባር ሁለት፡-

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡

1. ለ 2. ሀ 3. መ 4. ሐ 5. ለ

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር፡-

በዚህ ክፍል የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ ሁለት ተግባራት ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ተግባት በሚከተለው ቅደም ተከተል በማቅረብ የመማር ማስተማር ሂደቱን ያከናውኑት፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ለቃላት ተመሳሳይ ፍችን እንዲሰጡ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ለቃላቱ ተመሳሳ ፍቺዎቻቸውን እየፈለጉ እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ደግሞ በአንቀጽ ውስጥ ባሉ ክፍት ቦታወች ፊት ለፊት በቅንፍ ውስጥ የተሰጡ ቃላትን ተቃራኒ ፍች እንዲያሟሉ የቀረቡ ናቸው፡፡
- ✓ ለእነዚህ ቃላት ተቃራኒያቸውን በመስጠት አንቀጹን እንዲያሟሉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሁለቱንም ተግባራት ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን አንድ በአንድ ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ መልሶቻቸውን ተቀብለው ከጨረሱ በኋላ የመልስ ማስተካከያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያዎች፡-

- ✓ የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺዎች የሚያሳዩ ፍላሽ ካርዶች

ግምገማ

- ✓ ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ሲሰጡ መከታተል

የተግባራት መልሶች

ተግባር 1፡-

ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ረድፍ የቀረቡት ቃላትና ሐረጋት ቀደም ሲል ካነበባችሁት ምንባብ የወጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ቃላት በምንባቡ ውስጥ ለያዙት ትርጉም ተመሳሳይ ፍችዎቻውን በ‹‹ለ›› ረድፍ ከቀረቡት በመምረጥ እያዛመዳችሁ መልስ ስጡ፡፡

1. ሸ 2. መ 3. ሀ 4. ረ 5. ሐ 6. ሰ

ተግባር 2፡-

ከዚህ በታች በቀረበው አንቀፅ ውስጥ ያሉትን ባዶ ቦታዎች በቅንፍ ውስጥ በቀረቡት ቃላት ተቃራኒ አሟሉ፡፡

1. ጠላት 2. መጥፎ 3. ለበቀል 4. ተቃራኒ

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር !

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የአንቀጽ ተዋቃሪ አካላትን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ይከተሉ፡፡

- ✓ አራተኛ ክፍል ስለአንቀጽን ምንነት በተመለከተ የተማሩትን አስታውሰው እንዲገልጹ ያድርጓቸው፤
- ✓ በመቀጠልም በተማሪዎች መጽሐፍ የቀረበውን ስለአንቀጽ ክፍሎች የሚያወሳ አጭር ማስታዎሻ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመጽሐፉ ላይ የቀረቡትን ማስታዎሻና ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ የአንቀጽ ክፍሎችን ያብራሩላቸው
- ✓ ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ይረዳዎት ዘንድ የአንቀጽ ክፍሎችን ለይቶ የሚያሳይ ቻርት በማዘጋጀት ይጠቀሙ፡፡
- ✓ በመጽሐፉ ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎች ተመሳሳይ ምሳሌዎችን በማምጣት ትምህርቱን ግልጽ ያድርጉላቸው፤
- ✓ ተግባር አንድን በክፍል ስራነት፣ ካሰሩ በኋላ የእርምት መልስ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉ፡፡
- ✓ ተግባር ሁለትን እንዴት መስራት እንዳለባቸው፣ ካስረዱ በኋላ ቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ያድርጉ፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያዎች

- ✓ ኃይለ ቃልንና መዘርዝራዊ ዓረፍነገሮችን ለይቶ የሚያሳይ አንድ አንቀጽ የተጻፈበት ቻርት

ግምገማ

- ✓ አንቀጽ በመስጠት ኃይለ ቃሉንና መዘርዝራዊ ዓረፍተ ነገሮችን ሲለዩ

መከታተል

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

መምህር !

በዚህ ክፍል የወል ስምን እና የተጸውዖ ስምን ይማራሉ። ይህንትምህርትየሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ተከትለው ያቅርቡላቸው።

- ✓ የተጸውዖ ስም እና የወል ስምን በተመለከተ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበውን አጭር ማስታዎሻ መነሻ በማድረግ ያስረዷቸው፤
- ✓ የሁለቱን ምንነት ምሳሌዎቹን መሰረት በማድረግ፣ መጠነኛ ገለፃ ያድርጉላቸው፤
- ✓ በመጽሐፉ ላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች በተጨማሪ ሌሎች ስሞችን በማምጣት ያስረዷቸው፤
- ✓ በመቀጠልም በመጽሐፉ የቀረቡትን መልመጃዎች በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ
  ያድርጉ፣ መስራታቸውን ይከታተሏቸው፤
- ✓ በመጨረሻም በመልመጃዎቹ መልሶች ላይ ተማሪዎቹን በማወያየት ትምህርቱን ያጠቃሉት።

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያዎች፡-

- ✓ የወልና የተጸውኦ ስምን ለይቶ የሚያሲያይ ቻርት

ግምገማ

- ✓ የወልና የተጸውኦ ስሞችን እንዲለዩ በማድረግ መከታተል።

የሰዋሰው ተግባራትና ጥያቄዎች መልስ፡-

### ተግባር፡-

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ በማዘጋጀት፣ ቀጥሎ ከ"ሀ" እስከ "ተ" የተዘረዘሩትን ቃላት በትክክለኛው የስም ምድባቸው ላይ የ‹√› ምልክት በማድረግ መልሱ።

| ተ.ቁ | ቃል | የወል ስም | የተጸውዖ ስም |
|---|---|---|---|
| ሀ | አባይ | | √ |
| ለ | ወንዝ | √ | |
| ሐ | ቀበና | | √ |
| መ | ልጅ | √ | |
| ሠ | ንጉስ | √ | |
| ረ | ፈረስ | √ | |
| ሰ | ወርቅሸ | | √ |
| ሸ | አለማየሁ | | √ |
| ቀ | ነብር | √ | |
| በ | አፍሪካ | | √ |
| ተ | ዘበርጋ | | √ |

# አማርኛ
(፫) ክፍል

# ምዕራፍ ሁለት
# ጽዳትና ንጽሕና

(18 ክፍለ ጊዜ)

የምዕራፉ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ የሚነበብላቸውን አዳምጠው ይመልሳሉ፡፡
- ✓ ሰዎች ንጽሕናቸውን ለመጠበቅ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ይገልጻሉ፡፡
- ✓ ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ በትክክል ያነባሉ፡፡
- ✓ መጣኝ ርዕስ በመምረጥ አጭር አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ✓ በአዳዲስ የይዘት ቃላት ላይ ይወያያሉ፡፡
- ✓ የድምጾችና የምእላዶችን መዋቅር ይገነዘባሉ፡፡

ይዘት፡-

- ✓ አዳምጦ ማስታዎሻ መያዝ
- ✓ በቡድን ውይይት ውስጥ መሳተፍ
- ✓ የክፍሉን ደረጃ ባገናዘበ መልኩ አቀላጥፎ ማንበብ
- ✓ አጭር አንቀጽ መጻፍ
- ✓ በአዳዲስ ቃላት ይዘት ላይ መወያየት
- ✓ ውስብስብ ምእላድን በማጣመር እና በመነጠል መለየት

## ክፍል አንድ:- ማዳመጥና መናገር

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች አዳምጠው መረዳትን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማስተማር ይረዳ ዘንድ ቀጥሎ የሚያነቡላቸው ምንባብ ቀርቧል፡፡ የትምህርቱን ዓላማዎች ለማሳካት ይረዳዎት ዘንድ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ይከተሉ፡፡

### ቅድመ ማዳመጥ

- ✓ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪው መጽሐፍ የቀረቡትን ሁለት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎችን ጠይቋቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን መልስ በመቀበል ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ ያሳስቧቸው፡፡

### የማዳመጥ ሒደት

- ✓ ተማሪዎቹ ማስታዎሻ እየያዙ እንዲያዳምጡ ነግረው ለሁሉም ተማሪዎች በሚሰማ ድምጽ ያንብቡላቸው፡፡

የማዳመጥ ጊዜ እያነበቡ በማዳመጥ ጊዜ ያሉ ጥያቄን ቆም በማለት ተማሪዎችን ይጠይቋቸው ምላሻቸውንም በማስታዎሻ ደብተራቸው እንዲጽፉ ይጠቁሟቸው፡፡

### አዳምጦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበውላቸው ከጨረሱ በኋላ በአዳምጦ መረዳት ስር 2 ተግባራት ሲኖሩ ጥያቄዎቹን አሰሯቸው፡፡

ተግባር 1

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ከምንባቡ ሀሳብ በቀጥታ የሚመለሱ ናቸው፡፡
- ✓ በዚህም መሰረት ተማሪዎቹ በቃላቸው እንዲመልሱ በማድረግ መልሳቸውን ተቀበሏቸው፡፡ መምህር የመናገር ችግር ያለበት ተማሪ ካለዎት በምልክት ቋንቋ ተጠቅሞ ለጥቄዎቹ ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቱዋቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች መልስ ሰጥተው ከጨረሱ በኋላ ማስተካከያ በመስጠት ወደ ቀጣዩ ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጡት ምንባብ ውስጥ የያዙትን ማስታዎሻ መሰረት በማድረግ ተወያይተው የውይይታቸውን ጠቅላላ ሀሳብ በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ አቅርበው ከጨረሱ በኂላ የማጠቃለያ አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

## የአካባቢ ንጽህና

ጤናማና ደስተኛ ህይወት ለመምራት የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የመኖሪያ አካባቢያችን ንጽህና ካልተጠበቀ፣ የበሽታ አምጪ ተህዋስያንና የበሽታ አስተላላፊ ነፍሳት ምቹ ሁኔታ ስለሚፈጠርላቸው በቀላሉ ጤናችን ሊታወክ፣ ደስተኛ ህይወታችን ሊቃወስ ይችላል፡፡ በመሆኑም፣ ከግል ንጽህናችን ባልተናነሰ ደረጃ የአካባቢ ንጽህና ሊያሳስበን ይገባል፡፡

አካባቢያችን በተለያዩ ምክንያቶች ሊበከል ይችላል፡፡ በአግባቡ ያልተወገደ የቤት ጥራጊና ፍሳሽ ቆሻሻ ፣ ሰዎች በየመንገዱ ጥለውት የሚሄዱት የማሸጊያ ወረቀት እና የፍራፍሬ ልጣጭ አካባቢን ያቆሽሻል፡፡ በየቦታው መጸዳዳትም የአካባቢ ንጽህና ጉድለት ያስከትላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከመኪናዎች ና ከፋብሪካዎች የሚለቀቁ መርዛማ ጋዞችና ፈሳሾች ለአካባቢ መበከል ትልቅ አስተዋጽዖ አላቸው፡፡

አካባቢያችንን የሚበክሉት ዋና ዋና ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ጤናማ አካባቢን መፍጠር የሚቻለው እንዴት ነው?

በመሆኑም ንጽህናው የተጠበቀና ጤናማ አካባቢን ለመፍጠር የተለያዩ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የቤት ውስጥ ቆሻሻን በአገባቡ የማስወገድ ባህል ማዳበር ይገባል፡፡ የቤት ውስጥ ቆሻሻ ፈሳሽ ወይም ደረቅ ሊሆን ይችላል፡፡

ደረቅ ቆሻሻም በቀላሉ የሚበሰብስ ወይም የማይበሰብስ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም እነዚህን የተለያየ ባህሪ ያላቸው የቤት ውስጥ ቆሻሻዎች፣ እንደ የባህሪያቸው አግባብነት ባለው መንገድ ማከማቸትና ማስወገድ የአካባቢ ንጽህናን ለመጠበቅ ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡

ለአካባቢ ንጽህና መጠበቅ መሻሻል ያለበት ሌላው ጉዳይ፣ የሰዎች የመንገድ ላይ ቆሻሻ አወጋገድ ልምድ ነው፡፡ ሰዎች ከቤት ውጪ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ የማስቲካና ከረሜላ ማሸጊያዎችንና የፍራፍሬ ልጣጮችን የመሳሰሉ ነገሮችን ሲያስወግዱ የአካባቢን ጽዳትና ውበት በማያውክ መልኩ መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ሰዎች በየቦታው ከመጸዳዳት መታቀብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሌላውና አንገብጋቢው ጉዳይ፣ ከመኪናዎችና ፋብሪካዎች የሚለቀቁት መርዛማ ፍሳሾችና ጋዞች ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች የሚቀንሱበትና በአግባቡ የሚወገዱበት ሁኔታ ካልተፈጠረ የአካባቢ ንጽህና በእጅጉ ይጓደላል፡፡

በአጠቃላይ ለጤናማና ደስተኛ ሕይወት የግልና የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የአካባቢ ንጽህናን የሚያጓድሉ መንስዔዎችን ጠንቅቆ ማወቅና ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባል፡፡

ምዘና

- ✓ የቡድን ውይይቱ በምን ላይ ያተኮረ እንደሆነ በማዳመጥ ደግመው ሲገልጹ መከታተል፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

በዚህ ክፍል ተማሪዎች አቀላጥፎ ማንበብን ይማራሉ፡፡ ለትምህርቱ ማስተማሪያነትም በመማሪያ መጽሐፉ ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም የመማር ማስተማር ሒደቱን እንደሚከተለው ያከናውኑ፡፡

## ቅድመ ንባብ

- ✓ በመጀመሪያ ምንባቡን ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት ሁለቱን የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ለተማሪዎቹ ያቅርቡላቸው፡፡

በቅድመ ምንባብ ጥያቄዎቹ ተማሪዎች ለማንበብ ከተዘጋጁ በኋላ ተማሪዎች ምንባቡን አንድ በአንድ ድምጻቸውን እያሰሙ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ መምህር አይነ ስውር ተማሪ በክፍል ውስጥ ካሎት አንባቢ በመመደብ አልያም በብሬል የተገለበጠ መፀሀፍ ካለ እንዲጠቀም ያድርጉ፡፡

## የማንበብ ሒደት

- ✓ ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ወቅት ቃላትን ሳይገድፉ፣ በተገቢው አነባበብና ፍጥነት ማንበብ እንደሚጠበቅባቸው ያሳስቧቸው፡፡
- ✓ በሰጧቸው መመሪያ መሰረት እያነበቡ መሆናቸውን ይከታተሏቸው፡

## አንብቦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ የድህረ ምንባብ ተግባራትን እንዲሰሩ ያደርጓቸው፡፡

ተግባር 1

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ላሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ መልስ እየመረጡ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹ በቀጥታ ከምንባቡ የወጡ ሲሆኑ የምንባቡን ሀሳብ መሰረት አድርገው መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

ተማሪዎቹ መልስ ሰጥተው ከጨረሱ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ እርማት በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ሁለት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን ተማሪዎች ያለገደብ እንዲመልሱ የሚጠይቁ ናቸው፡፡
- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ሀሳቦቻቸውን በመግለጽ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ማጠቃለያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ መንገዶችን የሚያሳይ ቻርት

ምዘና

- ✓ ተማሪዎች የምንባብ ታሪክን መሰረት ያደረጉ ተግባራትን እንዲመልሱ ማድረግ

የተመረጠ ተግባር መልስ

ተግባር 1፡-

ለሚከተሉት ጥያቄዎቸ በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ለ | 3. ለ | 5. ሀ | 7. መ | 9. ለ |
| 2. መ | 4. ሀ | 6. መ | 8. ለ | |

ክፍል ሶስት፡- ቃላት

የትምህርቱ አቀራረብ

በዚህ ክፍል ለቃላት ፍቺ መስጠት እና የተጓደሉ ቃላትን በአንቀጽ ውስጥ ማስገባትን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ ሁለት ተግባራት የቀረቡ ሲሆን ተግባራቱን በሚከተለው ቅደም ተከተል ያቅርቡት፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ ስር ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍች እንዲሰጡና በፍችዎቻቸው ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር 2

- ✓ በቀረበው አንቀጽ ላይ ከተሰጡት ቃላት እየመረጡ አንቀጹን እንዲያሟሉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሶቻውን በመቀበልና አብሮ በመስራት እርማት ሰጥተው ትምህርቱን ያጠቃልሉ፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የቃላት ፍችዎችን የሚያሳይ ፍላሽ ካርድ

ምዘና

- ✓ ተማሪዎች የአዳዲስ ቃላት እውቀት ክምችት ማዳበራቸውን መከታተል

የተመረጡ ተግባራት መልሶች

ተግባር 2፡-

ቀጥሎ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ ለሚገኙት ክፍት ቦታዎች ከጽሑፍ በላይ ከተሰጡት ቃላት በመምረጥ ሙሏቸው፡፡

1. መሰረት
2. አፍታ
3. ታማኞች
4. ቢዳረጉ
5. በማሳሳታቸውም

ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

የትምህርቱ አቀራረብ

በጽሕፈት ክፍል አንቀጽ መጻፍ ይማራሉ፡፡ አንቀጽ ከመጻፋቸው በፊት ቢጋር ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንን ትምህርት በሚገባ በማስተማር ተማሪዎች መጻፍን እንዲለማመዱ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት በመከተል ትምህርቱን ያቅርቡት፡፡

- ✓ በመጀመሪያ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያለውን አጭር ማስታዎሻ ያጽፏቸው፤ እንዲሁም የተሰጠውን ምሳሌ አብራርተው ይግለጹላቸው።
- ✓ ቢጋሩን ካብራሩላቸው በኋላ ቢጋሩ እንዴት ወደ አንቀጽ ጽሑፍ እንደተቀየረ ከቢጋሩ ቀጥሎ ያለውን አንቀጽ በማሳየት ግልጽ ያድርጉላቸው።
- ✓ በመቀጠልም በተሰጡት የአንቀጽ መጻፊያ ርእሶች ወይም ሌላ የራሳቸውን ርዕስ መርጠው ቢጋር እንዲያዘጋጁ ያድርጓቸው።
- ✓ በመጨረሻም ያዘጋጁትን ቢጋር በመመልከት ማስተካከያ ሰጥተው ትምህርቱን ያጠቃልሉ።

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያዎች

- ✓ የመጻፊያ ይዘቶችን የሚያሳይ የቢጋር ሰንጠረዥ ቻርት

ምዘና

- ✓ አጭር አንቀጽ በቤታቸው ፅፈው እንዲመጡ በቤት ስራ መልክ መስጠት።

የትምህርቱ አቀራረብ

ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን በትክክለኛው የምእላድ አከፋፈል መነጣጠልንና ማጣመርን ይማራሉ። ትምህርቱን በሚገባ ለመስጠት የሚከተለውን ሒደት ተከትለው ያቅርቡት።

- ✓ በተማሪዎች መጽሐፍ ምእላድን የተመለከተ አጭር ማስታዎሻ ቀርቧል፤ ማስታዎሻውን እንዲጽፉ ያድርጓቸው።

- ✓ በመቀጠልም የተሰጡትን ምሳሌዎች ዋቢ በማድረግና የራስዎንም ሌሎች ምሳሌዎች በመጨመር የምእላድን ምንነት በተመለከተ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ለ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ምእላድ የሚከብድ ትምህርት ሊሆን ስለሚችል ቀላል ቀላል ቃላትን በማምጣት በትክክለኛው የምእላድ አከፋፈል እየከፈሉ ያስረዷቸው፡፡
- ✓ የምእላድን ትምህርትና የቃላትን መነጠልና ማጣመር ጽንሰ ሀሳብ በሚገባ ከተገነዘቡ በኋላ ተግባራቱን ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1

- ✓ በምእላድ የተነጣጠሉ ቃላት አሉ፡፡ ቃላቱን አጣምረው እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር 2

- ✓ ልዩ ልዩ ቃላት የቀረቡ ሲሆን በትክክለኛው የምእላድ አከፋፈል እንዲነጣጥሉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች ተግባራቱን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ የተግባራቱን መልሶች አብረው ሰርተው ማስተካከያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የተለያዩ የተነጣጠሉ ምእላዶችን የያዘ ቻርት

ምዘና

- ✓ ቃላትና በትክክለኛው የምእላድ አከፋፈል ስርዓት እንዲነጥሉና እንዲያጣምሩ ማድረግ

የተመረጡ ተግባራት መልሶች

ተግባር 1፡- ቀጥሎ ተነጣጥለው የቀረቡትን ምእላዶችን በማጣመር ቃላት መስርቱ።

ሀ. ሚዛንህ　　　　ሐ. ጆሮው　　　　ሠ. ቆዳው

ለ. ልጅነት　　　　መ. ትምህርትሽ

ተግባር 2፡- የሰሚከተሉትን ቃላት በትክክለኛው የምእላድ አከፋፈል ነጣጥላችሁ ጻፉ።

ሀ. ደብተር - ህ　　　　ሐ. ጨረሰ - ች　　　　ሠ. ሰፊ - ው

ለ. አልጋ - ዋ　　　　መ. ቆንጆ - ዎች

# አማርኛ

(፫) ክፍል

# ምዕራፍ ሶስት

# ልማድ

(18 ክፍለ ጊዜ)

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች:-

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:-

- ✓ አንድን ታሪክ አዳምጠው ይተርካሉ፡፡
- ✓ ተገቢውን ድምጸት ጠብቀው ጽሑፍን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያነባሉ፡፡
- ✓ የአንቀጽ አይነቶችን ይለያሉ፡፡
- ✓ ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ✓ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ተውሳከ ግሶችን ይለያሉ፡፡

ይዘት:-

- ✓ ታሪኩን አዳምጦ መተረክ
- ✓ ተገቢውን ድምጸት ጠብቆ በጮክታ ማንበብ
- ✓ የአንቀጽ አይነቶችን መለየት
- ✓ ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ መስጠት
- ✓ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ተውሳከ ግሶችን መለየት

## ክፍል አንድ፦ ማዳመጥና መናገር

የትምህርቱ አቀራረብ፦

መምህር!

ቀጥሎ ማዳመጥና መናገርን ለማስተማር የቀረበ ‹‹ቶክ ቤት›› የሚል ምንባብ ይገኛል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም የመማር ማስተማር ሒደቱን እንደሚከተለው ያከናውኑ፡፡

### ቅድመ ማዳመጥ

- ✓ ምንባቡን ከማበብዎት በፊት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን ሁለት የቅድመ ማዳመጥ ተግባራት ተማሪዎቹን ያሰሯቸው

ተግባር 1፦

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ከሚያነቡላቸው ምንባብ የወጡ አራት ቃላት ይገኛሉ፡፡ ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍቺዎች ቀድመው እንዲረዱ ያግዙ ዘንድ የቀረቡ ናቸው፡፡
- ✓ በመሆኑም ቃላቱን በሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸውና ፍቺዎቻቸውን በቃል እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡ የተማሪዎቹ ምላሽ ተከትለው በምንባቡ ያላቸውን ዓውዳዊ ፍቺ ይግለጹላቸው፡፡

ተግባር 2፦

- ✓ በዚህ ተግባር አንድ ጥያቄ የቀረበ ሲሆን የሚያዳምጡት ምንባብ ስለምን እንደሚያወሳ ቀድመው እንዲገምቱ ይረዳቸዋል፡፡
- ✓ በመሆኑም የተማሪዎችን መልስ በመቀበል የሚነበብላቸውን ምንባብ ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ አሳስቧቸው፡፡

### የማዳመጥ ሒደት

- ✓ ተማሪዎቹ ማስታዎሻ እየያዙ እንዲያዳምጡ ነግረው ለሁሉም ተማሪዎች በሚሰማ ድምጽ ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ በሚያነቡበት ወቅት የመስማት ውስንነት ያለባቸው ተማሪዎችን ታሳቢ በማድረግ በተመጣጣኝ ድምጸትና በግልጽ ሊመለከቱዎት በሚችሉበት ቦታ ሆነው ያንብቡላቸው፡፡

- ✓ ምንባቡን በማንበብ ላይ እያሉ በመሀል በማዳመጥ ጊዜ ያሉ ጥያቄዎችን ቆም በማለት ተማሪዎችን ይጠይቋቸው ምላሻቸውንም ተከትለው ማንበብዎን ይቀጥሉላቸው፡፡

## አዳምጦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ ሁለት ተግባራት ስር የሚገኙትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች ሲሆኑ በቀጥታ ካዳመጡት ምንባብ የወጡ ናቸው፡፡
- ✓ በመሆኑም ተማሪዎቹ በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ በማድረግ ያሰሯቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሶቻቸውን በጋራ በመስራት እርማት ሰጥተው ወደ ቀጣዩ ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በተግባር 2 የቀረቡት ጥያቄዎች ሶስት ሲሆኑ አንዱ አጠቃላዩን የምንባቡን ሀሳብ እንዲገልጹ የሚጠይቅ ነው፤ እንዲሁም ቀሪዎቹ ሁለት ጥያቄዎች ያዳመጡትን ምንባብ ቀድሞ ከሚያውቋቸው ጉዳዮች ጋር በማጣመር የሚመለሱ ናቸው፡፡
- ✓ የምንባቡን ሀሳብ እንዲገልጹ ለሚጠይቀው ጥያቄ ተማሪዎች በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ እንዲሁም ቀሪዎቹን ሁለት ጥያቄዎች በቤት ስራ መልክ ሰርተው እንዲመጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በቀጣዩ ጊዜም ተማሪዎቹ መስራታቸውን ካረጋገጡ በኋላ የተወሰኑ ተማሪዎችን

  በመምረጥ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ በመጨረሻም ለተማሪዎቹ ስራዎች ግብረ መልስ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት።

## ቶክ ቤኣ

አገራችን ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔረሰቦች አገር በመሆኗ፣ የተለያዩ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ኃይማኖታዊ እሴቶች ባለጸጋ ናት። የዳውሮ ብሔረሰብም ከነዚሁ አንዱ ሲሆን በደቡብ ክልል ካሉ 56 ብሄረሰቦች መካከል የሚጠቀስ ነው። የዳውሮ ብሄረሰብ "ቶክ ቤኣ" የሚባል የዘመን መለወጫ በዓል አለው።

"ቶክ ቤኣ" ማለት ጥሬ ትርጉሙ መዝኖ ማየት ማለት ሲሆን፣ በዳውሮ ብሄረሰብ የአሮጌ ዓመት መጨረሻ ወይም በአዲሱ ዓመት ዋዜማ ዕለት ማታ የሚከበር በዓል ነው። አዲሱ ዓመት የጥጋብ፣ የሰላም፣ የጤናና ምርታማነት ዓመት እንዲሆን በመመኘት በዓሉን፣ በሚገባ ተመግበው በደስታ ያከብራሉ።

"ቶክ ቤኣ" በበዓሉ ዋዜማ ዕለት ማታ ሁሉም የቤተሰብ አባላትም ሆኑ እንስሳት በልተውና ጠግበው የሚያድሩበት ዕለት ነው። ‹‹በዕለቱ በደንብ በልቶና ጠግቦ ካደረ ዓመቱን ሙሉ ጥጋብ ይሆንለታል›› ተብሎ ይታመናል።

የዳውሮ ብሄረሰብ የዘመን አቆጣጠር የጨረቃ ወራትን መሰረት ያደረገ ነው። በዚህ መሰረት የዳውሮ ጊዜ አቆጣጠር አስራ ሁለት ወራት ይኖሩታል። በጥንት ጊዜ ከነሀሴ ወር መጨረሻ እስከ መስከረም ወር ጨረቃ መታያ ድረስ ያሉት ቀናት‹‹የቶክ ቤኣ ቀናት›› ተብለው ይወሰዱ ነበር። ባሁኑ ጊዜ ግን፣ ከኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ጋር በዓሉን በማመሳሰል፣ "ቶክ ቤኣ" በጳጉሜ የመጨረሻ ቀን ማታ እየተከበረ ይገኛል። በእነዚህ አምስት ቀናት የበዓሉ ዝግጅት ሲደረግ ይቆይና ፣ በዋዜማው ዕለት ማታ ሁሉም የቤተሰብ አባላት ባሉበት በዓሉ በድምቀት ይከበር ነበር። በዚሁ ጊዜም ሁሉም ሰው ቤት ያፈራቸውን ባህላዊ ምግቦች እስኪጠግቡ በልተው ያድራሉ። የቤት እንስሳትም ቢሆኑ፣ ሳር ታጭዶላቸው በሚገባ በልተውና ጠግበው እንዲያድሩ ይደረጋል።

**በመደበኛው የኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ በዐል አከባበር እና በዳውሮ ዘመን መለወጫ አከባበር መካከል ምን ልዩነት አስተዋላችሁ?**

**በዳውሮ ዘመን መለወጫ አከባበር ስነ ስርዓት ላይ ልጆች፣ ወጣት ወንዶች እና ልጃገረዶች ምን ምን ሚና የሚኖራቸው ይመስላችኋ?**

የ"ቶክ ቤኣ" በዓል እራት ከተበላ በኋላ የሰፈር ልጆች ተሰብስበው የተለያዩ ዜማዎችን እያዜሙና እየጨፈሩ፣ ሰፈር ለሰፈር በመሄድ ከአካባቢው ሰዎች ስጦታ እየሰበሰቡ ይዞራሉ፣ የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችንም ይጋበዛሉ።

ልጃገረዶች ደግሞ፣ አንዲት እናት ቤት በመሰብሰብ ያዘጋጁትን እንሶስላ፣ አንዷ በአንዷ ጣት ላይ እያሰሩና እያጌጡ አምሽተው፣ አብረው ያድራሉ፡፡ ሌሊቱ ሲነጋ፣ ልጃገረዶቹ በአንድ ላይ ሆነው የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን እየዘፈኑ፣ እነሱም እንደ ወንዶቹ ሰፈር ለሰፈር ይዞራሉ፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ወንዶቹ የገንዘብ ሳይሆን፣ የምግብና የመጠጥ ስጦታ ይቀበላሉ፡፡ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የሚጨፍሩት በየቡድናቸው ሆነው ነው፤ ያንዱ ቡድን አባል ወደ ሌላ ቡድን አይቀላቀልም፡፡

በአጠቃላይ የ"ቶክ ቤአ" በዓል፣ የህዝቡን ማህበራዊ ግንኙነትና መንፈሳዊ ህይወት ያጠናክራል፡፡አንዱ ከሌላው የልምድ ልውውጥ እንዲያደርግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ዓመቱን በሙሉ በስራ የደከመ አዕምሮ እንዲያርፍ በማድረግ ፣ ሰዎች አዲሱን ዓመት በመነቃቃት መንፈስ እንዲቀበሉት ያደርጋል፡፡ በመሆኑም፣ በዓሉ ከየትኛውም ባህል ብረዛ ነጻ በሆነ መንገድ፣ ቱባነቱን በመጠበቅና የብሄረሰቡን የወራት አቆጣጠር መሰረት በማድረግ ቢከበር፣ የበለጠ ባህላዊነቱን ይጠብቃል፡፡

(ምንጭ፡ የዳውሮ ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ፣ዎንታ መፅሄት፣ ቀጥር 11፣ ገጽ 8 መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ፣ 2008ዓ.ም)

ምዘና፡-

- ✓ ተማሪዎች ያዳመጡትን ሲተርኩ መከታተል፡፡

የተመረጠ ተግባር መልስ፡-

ተግባር 1፡-

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ሐ 2. መ 3. ለ 4. ሀ 5. ለ

ክፍል ሁለት፡- ንበብ

የትምህርቱ አቀራረብ፡-

መምህር!

በክፍል ሁለት የቀረበው ምንባብ ተማሪዎች ተገቢውን ድምጸት ጠብቀው ማንበብን ለማስተማር የሚያገለግል ነው፡፡ይህንን ትምህርት ለማቅረብ የሚከተለውን የማስተማር ሒደት ተከትለው ያከናውኑ፡፡

### ቅድመ ንባብ

- ✓ ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ሁለቱን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸው፡፡
- ✓ በሰሌዳው ላይ የተጻፉትን ጥያቄዎች በቃል ካሰሯቸው በኋላ ጥንድ ጥንድ በመሆን ድምጻቸውን እያሰሙ እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ ዐይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ ምንባቡን የሚያነብላቸው ሰው መድቡላቸ፤ ወይም በትምህርት ቤቱ በብሬል የተዘጋጀ መጽሐፍ ካለ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

### የንባብ ሒደት

- ✓ ተማሪዎች በማንበብ ላይ እያሉ የማንበብ ተግባሩን በሚገባ እያከናወኑ መሆናቸውን እየተዘዋወሩ ይፈትሹ፤ አስፈላጊ ሲሆንም ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

### አንብቦ መረዳት

- ✓ ለማንበብ የተሰጠው ጊዜ ሲጠናቀቅ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንደ የመመሪያዎቻቸው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች በጽሑፍ የሚሰሩ ሲሆኑ በደብተራቸው ጽፈው መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ከተማሪዎች መልስ በማስከተልም እርማት በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች በቃል የሚመለሱ ሲሆኑ በቃል የሚመለሱ ናቸው፡፡
- ✓ ከምንባቡ ያገኙትን ግንዛቤ ከቀደመ እውቀታቸው ጋር በማጣመር በቃል እንዲመልሱ ያድረጓቸው፤ መልሶቻቸውንም እያበረታቱ ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ ከተማሪዎቹ ምላሽ በኋላ የማጠቃለያ አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የተመረጡ ተግባራት መልሶች

ተግባር 1፡-

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡

1. ሀ 2. መ 3. ሀ 4. ለ 5. ሀ

ክፍል ሶስት፡- ቃላት

የትምህርቱ አቀራብ፡-

መምህር!

በክፍል ሶስት ተማሪዎች ዓውዳዊ ፍቺን ይማራሉ፡፡ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ተከትለው ትምህርቱን ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ የቃላት ዓውዳዊ ፍቺን በተመለከተ በምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ የቃላት ዓውዳዊ ፍቺ በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ፍቺ እንደሚያመለክት በምሳሌዎች አስደግፈው ይግለጹላቸው፡፡

- ✓ በመቀጠልም በተግባር 1 እና 2 የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ከማድረግዎ በፊት በየተግባራቱ የቀረቡትን ምሳሌዎች አብራርተው ይግለጹላቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ዓውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን በደብተራቸው በመጻፍ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የሚሰጧቸው ፍቺዎች ዓውዳዊ እንደሆኑ አሳስቧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ ምላሾቻቸውን በመቀበል የማስተካከያ እርማት ይስጧቸው፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ደግሞ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ከሚገኙ ቃላት ውስጥ የተሰመረባቸውን ዓውዳዊ ፍቺዎች እንዲሰጡ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን በተግባር 1 እንደሰሩት ሁሉ በተመሳሳይ በደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን ለመመለስ ያመቻቸው ዘንድም ከጥያቄዎቹ ቀድመው የቀረቡትን ምሳሌዎች አብረው በመስራት ያለማምዷቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን በመቀበል የመልስ እርማት ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ዓውዳዊ ፍቺዎችን የተመለከተ ክለሳ በማድረግ ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ፡-

- ✓ የቃላትን ዓውዳዊ ፍቺ የሚያመለክቱ ፍላሽ ካርዶች

ምዘና፡-

- ✓ ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ ሲሰጡ መከታተል፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ማስታዎሻ

### የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶች

አንቀጽ የሚባለው ተመሳሳይ ሀሳብ የያዙ ዓረፍተነገሮችን የሚይዝ አነስተኛው የድርሰት ክፍል እንደሆነ በምዕራፍ አንድ ተምራችኋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ከአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶች ውስጥ ሁለቱን ትማራላችሁ፡፡ ከእነዚህ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶች ውስጥ ገላጭ አንቀጽ ማስፋፊያ እና ተራኪ አንቀጽ ማስፋፊያ ይገኙበታል፡፡

ገለጻ ስልት ፡- ስለአንድ ነገር ምንነት፣ አገልግሎት፣ አሰራር፣ አጠቃቀም፣ ወዘተ. ለመግለጽ የሚጠቅም የአንቀጽ አይነት ነው፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ምሳሌ ገላጭ አንቀጽ ሲሆን ገላጭ ያስባውም ስለባህል ምንነት ገለጻና ማብራሪያ የሚሰጥ አንቀጽ በመሆኑ ነው፡፡

ባህል ሲባል በሕብረተሰብ ታሪክ ሒደት ውስጥ መላውን የሰው ልጅ የፈጠራቸውን ቁሳዊና መንፈሳዊ ቅርሶችንና እንዲሁም እነዚህ ቁሳዊና መንፈሳዊ የባህል ግንኙነቶች የተፈጠሩበትን፣ ግልጋሎት ላይ የሚውሉበትንና የሚተላለፉበትን ዘዴዎች ያጠቃልላል፡፡ ቁሳዊ ባህል የሚባለው የሰው ልጅን ቁሳዊ ክንውንና ውጤቶችን የሚሸፍን መስክ ሲሆን ይህም የቴክኒክ መገልገያ መሳሪያዎችን፣ የማምረት ልምድንና ሌሎችንም ቁሳዊ ሀብቶች በማጠቃለል ይይዛል፡፡

(ምንጭ፡- ዳኛቸው ወርቁ፤ 1977፤ የጽሑፍ ጥበብ መምሪያ፤ ገጽ 196)

የትረካ ስልት፡- ስለአንድ ድርጊት ወይም ሁነት በጊዜ፣ በቦታና በሁኔታ ቅደም ተከተል የሚያብራራና የሚተርክ የአንቀጽ አይነት ነው፡፡ የሚከተለው አንቀጽ ለተራኪ አንቀጽ ምሳሌ ሲሆን ተራኪ አንቀጽ ያስባለውም በሁለት ጓደኛሞች መካከል ስለተፈጠረ ታሪክ በጊዜና በሁኔታ ቅደም ተከተል የሚተርክ በመሆኑ ነው፡፡

ባሻ አራምዴ ዛሬ አርጅተው ከቤት ውለዋል፤ ዐይናቸውን እርጅና ይከልለው እንጂ ልባቸው ብዙ ያያል፤ የወለዷቸው ልጆች ብዙ ስለሆኑ ባሻ አራምዴ በሚገባ ተይዘው የሚጦሩ ናቸው፡፡ ስድስቱ ልጆቻቸው ቀድመዋቸው ባይሞቱ ኖሮ ዛሬ የአስራ አራት ልጆች አባት ይሆኑ ነበር፤ ዐይናቸውንም የተተናኮላቸው ይኸው የልጆቻቸው ሀዘን ጠንቅ ሆኖ ነው ይባላል፡፡

(ምንጭ፡ ጳውሎስ ኞኞ፣ 2009፣ የጳውሎስ ኞኞ ስብስብ ስራዎች፣ ገጽ 27)

የትምህርቱ አቀራብ፡-

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ስለአንቀጽ አይነቶች ይማራሉ፡፡ ከአንቀጽ አይነቶች ውስጥ ለ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ይመጥናል ተብለው የታሰቡት ገላጭ አንቀጽ እና ተራኪ አንቀጽን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ይከተሉ፡፡

- ✓ በመጀመሪያ የአንቀጽ ምንነትንና ተዋቃሪዎችን በተመለከተ በምዕራፍ አንድ ስለተማሩት ተወያይተው ሀሳባቸውን በቃል እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ የተማሪዎችን ገለጻ ተመርኩዘው አጭር ክለሳ በማድረግ ተያያዥ ስለሆነው የአንቀጽ አይነቶች እንደሚማሩ ይግለጹላቸ፡፡

- ✓ በመቀጠል ከላይ ያለውን አጭር ማስታዎሻ በመጻፍ ማስታዎሻውን ከተሰጡት ምሳሌዎች ጋር እያገናዘቡ እንደ ክፍሉ ነባራዊ ሁኔታ ከሶስት እስከ አምስት ተማሪዎችን የያዘ ቡድን መስርተው እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡

ተወያይተው እንደጨረሱ ስለአንቀጽ አይነቶች የተገነዘቡትን በቡድን ተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ በመቀጠልም የተማሪዎቹን ገለጻ ተመርኩዘው በምሳሌዎቹ የታገዘ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

- ✓ ከገለጻው በኋላ በሁለቱ ተግባራት ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ሁለት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን የአንቀጾቹን አይነት የሚጠይቁ ናቸው፡፡ እርስዎም ተማሪዎቹ የአንቀጾቹን አይነት እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ የአንቀጾቹን አይነት ከገለጹ በኋላ ትክክለኛውን የአንቀጽ አይነትና ምክንያት አብራርተው ይግለጹላቸው፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር አንቀጽ የመጻፊያ ርእሶች ቀርበዋል፡፡ ተማሪዎቹ አንዱን ርእስ በመምረጥ ተራኪ ወይም ገላጭ አንቀጽ እንዲጽፉ በቤት ስራ መልክ ይስጧቸው፡፡

- ✓ በቀጣዩ ክፍለ ጊዜም የተማሪዎቹን ስራዎች በመሰብሰብ ጽሑፎቻቸው የአንቀጽ ባህርያትን ማሟላታቸውን ያረጋግጡ፤ ጽሑፎቻው ያለባቸውን ክፍተትም በጽሑፍ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት እንዲያስተካክሉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ለተማሪዎቹ ጽሑፎች ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ፡-

- ✓ ናሙና ተራኪ እና ገላጭ አንቀጽን የያዙ ቻርቶች

ምዘና፡-

- ✓ የአንቀጽ አይነቶችን ሲለዩና ሲጽፉ መከታተል፡፡

የተመረጡ ተግባራት መልሶች፡-

ተግባር1፡-

ከዚህ በታች የቀረቡት አንቀጾች እያንዳንዳቸው የትኛው የአንቀጽ አይነቶች እንደሆኑ ግለጹ፡፡

ሀ. ተራኪ አንቀጽ ለ. ገላጭ አንቀጽ

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

መምህር!

የዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ትምህርት ተውሳከ ግስ ነው፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ የሚከተለውን ቅደም ተከተል ይተግብሩ፡፡

- ✓ በመጀመሪያ ተውሳከ ግስን ለተማሪዎቹ ያስተዋውቋቸው፤ ርእሱንም በሰሌዳው ላይ በመጻፍ ያመልክቷቸው፡፡

- ✓ በመቀጠል በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበውን አጭር ማስታዎሻ ያስጽፏቸው።
- ✓ ማስታዎሻውን ጽፈው ከጨረሱ በኋላ በምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻና ማብራሪያ ይስጧቸው።
- ✓ ትምህርቱን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ በማስታዎሻው ላይ ከቀረቡት ተውሳከ ግሶች በተጨማሪ ሌሎችንም በማምጣትና በዓረፍተነገር ውስጥ በማስገባት ያስረዷቸው።
- ✓ ገለጻ ሲያደርጉ የተለያዩ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች ያገናዘበ አቀራረብ ማድረግዎን አይዘንጉ።
- ✓ ገለጻውን ከጨረሱ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ሁለት ተግባራት በደብተራቸው በመጻፍ እንዲሰሩ ያድርጓቸው።
- ✓ ተግባራቱን ከመስራታቸው በፊት በሁለቱም ተግባራት መጀመሪያ የቀረቡትን ምሳሌዎች ያብራሩላቸው።

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የቀረቡት ጥያቄዎች ከዓረፍተነገር ውስጥ ተውሳከ ግሶቹን ለይተው እንዲያወጡ የሚጠይቅ ሲሆን እንዴት አድርገው ማውጣት እንደሚጠበቅባቸው በተሰጠው ምሳሌ አስደግፈው ያብራሩላቸው።
- ✓ ከሰጡት ማብራሪያ በመቀጠል ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ በመጻፍ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው።
- ✓ ተማሪዎቹ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን ተቀብለው እርማት ይስጧቸው።

ተግባር 2፦

- ✓ በዚህ ተግባር ልዩ ልዩ ተውሳከ ግሶች የተሰጡ ሲሆን ተውሳከ ግሶቹን ተጠቅመው ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ተጠይቀዋል፡፡

ይህንንም እንዴት መተግበር እንዳለባቸው በምሳሌው አስደግፈው ያብራሩላቸው፡፡

- ✓ አብራርተው ከጨረሱ በኂላ ጥያቄዎቹን በጽሑፍ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን ከሰሩ በኂላ የመልስ እርማት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የተለያዩ ተውሳከ ግሶችን የሚያሳዩ ፍላሽ ካርዶች

ምዘና፦

- ✓ ተውሳከ ግሶችን ሲለዩና በዓረፍተ ነገር ሲጠቀሙ መከታተል፡፡

# አማርኛ (፰) ክፍል

# ምዕራፍ አራት
# የትራፊክ ደህንነት

(18 ክፊለ ጊዜ)

የምዕራፉ ዓላማዎች:- ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:-

- ምልልስ አዳምጠው አስፈላጊነቱን ይገልጻሉ፡፡
- የተለያዩ የማዳመጥ ስልቶችን ተጠቅመው ለተነበበላቸው ጽሑፍ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡
- ማህበራዊ አገላለጾችን ይገልጻሉ፡፡
- አንቀጽ አንብበው ጭብጡንና አስፈላጊነቱን ይገልጻሉ፡፡

ይዘት:-

- ✓ ለክፍል ደረጃው የተቀረጹ ድምጾችን ማሰማት
- ✓ አንብቦ ዋና መልእክቱን መለየት
- ✓ አዳምጦ ከጽሑፉ የወጡ ጥያቄዎችን መመለስ
- ✓ ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ መስጠት
- ✓ በሁኔታ ተውሳከ ግስ ዓረፍነገር መመስረት
- ✓ ገላጭ አንቀጽ መጻፍ

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

የትምህርቱ አቀራረብ፡-

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ከተቀረጹ ድምጾች ያዳመጡትን ጽሑፍ ሀሳብ መግለጽን ይማራሉ፡፡ ይህንን ለማስተማር የሚረዳ ምንባብ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡ ከትምህርቱ ክፍለ ጊዜ በፊት ምንባቡን በመቅረጽ ለማስተማሪያነት ዝግጁ ያድርጉት፡፡ በመቀጠልም የሚከተለውን ሒደት ተከትለው ትምህርቱን ያቅርቡት፡፡

### ቅድመ ማዳመጥ

- ✓ በድምጽ ቀርጸው ያዘጋጁትን ምንባብ ለተማሪዎች ከማስደመጥዎ በፊት በተማሪው መጽሐፍ የቀረቡትን ሁለት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎችን ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን መልስ በመቀበል የሚከፍቱላቸውን የተቀረጸ ምንባብ ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ ያሳስቧቸው፡፡

### የማዳመጥ ሒደት

- ✓ ቀርጸው ያዘጋጁትን ምንባብ ለሁሉም ተማሪዎች ሊሰማቸው በሚችል ቦታ አድርገው ይክፈቱላቸው፡፡ መምህር መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ በምልክት ቋንቋ ታግዘው ምንባቡን እንዲከታተሉ እገዛ ይደረግላው
- ✓ የተከፈተላቸውን ምንባብ እያዳመጡ እያሉ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች ላይ ሲደርሱ የሚያዳምጡትን በማቆም ተማሪዎችን ይጠይቋቸው ፤ ምላሻቸውንም ከተቀበሉ በኋላም እንደገና ይክፈቱላቸው፡፡

### አዳምጦ መረዳት

#### ዋናው መኖር

መነን፣ እንድሪስ፣ ሰዓዳና አለማየሁ አርብ ከትምህርት ቤት ሲለቀቁ፣ ቅዳሜ ዕለት በእነመነን ቤት ተገናኝተው ለማጥናት ቀጠሮ ይዘው ተለያዩ፡፡ ቅዳሜ ጧት መነን፣ መቀመጫዎችን ቤታቸው በረንዳ ላይ አዘጋጅታ፣ ጓደኞቿን መጠባበቅ ጀመረች፡፡ እንድሪስና አለማየሁ በቀጠሯቸው ሠዓት መጡ፡፡

መነን ጓደኞቿን በፍቅር ተቀብላ አብራቸው ተቀመጠች፡፡ ይሁን እንጂ ሰዓዳ ስላልመጣች ጥናታቸውን መጀመር አልቻሉምና እየተጨዋወቱ ይጠብቋት ጀመር፡፡ ሰዓዳ ከጥናት መጀመሪያ ሰዓታቸው ሀምሳ ደቂቃ ዘግይታ ፣ ጣደፍ ጣደፍ እያለች መጣች፡፡ ጓደኞቿም በሞቀ ሠላምታ ተቀበሏት፡፡ ሰዓዳ ግን ለጓደኞቿ የሞቀ ሠላምታ አፀፋውን መስጠትም ሆነ መረጋጋት አልቻለችም፤ ክፉኛ ተረብሻለች፡፡ ጓደኞቿ ምን እንደሆነች እንድትነግራቸው እየተቀባበሉ በጥያቄ አጣደፏት፡፡ ሰዓዳ ግን ምንም ነገር ተረጋግታ ማሰብም ሆነ መናገር አልቻለችም ነበር፡፡ ሁኔታዋ ስላሳሰባት፣ መነን ሰዓዳን ወደመኝታ ክፍሏ አስገብታ፣ አልጋው ላይ አረፍ እንድትል አደረገቻትና ወደ ጓደኞቿ ተመለሰች፡፡ ሠዓዳ ራሷን አረጋግታ እስክትመለስ፣ ጓደኛሞቹ ስለተለያዩ ጉዳዮች መጨዋወታቸውን ቀጠሉ፡፡

**ሰዓዳ ከጥናት መጀመሪያ ጊዜያቸው ምን ያህል ደቂቃ ዘግይታ መጣች?**

**ሰዓዳ መረጋጋት ያቃታት ምን ገጥሟት ይመስላችኋል?ሰ**

ከሀያ ደቂቃ በኋላ ሰዓዳ የመነን እናት በጆግ ውሀ እንዲሰጧት ጠይቃ፣ ፊቷን ተጣጥባ፣ ወደ በረንዳው ስትመጣ፣ ጓደኞቿ እንደገና በደስታ ተቀበሏት፡፡ ሰዓዳም በተቻላት መጠን ፈገግ ለማለት ሞከረች፡፡ የጥናት ቀጠሮውን አክብራ በሠዓቱ ባለመገኘቷ ጓደኞቿን ይቅርታ ጠየቀች፡፡ ቀጥሎም ምን ሆና እንዳረፈደችና እንዲህ የረበሻት ነገር ምን እንደሆነ እንድታስረዳቸው፣ ጓደኞቿ ጠየቋት፡፡

ሠዓዳም ከቤቷ በታክሲ ስትመጣ የትራፊክ አደጋ አጋጥሟት እንደነበረ፣ ለጓደኞቿ ስትነግራቸው፣ ሁሉም በድንጋጤ ክው ብለው ያዳምጧት ነበር፡፡ እሷ ተሳፍራበት የነበረው ታክሲ ባልተፈቀደ ቦታ ላይ፣ መንገድ ሲያቋርጥ የነበረን አንድ መንገደኛ ላለመግጨት ወደቀኝ ሲታጠፍ፣ የመኪናው የፊት ቀኝ ጎማ የውሀ መውረጃ ቦይ ውስጥ መግባቱን ነገረቻቸው፡፡ ታክሲው ውስጥ ከነበሩት ሰዎች ማንም የተጎዳ እንዳልነበረም ገለፀችላቸው፡፡

ጓደኞቿ በፍርሀት ውስጥ ሆነው፣ በጉጉት ያደምጧት ስለነበር፣ ትረካዋን ቀጠለች፡፡ ባልተፈቀደ ቦታ ላይ መንገዱን ሲያቋርጥ የነበረው እግረኛ፣ እሷ የነበረችበት ታክሲ እንዳይገጨው፣ ሮጦ ፣ መንገዱን ሊያቋርጥ ሲል፣ ከጎን ደርቦ ሲመጣ በነበረ ቪትዝ መኪና እንደተገጨ ስትነግራቸው፣ ሁሉም በድንጋጤ ውስጥ ተውጠው ነበር፡፡ ‹‹የቪትዙ ሾፌር ረጋ ብሎ ሲያሽከረክር ስለነበርና ቶሎ ፍሬን በመያዙ፣ መንገደኛው የከፋ ጉዳት አልደረሰበትም፡፡ ይሁን እንጂ ተገጭቶ ሲወድቅ፣ ግንባሩ ላይ በደረሰበት ቁስለት የተነሳ ፊቱ ደም በደም ሆኖ ነበር፡፡ወዲያው መኪና ተፈልጎ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ፡፡ እኔም ሌላ ታክሲ ለመያዝ ስለፈራሁ፣ መንደር ለመንደር ፣ በእግሬ እያቆራረጥኩ መጣሁ…›› እያለች በዝርዝር ነገረቻቸው፡፡

በመትረፏና በሠላም በመምጣቷ እፎይታ ስለተሰማቸው፣ ፍቅራቸውንና ደስታቸውን ገለፁላት፡፡ በመቀጠልም፤ መነን ፈጠን ብላ ወደ ቤት በመግባት ለጓደኞቿ መስተንግዶ በፔርሙዝ ያስቀመጠችውን ሻይና በዳንቴል በተሸፈነ ትሪ ላይ የነበረውን ዳቦ ይዛ መጣች፡፡ተመልሳ ሄዳ የሻይ ብርጭቆዎችን በማምጣት፣ ጓደኞቿንና ራሷን አስተናገደች፡፡ ሁሉም ከድንጋጤያቸው ወጥተው፣ በተረጋጋ መንፈስ መጫወታቸውን ቀጠሉ፡፡ ይሁን እንጂ ጨዋታቸው ሁሉ ከትራፊክ ደህንነት ጋር የተያያዘ ነበር፡፡

አለማየሁ‹‹በከተማችን የትራፊክ አደጋ በጣም ጨምሯል፤ሬዲዮውም ሆነ ቴሌቪዥኑ የሚያወራው ስለዚህ ጉዳይ ነው፡፡ ሰዎችም በየቦታው እየተነጋገሩበት ነው›› አለ፡፡

ሰዓዳም ከአለማየሁ ቀበል አድርጋ በየመገናኛ ብዙኃኑ ና በየቤቱ መወራቱ ብቻውን ምንም ለውጥ እንደማያመጣና ሰዎች የአመለካት ለውጥ በማምጣት፣ ስለትራፊክ ደህንነት የሚሰጠውን ትምህርት በማስተዋል መተግበር እንዳለባቸው አሳሰበች፡፡ አለማየሁና ሰዓዳ ሲናገሩ፣ በጥሞና እያዳመጠ ተራውን ሲጠብቅ የነበረው እንድሪስ፣ የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ፣ መንገዶችን ማስፋት እንደሚገባና አሁን ባለው ሁኔታ የመኪናዎች ብዛትና የመንገዶች ሁኔታ አለመመጣጠኑን አስረዳ፡፡

ጉድ ጉድ!እያለች፣ የጓደኞቿን ንግግር ስታዳምጥ የነበረችው መነን፣ ዋናው እህታችን በሠላም መምጣቷ መሆኑን ገልፃ፣ ስለትራፊክ አደጋ ማውራታቸውን አቁመው ወደ ጥናት መግባት እንደሚገባ አሳሰበች፡፡ አለማየሁ ግን ለማጥናትም፣ ተምሮ ያሰቡት ደረጃ ለመድረስም፣ በህይወት መኖር እንደሚያስፈልግ ገልጾ፣ ‹‹የዛሬው ጥናት ቀርቶ በተጀመረው የትራፊክ ደህንነት ጉዳይ ላይ ውይይቱ ቢቀጥል ይሻላል›› የሚል ሀሳብ አቀረበ፡፡ በዚህ ሀሳብ ሁሉም ተስማምተው ውይይታቸውን ቀጠሉ፡፡

በውይይታቸው መጨረሻም የጋራ ስምምነት ላይ ደረሱ፡፡ በዚህም መሰረት ሁሉም ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ቃል ተገባቡ፡፡ ቃላቸውንም ከቤተሰቦቻቸው አባላት በመጀመር፣ ወደ ትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ከዚያም ወደ ማኅበረሰቡ እንደሚያስፋፉት ወስነው ስራቸውን ጀመሩ፡፡

- ✓ ምንባቡን አዳምጠው ከጨረሱ በኋላ በአዳምጦ መረዳት ስር የቀረቡትን ሁለት ተግባራት ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር አራት የምርጫ ጥያቄዎች ሲኖሩ፤ ጥያቄዎቹ በቀጥታ ካዳመጡት ምንባብ የወጡ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹን ምንባቡ በያዘው ሀሳብ መሰረት ትክክለኛውን መልስ እየመረጡ በቃል እንዲመልሱ ያድረጓቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎቹን ምላሽ ተከትለው ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ ይግለጹላቸው፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር አራት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን፣ መልሶቻቸው በቀጥታ ከምንባቡ የማይገኙና አንድምታዊ ምላሽ የሚፈልጉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡
- ✓ ለጥያቄዎቹ መልስ ለመስጠት እንደ ክፍሉ ነባራዊ ሁኔታ ከ 3 እስከ 5 ተማሪዎችን የያዙ ቡድኖች በመመስረት እንዲወያዩ ያድርጉ፤ ለጥያቄዎቹ መልስ ሲሰጡም እያበረታቱ ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ መልሶቻቸውን አቅርበው ከጨረሱ በኋላ የማጠቃለያ ሀሳብ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ በድምጽ የተቀዳ ምንባብና ማጫወቻ መሳሪያ

ምዘና

- ✓ አዳምጠው የተገነዘቡትን መመለሳቸውን ማረጋገጥ

የተመረጠ ተግባር መልስ

ተግባር 1፡-

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ በቃል መልሱ፡፡

1. ሀ　　2. መ　　3. ሐ　　4. ለ

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### የትምህርቱ አቀራረብ

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ምንባብን አንብበው መልእክቱን መግለጽን ይማራሉ፡፡ ለትምህርቱ ማስተማሪያነትም በመማሪያ መጽሐፉ ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም የመማር ማስተማር ሒደቱን እንደሚከተለው ያከናውኑ፡፡

### ቅድመ ንባብ

- ✓ በመጀመሪያ ምንባቡን ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት ሁለቱን የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ለተማሪዎቹ ያቅርቡላቸው፡፡
- ✓ የመጀመሪያው የቅድመ ንባብ ጥያቄ ተማሪዎች የትራፊክ አደጋ ሲከሰት አጋጥሟቸው እንደሆነ የሚጠይቅ ሲሆን፣ ለዚህ ጥያቄ ተማሪዎች በየተራ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በሁለተኛው ቅድመ ንባብ ጥያቄ ተማሪዎች ስዕሉንና ርዕሱን በመመልከት ምንባቡ የሚያነሳውን ጉዳይ የሚጠይቅ ሲሆን ለጥያቄው የሚሰጧቸውን መልሶች ተቀበሏቸው፤ የሚመልሱትን መልስም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ያስፍሩ፡፡
- ✓ በቅድመ ምንባብ ጥያቄዎቹ ተማሪዎች ለማንበብ ከተዘጋጁ በኋላ ተማሪዎች ምንባቡን በአርምሞ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

### የንባብ ሒደት

- ✓ ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ወቅት ቃላትን ሳይገድፉ፣ በተገቢው አነባበብና ፍጥነት ማንበብ እንደሚጠበቅባቸው ያሳስቧቸው፡፡
- ✓ በሰጧቸው መመሪያ መሰረት እያነበቡ መሆናቸውን ይከታተሏቸው፡

### አንብቦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ የድህረ ምንባብ ተግባራትን እንዲሰሩ ያደርጓቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች በምንባቡ ሀሳብ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን መልስ ከተቀበሉ በኋላ የማስተካከያ እርምት ይሰጧቸው፡፡

ተግባር 2፡

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ሶስት ጥያቄዎች አሉ፡፡
- ✓ በተራ ቁጥር ‹ሀ› እና ‹ለ› የቀረቡት ጥያቄዎች ከምንባቡ ባገኙት ግንዛቤ መሰረት የራሳቸውን ልምድ ጨምረው የሚገልጹበት ነው፡፡
- ✓ እንዲሁም በ‹ሐ› የቀረበው ጥያቄ አጠቃላዩን የምንባቡን ሀሳብ በጽሑፍ እንዲገልጹ የሚጠይቅ ነው፡፡
- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች የተማሪዎችን ምላሽ እያበረታቱ ይቀበሏቸው፤ መልሳቸውንም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ያስፍሩ እና በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ ከመለሷቸው መልሶች ጋር እንዲያመሳክሩ እድሉን ያመቻቹላቸው፡፡

- ✓ በመጨረሻም ለተማሪዎቹ መልስ እርማት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የትራፊክ ደህንነትን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ (ቻርት)

ምዘና

- ✓ ተማሪዎች የምንባብ ታሪክን መሰረት ያደረጉ ተግባራትን እንዲመልሱ ማድረግ

የተመረጡ ተግባራት መልሶች

1. ሀሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. ሀሰት

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች መዝገበ ቃላዊ ፍቺን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለመስጠት የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ይከተሉ፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ከምንባቡ የወጡ ቃላት ቀርበዋል፡፡ ቃላቱ ያላቸውን መዝገበ ቃላዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ምንም እንኳን ቃላቱ በምንባቡ ላይ ያሉ ቢሆኑም፣ ፍቺዎቻቸው ግን ከምንባቡ ጋር ያልተገናኘ ሊሆን ይችላሉ፡፡
- ✓ በመሆኑም ተማሪዎቹ በዓውዱ መሰረት ሳይሆን ከመዝገበ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ መልስ ከሰጡ በኋላ የማስተካከያ ምላሽ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍችዎችን የሚያሳይ ፍላሽ ካርድ

ምዘና

- ✓ ተማሪዎች የአዳዲስ ቃላት እውቀት ክምችት ማዳበራቸውን መከታተል፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

የትምህርቱ አቀራረብ

በጽሕፈት ክፍል ገላጭ አንቀጽ መጻፍን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት በሚገባ በማስተማር ተማሪዎች ገላጭ አንቀጽ መጻፍን እንዲለማመዱ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት በመከተል ትምህርቱን ያቅርቡት፡፡

- ✓ በመጀመሪያ በምዕራፍ ሶስት ስለገላጭ የአንቀፅ ማስፋፊያ ስልት የተማሩትን ይከልሱላቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በዚህ ክፍል የቀረቡትን ሁለት ተግባራት ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡ ዓረፍተ ነገሮቹ በቅደም ተከተላቸው ሲቀርቡ ገላጭ አንቀጽ ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም ቅደም ተከተላቸውን አስተካክለው እንደገና በገላጭ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልትን በመጠቀም እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ ተማሪዎቹ ተግባሩን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ የማስተካከያ ምላሽና ማብራሪያ ይስጧቸው።

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ደግሞ የቢጋር ሰንጠረዥ ቀርቦላቸዋል። የቀረበውን ቢጋር በማበልጸግ ገላጭ አንቀጽ እንዲጽፉ ያድርጓቸው።
- ✓ ተማሪዎቹ የጻፉትን አንቀጽ በመመልከት ግብረ መልስ ይስጧቸውና ትምህርቱን ያጠቃልሉት።

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያዎች

- ✓ ገላጭ አንቀጽ የሚያስጽፍ ስዕላዊ የሰንጠረዥ ቢጋር

ምዘና

- ✓ ገላጭ አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

የትምህርቱ አቀራረብ

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የሁኔታ ተውሳከ ግስን ይማራሉ። ትምህርቱን በሚገባ ለመስጠት የሚከተለውን ሒደት ተከትለው ያቅርቡት።

- ✓ በመጀመሪያ በምዕራፍ ሶስት ስለተውሳከ ግስ የተማሩትን አስታውሰው እንዲገልጹ ያድርጓቸው።
- ✓ እርስዎም የተማሪዎቹን ምላሽ ተከትለው አጭር ክለሳ ይስጧቸው።
- ✓ በመቀጠል የሁኔታ ተውሳከ ግን በማስከተል በመማሪያ መጽሐፉ የሁኔታ ተውሳከ ግስን በማስመልከት የቀረበውን ምንባብ እንዲጽፉ ያድርጓቸው።

- ✓ ማስታዎሻውን ከጻፉ በኋላ በመጽሐፉ የቀረቡትን ምሳሌዎችና ሌሎችንም ምሳሌዎች በማምጣት ርእሰ ጉዳዩን ያብራሩላቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ተግባራት ያሰሯቸው፡፡

በተግባር አንድ የተለያዩ ዓረፍተነገሮች ቀርበዋል፡፡ በዓረፍተ ነገሮቹም የሁኔታ ተውሳከ ግሶች ቀርበዋል፡፡

- ✓ ከየዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የሁኔታ ተውሳከ ግሶች ለይተው እንዲያወጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ የማስተካከያ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በተግባር ሁለት የተለያዩ የሁኔታ ተውሳከ ግሶችን በማምጣት በተውሳከ ግሶቹ ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ተማሪዎች የመሰረቷቸውን ተውሳከ ግሶች በትክክለኛው አጠቃቀም በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀማቸውን በማረጋገጥና እርማት በመስጠት ትህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የሁኔታ ተውሳከ ግሶችን የሚያሳይ ቻርት

ምዘና

- ✓ የሁኔታ ተውሳከ ግሶችን በመጠቀም ዓፍተነገር ሲመሰርቱ መከታተል፡፡

የተመረጡ ተግባራት መልሶች

ተግባር 1፦

ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ሀረጎች በ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት የሚስማሟቸውን በመምረጥ ዓረፍተነገሮቹን አሟሏቸው፡፡

1. ሠ 2. ሐ 3. ለ 4. ሀ 5. መ

ተግባር 3፦

ከላይ የቀረበውን ማስታዎሻና ምሳሌዎች በሚገባ በማጤን በሚከተሉት ዓረፍነገሮች ውስጥ የሚገኙትን የሁኔታ ተውሳከ ግሶች አውጥታችሁ የሁኔታ ተውሳከ ግስ ያስባላቸውን ምንያት አብራርታችሁ በመጻፍ መልሱ፡፡

ሀ. ተንደርድራ ሐ. እየሮጠ ሠ. አምርሮ

ለ. በድንገት መ. በቁጣ

# አማርኛ

(፰) ክፍል

# ምዕራፍ አምስት
# የአካባቢ ጥበቃ

(18 ክፍለ ጊዜ)

የምዕራፉ ዓማዎች፡-

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ የቀደመ እውቀታቸውን ከአሁኑ ጋር ያዛምዳሉ

መዝገበ ቃላትን ተጠቅመው የቃላትን ድምጽ አሰዳደር፣ ትርጉማቸውንና ግንኙነታቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

- ✓ በጽሑፍ ውስጥ የቀለም መለያ ምልክቶችን ይጠቀማሉ፡፡

ይዘት፡-

- ✓ ያዳመጡትን በቃል መተረክ
- ✓ ቃላትን በመነጠልና በማጣመር ማንበብ
- ✓ ከአንቀጽ ውስጥ ኃይለ ቃሉን ማውጣት
- ✓ የነጠላና የብዙ ቁጥር ስሞችን በመለየት በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### ብርቱዋ እናት

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

ቀጥሎ ‹‹ብርቱዋ እናት›› በሚል ርእስ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማስተማር ምንባብ ቀርቧል፡፡ ትምህርቱን በሚከተሉት ቅደም ተከተሎችና አቀራረቦች ያከናውኑ፡፡

### ቅድመ ማዳመጥ

- ✓ ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት በቅድመ ማዳመጥ ተግባር ስር ያሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲሰሯቸው ያድርጉ፡፡

ተግባር፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የሚነበብላቸው ምንባብ ስለምን እንደሚያወሳ ቀድመው እንዲገምቱ የሚያደርጓቸውን ሁለት ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹም ስዕሉን በመመልከት የምንባቡን ሀሳብ እንዲገምቱ እና በአካባቢያቸው ግቢያቸውን በእጽዋት የሚያስውቡ ሰዎች እንዳሉ እንዲገልጹ የሚጠይቁ ናቸው
- ✓ ለጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ የሰጧቸውን ሀሳቦች ከተቀበሉ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ የማዳመጥ ሒደት የቀረበውን ሰንጠረዥ በደብተራቸው እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ ተማሪዎቹ መልስ ከሰጡ በኋላ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አይጠበቅብዎትም፡፡
- ✓ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ የሚነበብላቸውን ምንባብ በጥሞና እንዲያዳምጡ ያሳስቧቸው፡፡

## የማዳመጥ ሒደት

ተግባር፡-

- ✓ ተማሪዎቹ ለማዳመጥ ዝግጁ ከሆኑ በኋላ ረጋ ባለና ሁሉም ተማሪዎች ሊያደምጡዎት በሚችሉት ድምጸት ያንብቡላቸው፤ አስፈላጊ ከሆነም አንድ ጊዜ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ ምንባቡን ሲያነቡ መስማት የተሳናቸው ወይም የመስማት ውስንነት ያለባቸውን ተማሪዎች ባገናዘበ መንገድ ያቅርቡት፡፡
- ✓ በምንባቡ መሀል ላይ ያሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ በትክክል እያዳመጡ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ✓ በተጨማሪም ማንበብ ከመጀመርዎት በፊት እንዲጽፉ ባዘዟቸው ሰንጠረዥ ውስጥ ላሉ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ እየተከታተሉዎት መሆናቸውን ካረጋገጡና ለቃላቱ ፍቺ እንዲሰጡ ካደረጓቸው በኋላ ምንባቡን ካቋረጡበት ቦታ ይቀጥሉ፡፡

## አዳምጦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበውላቸው እንደጨረሱ የአዳምጦ መረዳት ተግባራትን እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የቀረቡት ጥያቄዎች በቃል የሚመለሱ ሲሆኑ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ያለገደብ እንዲገልጹ የሚጠይቁ ናቸው፡፡
- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ መልስ ሲሰጡ በቃል ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹ የአንድምታዊ ጥቄዎች በመሆናቸው ከሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ መልስ ላይሰጥ ይችላል፡፡ በመሆኑም መልሶቻቸውን ሲቀበሉ ንግግራቸውን እንዲቀጥሉ ከማበረታታት ውጭ መልሳቸው ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን እንዳይገልጹ፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ምላሽ ተቀብለው ከጨረሱ በኋላ ማበረታቻ አስተያየት በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ካዳመጡት ምንባብ በቀጥታ የሚመለሱ ናቸው፡፡
- ✓ ምንባቡን መሰረት አድርገው ለጥያቄዎቹ በጽሑፍ መልስ እንዲሰጡ ያድጓቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎቹን ምላሽ ከተቀበሉ በኋላ የማስተካከያ ምላሽ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም የማጠቃለያ አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

## ብርቱዋ እናት

ወይዘሮ አስካለ የሚኖሩት በዛፎች በታጠረና መንገድ ዳር በሚገኝ ቆርቆሮ ቤት ውስጥ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት፣ ከቤታቸው ፊት ለፊት ባለው የአትክልት ቦታቸው ውስጥ ደፋ ቀና እያሉ ነው፡፡ በመንገድ የሚያልፉ ሰዎች ሠላምታ ሲያቀርቡላቸው እንኳን የሠላምታውን አፀፋ የሚመልሱት፣ ማንንም ቀና ብለው ሳያዩ ነው፡፡

እሳቸው በጥረታቸው ከራሳቸው አልፈው ለሌላው መትረፍ የቻሉ ብርቱ ሴት ናቸው፡፡ ወይዘሮ አስካለ ፣ ጎመን ፣ ቃሪያ፣ ቲማቲምም ሆነ ጤናዳም ጉልት ሄደው ሲገዙ አየኋቸው የሚል ሰው አይገኝም፡፡ የሚያስፈልጓቸውን አትክልት በግቢያቸው ውስጥ ባለው የአትክልት ቦታ ያመርታሉ፡፡ አልፎ አልፎም ለጎረቤቶቻቸው በመሸጥ ኑሯቸውን ይደጉማሉ፡፡

በዚህም የተነሳ፣ ወይዘሮ አስካለን የሠፈሩ ሰው የሚጠራቸው ‹‹ብርቱዋ እናት›› እያለ ነው፡፡ ይህንን መጠሪያ ያገኙት፣ ከሚሰሩበት የመንግስት መስሪያ ቤት በጡረታ ተገልለው፣ ግቢያቸው ውስጥ በአረንጓዴ ልማት ተሰማርተው ባሳዩት ለውጥ ነው፡፡

ወይዘሮ አስካለ፣ ለዕለት ፍጆታ ከሚያውሉት አትክልት በተጨማሪ ልዩ ልዩ የፍራፍሬ ዛፎችንም ይተክላሉ፡፡ የግቢያቸው ዙሪያ አጥርም የተዋቀረው በነዚሁ ዛፎች ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፣ ዛፎቹ ፍሬ ለማፍራት ገና ያልደረሱ መሆናቸውን የሠፈሩ ሠዎች እያዩ ‹‹ወይዘሮ አስካለ፣ እነዚህን የፍራፍሬ ዛፎች የሚተክሉት ለምንድን ነው? ፍሬ ለማፍራትኮ ብዙ ዓመት ይፈልጋሉ›› ይሏቸዋል፡፡ እሳቸውም፣ ‹‹ፈጣሪ ዕድሜውን ካደለኝ፣ ከፍሬያቸው እቋደስ ይሆናል፡፡ ካልሆነም፣ ዕድሜዬ እስኪፈቅድ ድረስ፣ በውበታቸው እየተደሰትኩ እኖራለሁ፡፡ ከዚህም በላይ እኔ ባልፍ እንኳን፣ ልጆቼና የልጅ ልጆቼ ከሠፈሩ ሠው ጋር የዛፎቹን ፍሬ እንደሚቋደሷቸው እያሰብኩ የህሊና እርካታን አገኛለሁ›› በማለት ይመልሳሉ፡፡

ወይዘሮ አስካለ የሚያለሟቸውን ተክሎች ለራሳቸው ብቻ አስበው አለመሆኑ ምን አይነት አመለካከት እንዳላቸው ያመለክታል?

ወይዘሮ አስካለ ከሚሰሩት ስራ ምን ጥቅም የሚያገኙ ይመስላችኋል?

ወይዘሮ አስካለ፣ የሠፈሩ ሰው ሁሉ የእሳቸውን አርአያነት ተከትሎ በየግቢው እንዲያለማ፣ የልዩ ልዩ አትክልትና ፍራፍሬ ችግኞችን በነፃ ይሠጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ አብዛኛው ሰው ችግኞችን ቢወስድም፣ ተንከባክቦ ስለማያሳድጋቸው፣ በጣም ይቆጫሉ፡፡ ‹‹ችግኞች ልጆች ማለት ናቸው፤ ትኩረትና እንክብካቤን ይሻሉ፡፡ ልጆቻችንን በዕድላቸው ይደጉ፣ ብለን መተው እንደሌለብን ሁሉ፣ ችግኞችንም ተክለን ብቻ መተው የለብንም›› እያሉ በስሜት ይናገራሉ፡፡

የሠፈሩ ህፃናት አትክልት ለመግዛት ወደእሳቸው ቤት ሲመጡ፣ የአትክልት ቦታቸውንና በቤታቸው ዙሪያ የተተከሉትን ዛፎች ማስጎብኘት ያዘወትራሉ፡፡ ለዚህም ምክንያታቸው ህፃናት በልጅነታቸው ያዩትን ነገር ይዘው እንደሚያድጉ ስለሚያምኑ ነው፡፡ ስለሆነም የአበቦች፣ የአትክልትና የዛፎችን ፍቅር ይዘው እንዲያድጉ፣ መኮትኮት ያለባቸው ከዛሬ ጀምሮ ነው፡፡ ‹‹ብዙ ሰዎች ችግኝ ለመትከል የማይረባረቡት፣ ከተከሉም በኋላ የማይንከበከቡት፣ ከልጅነታቸው ጀምሮ የዕፅዋት ፍቅር እንዲያድርባቸው ሆነው ስላላደጉ ይሆናል›› የሚል አቋም አላቸው፡፡

አንዳንድ ሰዎች ወይዘሮ አስካለን በቤታቸው ዙሪያ ያሉትን ዛፎች ቆራርጠው፣ ቤቶችን በመስራት ቢያከራዩ የተሻለ ገቢ እንደሚያገኙ ይመክሯቸዋል፡፡ እሳቸው ግን፣ ‹‹ቤት መስራት እኔን ይጠቅመኝ ይሆናል፤ ዛፎችን ማልማት ግን በዓለም ላይ ያሉ ፍጥረቶችን በሙሉ ይጠቅማል›› በማለት ይመልሱላቸዋል፡፡

ምዘና፡-

- ✓ ያዳመጡትን ምንባብ በቃል ሲተርኩ መከታተል፡፡

የተመረጠ ተግባር መልስ

ተግባር 2፡-

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ለ 2. ሀ 3. ሐ 4. ሀ 5. መ

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

የትምህርቱ አቀራረብ፡-

መምህር!

በዚህ ክፍል ማንበብን ለማስተማር በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበ ‹‹ጓሳ መገራ ፓርክ›› የሚል ምንባብ ይገኛል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም ትምህርቱን እንደሚከተለው ያቅርቡ፡፡

### ቅድመ ንባብ

- ✓ ተማሪዎቹ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የሚሰሩት አንድ ተግባር ሲኖር ተግባሩን በቃል ያሰሯቸው፡፡

ተግባር ፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ሁለት ጥያቄዎች ሲኖሩ ምንባቡ የያዘውን ሀሳብ በማስመልከት ፍንጭ እንዲያገኙ የሚያደርጉ ጥያቄዎች ሲኖሩ በቃል መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ምላሽ ተከትለው ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አያስፈልግዎትም፡፡
- ✓ ምንባቡን ለማንበብ ዝግጁ ከሆኑ በኋላ በተናጠል ድምጽ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

## የንባብ ሒደት

- ✓ ተማሪዎች በተናጠል ድምጽ ሳያሰሙ እያነበቡ መሆናቸውን እየተዘዋወሩ ያረጋግጡ፡፡

## አንብቦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበው እንደጨረሱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን እንደየ መመሪያዎቻቸው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የቀረቡት ጥያቄዎች በቀጥታ ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ናቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን ተማሪዎቹ በደብተራቸው ላይ እንዲገለብጧቸውና መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ለጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ የሰጧቸውን መልሶች በመቀበልና የማስተካከያ ምላሾች በመስጠት ወደ ሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የቀረቡት አምስት ጥያቄዎች ደግሞ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ሀሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ የሚያዙ ናቸው፡፡
- ✓ የዚህ ተግባር የመጀመሪያው ጥያቄ ተማሪዎች በቢጋሩ ላይ የቀረቡትን ዋና ዋና ሀሳቦች እንዲገልጹ የሚጠይቁ ናቸው፡፡
- ✓ ለዚህም ምሳሌ ይሆን ዘንድ አንደኛው የቢጋሩ ክፍል መልስ ተቀምጦላቸዋል

- ✓ በዚህም መሰረት ቀሪዎቹን ሶስት የቢጋር ክፍሎች ተማሪዎቹ እንዲያሟሉ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ተማሪዎች የጻፏቸውን ጽሑፎች በመውሰድ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ቀሪዎቹ አራት ጥያቄዎች ደግሞ ቋንቋ ነክ ጥያቄዎች ሲሆኑ የጥያቄዎቹን ሀሳቦች መሰረት አድርገው መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡
- ✓ ጥያቄዎቹም የአንቀጽን ሀሳብ እንዲገልጹ፣ ምንባቡ ስንት አንቀጾች እንዳሉት እንዲገልጹ፣ በምንባቡ የቀረበ አንድ ዓረፍተነገር ምን ሀሳብ እንዳለው እንዲያስረዱ እና አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ እንዲገልጹ የሚጠይቁ ናቸው፡፡
- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች የሰጧቸውን መልሶች በመመልከት የጽሑፍ ግብረ መልስ ይሰጧቸው፡፡
- ✓ ግብረ መልስ ሰጥተው ከጨረሱ በኋላ አጠቃላይ የሆነ አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

ምዘና፡-

- ✓ የምንባቡን ሀሳብ ሲገልጹ መከታተል

የተመረጠ ተግባር መልስ

ተግባር 1፡- ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ለ 2. ሐ 3. ሀ 4. ሐ 5. ሀ 6. መ 7. መ

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን መነጠልና ማጣመርን እና ለቃላት ፍቺ መስጠትን ይማራሉ፡፡ ትምህርቱን በሚከተለው መንገድ ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበውን አጭር ማስታዎሻና ምሳሌዎች ተማሪዎች እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ✓ በመቀጠል በመጽሐፉ ካሉት ምሳሌዎች በተጨማሪ ሌሎች ቃላትንም በማምጣት ቃላትን እንዴት እንደሚነጥሉና እንደሚያጣምሩ ያስረዷቸው፡፡
- ✓ ትምህርቱን ካስረዱ በኋላ ተግባራቱን በጽሑፍ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በዚህ ክፍል ሶስት ተግባራት ሲኖሩ ተግባራቱ እንደሚያዟቸው ትእዛዞች ተማሪዎቹን ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የተነጣጠሉ ቃላትን እንዲያጣምሩ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን በደብተራቸው እንዲጽፉ ካደረጉ በኋላ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡

- ✓ መልሳቸውን ተከትለው እርማት ከሰጡ በኋላ ወደሚቀጥለው ተግባር ይቀጥሉ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በተግባር 2 ደግሞ የተጣመሩ ቃላትን እንዲነጣጠል የሚጠይቁ ጥያቄዎች ናቸው፡፡
- ✓ ሁለቱን ተግባራት ሰርተው ከጨረሱ በኋላ የተማሪዎችን መልሶች ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ስለመልሶቹ ከተማሪዎች ጋር በመነጋገርና እርማት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

ተግባር 3፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ከምንባቡ የወጡ ቃላት በሰንጠረዥ ቀርበዋል፤ ሰንጠረዡን በደብተራቸው እንዲገለብጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ቃላቱ በሰንጠረዡ አግድም የቀረቡ ሲሆን ፍቺዎቻቸው ደግሞ በቁልቁል ቀርበዋል፡፡
- ✓ በአግድም ለቀረቡት ቃላት እና ሐረጋት በቁልቁል ከቀረቡት ፍቺዎቻቸው የሚስማሟቸውን በመምረጥ እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሶቻቸውን ተራ በተራ እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ለመልሶቻቸው እርማትና ማጠቃለያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ፡-

- ✓ የተነጣጠሉ ፊደላትን የያዘ ፍላሽ ካርድ ወይም ባለሰንጠረዥ ቻርት

ምዘና፡-

- ✓ ቃላትን በሚገባ መነጠልና ማጣመራቸውን ማረጋገጥ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የአንቀጽን ኃይለ ቃል ከመዘርዝራዊ ዓረፍነገሮች መለየትን እና በተሰጣቸው ኂይለ ቃል አንቀጽ መጻፍን ይማራሉ፡፡ የትምህርቱ ዓላማ ይሳካ ዘንድ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሂደትና ቅደም ተከተል በመከተል ትምህርቱን ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ በምዕራፍ አንድ ስለአንቀጽ ኃይለ ቃል እና መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮች የተማሩትን በማስታወስ እንዲገልጹ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ምላሽ በመመርኮዝ ርዕሰ ጉዳዩን ይከልሱላቸው፡፡
- ✓ ትምህርቱን በሚገባ ለማስታወስ ይረዳቸው ዘንድ ከምንባቡ ውስጥ የተወሰኑ አንቀጾችን በማውጣት የአንቀጾቹን ኃይለቃልና መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮች አውጥተው ያሳይዋቸው፡፡
- ✓ ከዚህም በተጨማሪ እንደ ማገዣ ይረዳዎት ዘንድ ቀጥሎ የቀረበውን አንቀጽ በምሳሌነት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

<u>አንድን ታማሚ ከህመሙ ለመፈወስ ሁለት አይነት የህክምና መስጫ ዘዴዎችን ልንጠቀም እንችላለን፡፡</u> አንደኛው ባህላዊ ህክምና ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ ዘመናዊ ህክምናነው፡፡ ባህላዊ ህክምና የሚባለው ሰዎች በሕይወት ልምዳቸው ያዳበሩት ሀገር በቀልእውቀትን የያዘ እና የተለያዩ ተፈጥሯዊ ግብዐቶችን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ በአንጻሩደግሞ ዘመናዊ ህክምና መሰረቱ የባህል ህክምና ቢሆንም የመድኃኒቱ ይዘት በመጠን ተለክቶና ብዙ የማጣራት ሒደቶችን አልፎ ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡

- ✓ ከላይ በቀረበው አንቀጽ የተሰመረበት ዓረፍተነገር ኃይለ ቃል ሲሆን ቀሪዎቹ ዓረፍተነገሮች ደግሞ መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮች ናቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በመማሪያ መጽሐፉ ያሉትን ሁለት ተግባራት ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በተግባሩ ስር አንድ አንቀጽ የቀረበ ሲሆን ተማሪዎች የአንቀጹን ኃይለ ቃልና መዘርዝር እንዲለዩ የሚያዝ ነው፡፡
- ✓ ይህንን ተግባር ተማዎቹ እንዲሰሯቸው ካደረጉ በኋላ ምላሽ ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ መልስ ሲሰጡ ኃይለ ቃልና መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮች ያስባሏቸውን ምክንያት በዝርዝር እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ይህም ኃይለ ቃሉንና መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮችን በሚገባ ተረድተዋቸው እንዲያወጧቸው ያግዛቸዋል፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ የሰሩትን መልስ ተቀብለው ከጨረሱ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ሶስት መንደርደሪያ ዓረፍተነገሮች ቀርበዋል፡፡
- ✓ እነዚህን መንደርደሪያ ዓረፍተነገሮች በመጠቀም ወይም እርስዎ የሚሰጧቸውን ሌላ መንደርደሪያ ዓረፍተነገር በመጠቀም ለኃይለ ቃሉ መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮችን በመጨመር አንቀጽ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ አንቀጹን በሚጽፉበት ወቅት አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ አንቀጹን ጽፈው ከጨረሱ በኋላ ጽሑፎቻቸውን በመመልከት ተገቢ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም የማጠቃለያ ሀሳብ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የአንቀጽን ኃይለ ቃልና መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮች ለይቶ የሚያመለክት ቻርት ምዘና
- ✓ የአንቀጽን ኃይለ ቃልና መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮች መለየታቸውን ማረጋገጥ

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

የትምህርቱ አቀራረብ

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ነጠላ ቁጥር እና ብዙ ቁጥር ስሞችን ይማራሉ፡፡ የትምህርቱ ዓላማ ይሳካ ዘንድ በሚከተለው መንገድ ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ ቀደም ባሉት ክፍሎች የተማሯቸውን አስታውሰው ስለስም ምንነት የሚያውቁትን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎቹን ምላሽ በመንተራስ ምሳሌዎችን እያቀረቡ የስምን ምንነት አብራርተው ያስረዷቸው፡፡
- ✓ በመቀጠል በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኘውን አጭር ማስታዎሻና ምሳሌዎች በደብተራቸው እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ጽፈው ከጨረሱ በኋላ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን በተመለከተ በምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻና ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም የቀረቡትን ሁለት ተግባራት በሚያመችዎት መንገድ በክፍል ስራ ወይም በቤት ስራ መልክ ይስጧቸው፡፡

ተግባር 1፦

- ✓ በዚህ ተግባር የተለያዩ የብዙና የነጠላ ቁጥር ስሞችን የያዙ ዓረፍተነገሮች ይገኛሉ፡፡ ከዓረፍተነገሮቹ ውስጥ ተማሪዎቹ ስሞቹን ለይተው በማውጣት ነጠላ ወይም ብዙ ቁጥር መሆናቸውን እንዲገልጹ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን ለመስራት ምሳሌዎችን ያሳይዋቸውና ቀሪዎቹን እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ ስራዎቻቸውን ጥንድ ጥንድ ሆነው እርስ በእርሳቸው እንዲተራረሙ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር 2፦

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ልዩ ልዩ ስሞች ቀርበውላቸው ስሞቹ ነጠላ ወይም ብዙ መሆናውን እንዲለዩ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን በግላቸው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም መልሶቻውን ጥንድ ጥንድ በመሆን እርስ በእርሳቸው እንዲተራረሙ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በሁለቱም ተግባራት ተማሪዎች የተራረሙበትን ደብተር በመሰብሰብ ያመጡትን መሻሻል ይገምግሙ፡፡
- ✓ በመጨረሻም መልሶቹ ላይ ከተማሪዎች ጋር በጋራ በመወያየት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ ነጠላ ቁጥር እና ብዙ ቁጥር ስሞችን የያዘ የሰንጠረዥ ቻርት

ምዘና፡-

- ✓ ነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞችን መለየታቸውን መከታተል

# አማርኛ
(፰) ክፍል

# ምዕራፍ ስድስት
## ጻረ-አደንዛዥ እጾችና ንጥረ ነገሮች

(18 ክፊለ ጊዜ)

የምዕራፉ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ አዳምጠው አደንዛዥ እጽን እንዴት መዋጋት እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡
- ✓ ጽሑፉ ስለምን እንደሆነ ይገምታሉ፡፡
- ✓ ምልክቶችንና መግለጫዎችን በማንበብ የጽሑፉን መልእክት ይረዳሉ፡፡
- ✓ የሽግግር ቃላትን ይለያሉ፡፡
- ✓ ለቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡

ይዘት፡-

- ✓ ማዳመጥና የቃላት ድምጾችን መለየት፡፡
- ✓ የሚነበበው ጽሑፍ ስለምን እንደሆነ መገመት፡፡
- ✓ ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ መስጠት፡፡
- ✓ በአንቀጽ ውስጥ መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋትን መጠቀም፡፡
- ✓ ስምና ግስን ተጠቅሞ ዓረፍተነገር መመስረት፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### ትውልድን መታደግ

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ያዳመጡትን ጽሑፍ ሀሳብ መግለጽን ይማራሉ፡፡ ይህንን ለማስተማር የሚረዳ ምንባብ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡ ትምህርቱን ለማቅረብ የሚከተለውን ሒደት ይከተሉ፡፡

#### ቅድመ ማዳመጥ

- ✓ ምንባቡን ለተማሪዎች ከማንበብዎ በፊት በተማሪው መጽሐፍ የቀረቡትን ሁለት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ተማሪዎችን ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን መልስ ከተቀበሉ በኋላ በአዳምጦ መረዳት ተግባር አንድ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ቀድመው በደብተራቸው ላይ እንዲጽፏቸው ያድርጉ፡፡
- ✓ በመቀጠል ጥያቄዎቹን መሰረት በማድረግ ማስታዎሻ እየያዙ እንዲያዳምጡ ያድርጓቸው፡፡

#### የማዳመጥ ሒደት

ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ ለሁሉም ተማሪዎች ሊደመጥ በሚችል ሁኔታ ያንብቡላቸው፡፡ መምህር መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ በምልክት ቋንቋ ታግዘው (ሌሎች አማራጮችን ተጠቅመው) ምንባቡን እንዲከታተሉ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ለምሳሌበከንፈር የማንበብ ዘዴን እንዲጠቀሙ ከፊት ወንበር ላይ እንዲቀመጡ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ ምንባቡን በማንበብ ላይ እያሉ በመሀል የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፤ ምላሻቸውን ከተቀበሉ በኋላም እንደገና ምንባቡን ማንበብ ይቀጥሉ፡፡

#### አዳምጦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ በመማሪያ መጽሑፉ ላይ የቀረቡትን ተግባራት እንደሚከተለው አሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

✓ በዚህ ተግባር አምስት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን ሶስቱ (ሀ፣ ሐ፣ መ) ከምንባቡ በቀጥታ የሚመለሱ፣ ሁለቱ (ለ፣ ሠ) ደግሞ ከምንባቡ በቀጥታ የማይገኙና አፍልቆ መናገርን የሚያበረታቱ ናቸው፡፡

✓ በጥያቄዎቹ ባህርያት መሰረት ጥያቄዎቹን ያሰሯቸው፡፡

✓ በተራ ቁጥር ‹ሀ፣ ሐ እና መ› ለቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት አድርገው የሚመልሷቸውን መልሶች ይቀበሏቸው፡፡

✓ እንዲሁም በተራ ቁጥር ‹ለ፣ እና ሠ› የቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጡት ምንባብ ላይ በቀጥታ የማይገኙ ናቸው፡፡ ዓላማቸውም ሀሳባቸውን በንግግር እንዲገልጹ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ለእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች የሚሰጧቸው መልሶች የግል አመለካከታቸውንና ቀደም ሲል ያላቸውን መረጃ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

ተግባር 2፡-

✓ የዚህ ተግባር ጥያቄ በሰንጠረዥ የቀረበ ነው፡፡ በሰንጠረዡም የመንግስት፣ የትምህርት ቤቶችና የወላጆችን ሚና እንዲገልጹ ተጠይቀዋል፡፡

✓ ምንባቡን ከማዳመጣቸው በፊት ጥያቄዎቹን መመልከታቸውና ማስታዎሻ መያዛቸው ይህንን ጥያቄ ለመስራት ያግዛቸዋል፡፡

✓ በመሆኑም ተማሪዎቹ ምንባቡን መሰረት አድርገው ታዳጊዎችና ወጣቶች ከአደንዛዥ እጽ ሱሶች ነጻ ሆነው እንዲያድጉ መንግስት፣ ቤተሰብና ትምህርት ቤት ያላቸውን ሚና እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር 3፡-

✓ በዚህ ተግባር ስር አንድ ጥያቄ ሲኖር የጤናና የሰውነት ማጎልመሻ መምህራቸውን ጠይቀው እንዲሰሩ የሚጠይቅ ነው፡፡

- ✓ ጥያቄውን እንደሚያመችዎት በቡድን ወይም በግል፣ በቤት ስራ መልክ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ለጥያቄዎቹ መልስ ለመስጠትም አስፈላጊዎቹን መረጃዎች ከተገቢዎቹ አካላት እንዲሰበስቡ ያሳስቧቸው፡፡
- ✓ አዘጋጅተው የመስጠትን ጽሑፍ ለክፍል ጓደኞቻው እንዲያነቡ ወይም እንዲያስረዱ ዕድል ይስጧቸው፡፡
- ✓ ለስራዎቻቸው አስፈላጊውን ግብረ መልስ ከሰጧቸው በኋላ አጠቃላይ አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

## ትውልድን መታደግ

ወጣቶችና ታዳጊዎች የወደፊት ሀገር ተረካቢዎችና የወገን ተስፋዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ትውልድን የመፍጠር ና የመገንባት ስራ በዋነኝነት መሰራት ያለበት በታዳጊዎችና ወጣቶች ላይ ነው፡፡ ወጣቶችና ታዳጊዎች፣ በአካል፣ በአዕምሮና በሰብዕና በሚገባ ታንፀው እንዲያድጉ የሁሉም ርብርብ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ወጣቶችና ታዳጊዎች ለመጤ ልማዶችና አደንዛዥ ዕፆች እንዳይጋለጡ መንግስት፣ ትምህርት ቤቶችና ቤተሰብ የላቀ ድርሻ አላቸው፡፡

አደንዛዥ ዕፆች ለሱሰኝነት የሚዳርጉ አደገኛ ንጥረ ነገሮች ናቸው፡፡ ሱስ ወይም ሱሰኝነት በዋነኝነት አእምሮን ከሚጎዱ በሽታዎች መካከል ልንመድበው የምንችለው ሕመም ነው፡፡ አደንዛዥ ዕፆች ከጭንቀት፣ ከሥጋትና ከድብርት ለመላቀቅ ሲባል፣ እንዲሁም ደስታን ለማግኘት ሲባል፣ የሚወሰዱ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜም፣ ለሕመም ማስታገሻና የእንቅልፍ ችግርን ለማስወገድ ወይም ለንቃት፣ ለመዝናናት ሲባል ይወሰዳሉ፡፡ እነዚህ ዕፆች በአፍ፣ በአፍንጫ፣ በኪኒን፣ በመርፌ፣ በሚጠጣ መልክ፣ የሚወሰዱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ሱሰኝነት፣ ጫት፣ ሲጋራ፣ ሀሺሽ፣ ሺሻ፣ ሄሮይን የመሳሰለ ከሰውነት ጋር በፍጥነት የሚላመዱና ለጊዜው ሊያነቃቁ፣ ሊያስታግሱ፣ ሊያስደስቱ፣ ሊያስተኙ የሚችሉ ነገሮችን፣ ዕፆችን፣ መድኀኒቶችን በተደጋጋሚ በመውሰድ ወይም በማድረግ የሚመጣ ሕመም ነው ፡፡

ወጣቶችንና ታዳጊዎችን ከአደንዛዥ ዕፆችና መጤ ልማዶች ከመጠበቅ አኳያ የመንግስት ሚና ላቅ ያለ ነው፡፡ መንግስት ወጣቶችንና ታዳጊዎችን ከመጤ ባህሎችና አደንዛዥ ዕፆች ተጋላጭነት የሚጠብቅ ጠንከር ያለ ህግ ማውጣትና መተግበርይኖርበታል፡፡ በዚህም መሰረት፣ ትምህርት ቤቶች፣ የስፖርት ማዘውተሪያዎች፣ የወጣቶች መዝናኛዎችና የታዳጊዎች መጫወቻ ስፍራዎች ለአደንዛዥ ዕፆችና መጤ ልማዶች የማያጋልጡ እንዲሆኑ መስራት አለበት፡፡

በአደንዛዥ እጾች እና መጤ ባህሎች የበለጠ ተጠቂ የሆኑት አካላት የትኞቹ ናቸው?

ዜጎችን ከአደንዛዥ እጾችና መጤ ባህሎች ለመታደግ ምን ምን ተግባራት መከናወን አለባቸው? በማን?

ከመንግስት በተጨማሪ ወጣቶችና ተማሪዎች በግንዛቤ እጥረት ምክንያት ከማይወጡበት ችግር ውስጥ እንዳይገቡ ለመጠበቅና መልካም ስብዕና እንዲላበሱ ለማድረግ መምህራንና የትምህርት ቤት አስተዳደር አካላት ያለባቸው ኃላፊነት ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አደንዛዥ ዕጾችን መጠቀም ያለውን አስከፊ ጉዳት በተመለከተ ተማሪዎችን በማስተማር፣ በሱስ ከመያዛቸው አስቀድሞ የመከላከል ስራ መስራት አለባቸው፡፡ በተጨማሪም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ በሱስ የተያዙ ተማሪዎችን በመለየት  የሚያገግሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገርም ትምህርት ቤቶችና አካባቢያቸው፣ ለመጤ ልማዶችና አደንዛዥ ዕፆች  ከሚያጋልጡ ሁኔታዎች እንዲርቁ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የኅብረተሰብ መፍለቂያ የሆነው ቤተሰብ፣ ወጣቶችንና ታዳጊዎችን በአግባቡ ተንከባክቦና መልካም ሰብዕናን አላብሶ የማሳደግ መተኪያ የሌለው ድርሻ አለው፡፡ በተለይ ደግሞ ወጣቶችና ታዳጊዎችን ለመጤ ልማዶችና አደንዛዥ ዕፆች እንዳይጋለጡና ህይወታቸው እንዳይመሰቃቀል፣ የመከላከል ትልቁ ኃላፊነት የቤተሰብ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ማንኛውም የቤተሰብ አባል፣ ልጆችን በግልጽ ከመምከር በተጨማሪ አዋዋላቸውንና የባህሪ ለውጣቸውን በመከታተል ከስር ከስሩ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይገባዋል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ታዳጊዎችና ወጣቶች ውድ የሀገር ሀብቶች በመሆናቸው ልዩ ትኩረት፣ እንክብካቤና ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል፡፡ አካላዊና አዕምሯዊ ዕድገታቸው የተስተካከለ እንዲሆንና መልካም ሰብዕናን እንዲያዳብሩ የሁሉንም ድጋፍ ይሻሉ፡፡ በተለይም ደግሞ ከአደንዛዥ ዕፆችና መጤ ልማዶች ተጠብቀው ማደግ ስላለባቸው፣የሚመለከታቸው ሁሉ የየበኩላቸውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡

(ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር፤ በድረ ገጹ ላይ፣ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ያሰፈረውን ጽሑፍ መነሻ በማድረግ፣ የተቀነባበረ ምንባብ)

ምዘና

- ✓ አዳምጠው የተገነዘቡትን መግለፃቸውን ማረጋገጥ

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ምንባብን አንብበው የምንባቡን ሀሳብ መግለጽን ይማራሉ፡፡ ለትምህርቱ ማስተማሪያነትም በመማሪያ መጽሐፉ ‹‹ ሱስ ደህና ሰንብት ›› የሚል ርእስ ያለው ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም የመማር ማስተማር ሒደቱን እንደሚከተለው ያከናውኑ፡፡

## ቅድመ ንባብ

- ✓ በመጀመሪያ ምንባቡን ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት በቅድመ ንባብ ተግባር ውስጥ የቀረቡትን አራት ጥያቄዎች በሰሌዳው ላይ ይጻፉና ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ ወደ ምንባቡ እንዲንደረደሩና ቀድመው የምንባቡን ሀሳብ እንዲገምቱ የሚረዷቸው በመሆናቸው ከተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ላይጠበቅ ይችላል፡፡
- ✓ እነዚህን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ለጥያቄዎቹ የሚሰጧቸውን መልሶች ተቀበሏቸው፤ የሚመልሱትን መልስም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ያስፍሩ፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ለቅድመ ንባብ የሰጧቸውን ምላሾች ማስተካከልም ሆነ ድምዳሜ መስጠት አያስፈልግዎትም፤ ትክክል መሆን አለመሆናቸውን ምንባቡን ካነበቡ በኋላ በራሳቸው ጊዜ ስለሚያገኙት የእርስዎ እርማት አያስፈልጋቸውም፡፡
- ✓ በቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹ ተማሪዎች ለማንበብ ከተዘጋጁ በኋላ ምንባቡን በአርምሞ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

## የንባብ ሒደት

- ✓ ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ወቅት ቃላትን ሳይገድፉ፣ በተገቢው አነባበብና ፍጥነት ማንበብ እንደሚጠበቅባቸው ያሳስቧቸው፡፡
- ✓ በሰጧቸው መመሪያ መሰረት እያነበቡ መሆናቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፡

## አንብቦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ የድህረ ምንባብ ተግባራትን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በአንብቦ መረዳት ስር ሁለት ተግባራት የቀረቡ ሲሆን የመጀመሪያው ተግባር የምርጫ፣ ሁለተኛው ተግባር ደግሞ የአጭር መልስ መስጠት ጥያቄዎች ናቸው፤ እነዚህን ተግባራት እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር 7 የምርጫ ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን በቀጥታ ከምንባቡ ባገኙት ሀሳብ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዙትን ሆሄያት በመምረጥ የሚሰሩ ናቸው፡፡
- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች በታዘዙት መሰረት ትክክለኛውን መልስ እየመረጡ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ምላሻቸውንም ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን መልስ ከተቀበሉ በኋላ የማስተካከያ እርማት በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡

- ✓ በዚህ ተግባር ስር አራት ጥያቄዎች ይገኛሉ፤ የጥያቄዎቹ ትኩረት ትክክለኛ መልስ መስጠት ላይ ሳይሆን የምንባቡን መልእክት ተረድተው የቀደመ እውቀታቸው ጋር በማቀናጀት ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ማድረግ ነው፡፡
- ✓ በመሆኑም ለተማሪዎቹ ሰፋ ያለ ጊዜ ሰጥተዋቸው፣ ያለምንም ጣልቃ ገብነት እንዲናገሩ ቢያበረታቷቸው ይመረጣል፡፡
- ✓ በዚህም መሰረት በዚህ ተግባር ስር ከቀረቡት ስድስት ተግባራት ውስጥ ሁለቱን እዚያው በክፍል ውስጥ በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በተራ ቁጥር ‹ሀ› የቀረበው ጥያቄ ‹‹እንኳን ለዚህ አበቃህ›› የሚለው አገላለጽ የሚነገርባቸውን የተለያዩ ማህበራዊ ዓውዶች እንዲገልጹ ተጠይቀዋል፤ እንዲሁም በተራ ቁጥር ‹ለ› ባታሪኩ በንግግሩ በሀል ‹‹በዚህ አጋጣሚ›› ያለው የትኛውን አጋጣሚ ለመግለጽ እንደሆነ እንዲገልጹ ተጠይቀዋል፡፡

- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች የተለያዩ መልሶች በተማሪዎች ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ያሏቸውን ሀሳቦች እንዲገልጹ እያበረታቱ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሁለቱን ጥያቄዎች አሰርተው ከጨረሱ በኋላ የማጠቃለያ አስተያየት ሰጥተው፣ የሚቀጥሉትን አራት ጥያቄዎች ለማሰራት ቡድኖችን ያደራጁ፡፡
- ✓ እንደ መማሪያ ክፍሉ ነባራዊ ሁኔታ ከ3 እስከ 5 ተማሪዎች የተካተቱባቸው ቡድኖችን ያደራጁ፡፡
- ✓ በመቀጠልም ቀሪዎቹን ሁለት ጥያቄዎች ለየቡድኖቹ አከፋፍለው በቡድን ስራ መልክ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜም ቡድኖቹ በተወካዮቻቸው አማካኝነት ስራዎቻቸውን ለክፍል ጓኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ስራዎቻቸውን አቅርበው ከጨረሱ በኋላ የማጠቃለያ ሀሳብ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

ምዘና

ተማሪዎች የምንባብ ታሪክን መሰረት ያደረጉ ተግባራትን እንዲመልሱ ማድረግ

## የተመረጠ ተግባር መልስ

ተግባር 1

1. ለ  2. ሀ  3. መ  4. ለ  5. ለ  6. ሐ  7.ሐ

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ዓውዳዊ ፍቺን ይማራሉ። ትምህርቱን ከማቅረብዎ በፊት ለቃላት ዓውዳዊ ፍች የሚሰጥበትን መንገድ በምሳሌ አስደግፈው ያስረዷቸው። ይህንን ለማድረግም ቀደም ባሉት ምዕራፎች የተማሯቸውን ተመርኩዘው ይከልሱላቸው። ትምህርቱን ለማቅረብ በመማሪያ መጽሐፉ ሶስት ተግባራት ቀርበዋል። እነዚህን ተግባራት በማሰራት ዓላማውን ለማሳካት የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ይከተሉ።

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ከምንባቡ የወጡ አምስት ቃላት ቀርበዋል። ቃላቱ ያላቸውን ዓውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡም ታዝዘዋል።
- ✓ ለቃላቱ ዓውዳዊ ፍቺ ለመስጠት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን መልእክት ከምንባቡ ላይ መመልከት እንዳለባቸው ያስረዷቸው።
- ✓ ይህንን ግልጽ ለማድረግም በተግባሩ መጀመሪያ ላይ ያለውን ምሳሌ ያስረዷቸው።
- ✓ በምሳሌው የቀረበው ቃል ‹‹ልቡ ተነካ›› የሚል ሲሆን በምንባቡ ውስጥ ያለው ዓውዳዊ ፍቺ አዘነ የሚል እንደሆነ ያስረዷቸው፤ የቃሉ ቀጥተኛ ፍቺ ደግሞ ልቡን በሆነ ነገር መንካት (መዳሰስ)፣ መወጋት ጋር የተገናኘ እንደሚሆን ያሳስቧቸው።
- ✓ በምሳሌው መሰረት ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን በደብተራቸው በመጻፍ በግል እንዲሰሩ ያድርጓቸው።

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ከምንባቡ የወጡ አምስት ቃላት ቀርበዋል፤ ለቃላቱም ከምንባቡ ዓውድ ውጭ ያላቸውን ፍቺ እንዲሰጡ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ይህ የተደረገውም ተማሪዎቹ ቃላት በዓውድ ውስጥ እና ከዓውድ ውጭ ያላቸውን ፍቺ ለይተው እንዲረዱ ለማድረግ ነው፡፡
- ✓ በመሆኑም በምንባቡ ውስጥ ካላቸው ፍቺ ውጭ የሚኖራቸውን ፍቺ የተሰጣቸውን ምሳሌ መሰረት አድርገው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ መስራት ከመጀመራቸው በፊት የተሰጠውን ምሳሌ ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- ✓ በምሳሌው የተሰጠው ቃል ‹‹ቋጨ›› የሚለው ሲሆን በምንባቡ ዓውድ መሰረት ‹‹አጠናቀቀ/ዘጋ›› የመሳሰሉ ፍቺዎች አሉት ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከምንባቡ ዓውድ ውጭ ያለው ፍቺ ‹‹ሰገሰገ፣ ገመደ፣ አከረረ›› የሚል ነው፡፡ ይህንን ፍቺ በዓረፍተነገር ለማሳየትም ‹‹ሰይድ አዲሱን ጋቢ ቋጨ›› ሲል ዘርፉን አከረረ በማለት ከምንባቡ ዓውድ ውጭ ያለውን ፍቺ ያመልክቷቸው፡፡

ተግባር 3፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ውስጥ የተለያዩ የተሰመረባቸው ቃላት በዓረፍተነገሮች ቀርበው ዓውዳዊ ፍቺዎቻቸውን እንዲሰጡ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ይህንን ተግባር ለመስራት ያመቻቸው ዘንድም ቀድመው የራስዎን ዓረፍተነገሮች በማምጣት የተለያዩ ቃላት በዓውድ ውስጥ እና ከዓውድ ውጭ ያላቸውን ፍቺ ያሳዩዋቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ተማሪዎቹ በደብተራቸው ላይ በመጻፍ በግላቸው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በዚህ ክፍል የቀረቡትን ተግባራት ሰርተው ከጨረሱ በኋላ የተማሪዎቹን መልስ ይቀበሏቸው፡፡

- ✓ በመጨረሻም ለተማሪዎቹ መልሶች የማስተካከያ እርማት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

የቃላትን ዐውዳዊ ፍቺዎች የሚያሳዩ በተለያዩ ቀለማት የተቀለሙ ፍላሽ ካርዶች፡፡

ምዘና

- ✓ ተማሪዎች የዓውዳዊ ፍቺ እውቀት ማዳበራቸውን መከታተል፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

በጽሕፈት ክፍል በአንቀጽ ውስጥ የመሸጋገሪያ ቃላት መጠቀምን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት በሚገባ በማስተማር ተማሪዎች በአንቀጽ ውስጥ ተገቢዎቹን የመሸጋሪያ ቃላት ይጠቀሙ ዘንድ የሚረዳ አጭር ማስታዎሻ በመማሪያ መጽሐፉ ቀርቧል፡፡ ማስታዎሻውን በመነሻነት በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱን እንደሚከተለው ያከናውኑት፡፡

- ✓ በመጀመሪያ የትምህርቱን ርዕስ በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ለትምህርቱ ዝግጁ እንዲሆኑ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኘውን ማስታዎሻ እስከ ምሳሌዎቹ በደብተራቸው እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ማስታዎሻውን ጽፈው ከጨረሱ በኋላ እንደ መማሪያ ክፍሉ ነባራዊ ሁኔታ ከ2 እስከ 5 ተማሪዎች በቡድን ሆነው ስለትምህርቱ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ ለውይይት የሰጧቸው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ሁለት ወይም ሶስት ቡድኖች በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ አቅርበው ከጨረሱ በኋላ በምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻና ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ትምህርቱን እንደተገነዘቡ ካረጋገጡ በኋላ ከማስታዎሻው ቀጥሎ የቀረበውን ተግባር ያሰሯቸው፡፡

ተግባር፡-

- ✓ በዚህ ተግባር አምስት ክፍት ቦታዎች ያሉት አንድ አንቀጽ ቀርቧል፤ እንዲሁም ከአንቀጹ በፊት አምስት የመሸጋገሪያ ቃላት የቀረቡ ሲሆን ቃላቱን በክፍት ቦታዎቹ በማስገባት አንቀጹ ሙሉ ሀሳብ እንዲኖረው እንዲያደርጉ ታዘዋል፡፡
- ✓ ይህንን ለማድረግ ቀደም ሲል የተሰጣቸውን ማስታዎሻና ምሳሌ ተመልሰው እንዲመለከቱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ የታዘዙትን በትክክል እየሰሩ መሆናቸውን ይከታተሏቸው፡፡
- ✓ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን ተቀብለውና እርማት ሰጥተው ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያዎች

- ✓ ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ሀሳቦችን ለማጣመር የሚያለግሉ የመሸጋገሪያ ቃላትን የያዘ የሰንጠረዥ ቻርት

ምዘና

- ✓ የመሸጋገሪያ ቃላትን በአንቀጽ ውስጥ ሲጠቀሙ መከታተል፡፡

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ስምና ግስን በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀምን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ በተማሪው መጽሐፍ ላይአጭርማስታዎሻቀርቧል፡፡ማስ ዎሻውን በመጠቀም ትምህርቱን በሚገባ ለመስጠት የሚከተለውን ሒደት ተከትለው ያቅርቡት፡፡

- ✓ በመጀመሪያ የትምህርቱን ርዕስ በሰሌዳው ላይ በመጻፍ ለተማሪዎች ያሳውቋቸው፤ ማየት የተሳናቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ በሰሌዳው ላይ የጻፉትን ርእስ ድምጽዎን ከፍ በማድረግ ይግለጹላቸው፡፡

በመቀጠልም ማስታዎሻውንና ምሳሌዎቹን በደብተራቸው እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ ጽፈው ከጨረሱ በኋላ እንደክፍሉ ነባራዊ ሁኔታ ከ2 እስከ 5 ተማሪዎች በተካተቱባቸው ቡድኖች ከአሁን በፊት የተማሩትንና የተሰጣቸውን ማስታዎሻ በመመርኮዝ ስለስም እና ግስ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ተወያይተው ከጨረሱ በኋላ የውይይታቸውን ውጤት እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ አቅርበው ከጨረሱ በኋላ ስምንና ግስን በተመለከተ በምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻና ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ከገለጻው በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ሶስት ተግባራት በጽሑፍ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ እያንዳንዳቸውን ተግባራት በሚከተለው ቅደም ተከተል ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፦

- ✓ በዚህ ተግባር ስሞች በ‹ሀ› ምድብ እንዲሁም ግሶች በ‹ለ› ምድብ የቀረቡ ሲሆን፣ ለስሞቹ ተስማሚ የሆኑትን ግሶች እየመረጡ እንዲያዛምዱ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ይህንን ተግባር ተስማሚዎቹን ቃላት በጽሑፍ እንዲያዛምዱና የተዛመዱትን ቃላት በዓረፍተነገር መልክ እንዲጽፏቸው ያድርጉ፡፡
- ✓ በትክክል ተግባሩን እየሰሩ መሆናቸውን ይከታተሏቸው፡፡

ተግባር 2፦

- ✓ በዚህ ተግባር ዓረፍተነገሮች የቀረቡ ሲሆን ከዓረፍተነገሮቹ ውስጥ ስሞቹንና ግሶቹን ለይተው እንዲያወጡና እንዲያመለክቱ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ይህንን ተግባር ለመስራት ያመች ዘንድ ከጥያቄዎቹ በፊት የቀረበውን ምሳሌ አብራርተው ያስረዷቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ተማሪዎቹ ሌሎቹን ጥያቄዎች በጽሑፍ እንዲሰሯቸው ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ሲሰሩ በትክክል እየሰሩ መሆናቸውን ይከታተሏቸው፡፡

ተግባር 3፦

- ✓ በዚህ ተግባር ስር አምስት ስምና ግሶች ተቀላቅለው የቀረቡ ሲሆን፣ በቃላቱ ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ታዘዋል፡፡
- ✓ ይህንን ተግባር በጽሑፍ እንዲሰሩ ያድርጓቸውና መስራታቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፤ አስፈላጊ ከሆነ ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ የተሰጡትን ስሞችና ግሶች በተገቢ ቦታቸው ተጠቅመው ዓረፍተነገሮቹን ማዋቀራውቸን ያረጋግጡ፡፡
- ✓ ሶስቱንም ተግባራት ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሶቻቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ መልሶቹን ተቀብለው ከጨረሱ በኋላ የመልስ እርማት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

በተለያዩ ቀለማት የተቀለሙና ስምና ግሶችን የያዙ ፍላሽ ካርዶች

ምዘና

ስምና ግስን ሲለዩ መከታተል፡፡

የተመረጡ ተግባራት መልሶች

ተግባር 1 ፡-

ቀጥሎ በ‹‹ሀ››ስር የቀረቡት ስሞችን በ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት ግሶች በመምረጥ ሙሉ ሀሳብ እንዲያስተላልፍ አድርጉ፡፡

1. ሐ 2. ሀ 3. ሠ 4. መ 5. ለ

ተግባር 2፡-

ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ባሉት ዓረፍነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ስምና ግሶች በማውጣት ለይታችሁ በየቃል ክፍሎቻቸው መድቧቸው፡፡

| ተ.ቁ | ዓፍተገር | ስም | ግስ |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ | ልጆቹ ደከሙ፡፡ | ልጆቹ | ደከሙ |
| ሀ | አስቴር ተመለሰች፡፡ | አስቴር | ተመለሰች |
| ሐ | መብረቅ መታው፡፡ | መብረቅ | መታው |
| መ | ማር እወዳለሁ፡፡ | ማር | እወዳለሁ |
| ሠ | ዝናቡ መጣ፡፡ | ዝናቡ | መጣ |
| ረ | ጸሐይዋ ታቃጥላለች፡፡ | ጸሐይዋ | ታቃጥላለች |

# አማርኛ
(፩) ክፍል

# ምዕራፍ ሰባት
# ምግብ

(18 ክፍለ ጊዜ)

የምዕራፉ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ አንድን ገላጭ ጽሁፍ አዳምጠው መልዕክቱን ይገልጻሉ፡፡
- ✓ ስርዓተ ነጥቦችን ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ አስተካክለው ያነባሉ፡፡
- ✓ ሂደታዊ ተንታኝ አንቀጾችን ተረድተው ይገልጻሉ፡፡
- ✓ የምዕላድ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው እንግዳ ቃላትን ያነባሉ፡፡

ይዘት፡-

- ✓ ያዳመጡትን ሀሳብ ማወዳደርና ማነጻጸር
- ✓ የሒደታዊ ትንታኔ አንቀጾችን ማንበብና መጻፍ
- ✓ ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ መስጠት
- ✓ የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞችን መጠቀም

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### የምግብ አዘገጃጀት

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

ቀጥሎ ‹‹የምግብ አዘገጃጀት›› በሚል ርእስ የማዳመጥና የመናገር ክሒሎን ለማስተማር ምንባብ ቀርቧል፡፡ ትምህርቱን በሚከተሉት ቅደም ተከተሎችና አቀራረቦች ያከናውኑ፡፡

**ቅድመ ማዳመጥ**

- ✓ ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት በቅድመ ማዳመጥ ተግባር ስር ያለውን ጥያቄ ተማሪዎችን ያሰሯቸው፡፡

ተግባር፡-

- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ የቅድመ ማዳመጥ ተግባር ስር አንድ ሰንጠረዥ ቀርቧል፤ በሰንጠረዡ ውስጥም የሚያውቋቸውን አምስት የምግብ አይነቶች እና ምግቦቹን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጓቸውን ግብዓቶች እንዲገልጹ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ይህንን ጥያቄ ለመስራት በመጀመሪያ ሰንጠረዡን በደብተራቸው እንዲያዘጋጁ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በተጠየቁት መሰረት የምግብ አይነቶችንና የማዘጋጃ ግብዓቶችን እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሰንጠረዡን አሟልተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ መልስ ከሰጡ በኋላ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አይጠበቅብዎትም፡፡
- ✓ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ በአዳምጦ መረዳት ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲያነቧቸው ያድርጓቸው፡፡

ይህንን ማድረግዎት እርስዎ በሚያነቡበት ወቅት ተማሪዎቹ ትኩረት ሰጥተው ማስታዎሻ የሚይዙባቸውን የማዳመጥ ክፍል ቀድመው እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፡፡

- ✓ በመቀጠልም የሚነበብላቸውን ምንባብ በጥሞና እንዲያዳምጡ ያሳስቧቸው፤ እርስዎ በሚያነቡበት ወቅትም ማስታዎሻ እየያዙ እንዲያዳምጡ ያሳስቧቸው፡፡

### የማዳመጥ ሒደት

ተግባር፡-

- ✓ ተማሪዎቹ ለማዳመጥ ዝግጁ ከሆኑ በኋላ ረጋ ባለና ሁሉም ተማሪዎች ሊያደምጡዎት በሚችሉት ድምጸት ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ ምንባቡን ሲያነቡ መስማት የተሳናቸው ወይም የመስማት ውስንነት ያለባቸውን ተማሪዎች ባገናዘበ መንገድ ያቅርቡት፡፡
- ✓ በምንባቡ መሀል ላይ ያሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ በትክክል እያዳመጡ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ✓ እየተከታተሉዎት መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ምንባቡን ማንበብ ካቋረጡበት ቦታ ማንበብዎን ይቀጥሉ፡፡

### አዳምጦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበውላቸው እንደጨረሱ እርስዎ ሲያነቡ ተማሪዎቹ በያዙት ማስታዎሻ በመታገዝ የአዳምጦ መረዳት ተግባራትን እንደሚከተለው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር 6 ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን በያዙት ማስታዎሻ በመታገዝ በቃል የሚመለሱ ናቸው፡፡ ይህም ማዳመጥንና መናገርን በማጣመር ማስተማር ያስችልዎታል፡፡
- ✓ ሶስቱ ጥያቄዎች (‹ሀ›፣ ‹ለ› እና ‹መ›) ካዳመጡት ምንባብ በቀጥታ የሚመለሱ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ሶስት ጥያቄዎች (‹ሐ›፣ ‹ሠ› እና ‹ረ›) ደግሞ አንድምታዊ ምላሾችን የሚሹ በመሆናቸው እንደጥያቄዎቹ ባህርያት የተማሪዎቹን ምላሾች ይቀበሏቸው፡፡

- ✓ በጥያቄዎቹ ባህርያት መሰረትም ከምንባቡ በቀጥታ ለሚመለሱት ጥያቄዎች የሚሰጧቸውን መልሶች የምንባቡን ሀሳብ መሰረት ያደረጉ መልሶች እንዲሰጡዎት ያሳስቧቸው፡፡
- ✓ እንዲሁም ለቀሪዎቹ የአንድምታ ጥያቄዎች ያዳመጡትን ምንባብ ከቀደመ እውቀታቸው ጋር በማቀናጀት እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ለአንድምታዊ ጥያቄዎች ሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ መልስ ላይሰጡ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም መልሶቻቸውን ሲቀበሉ ንግግራቸውን እንዲቀጥሉ ከማበረታታት ውጭ መልሳቸው ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን መግለጽ አይጠበቅብዎትም፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ምላሽ ተቀብለው ከጨረሱ በኋላ ምንባብ ተኮር ለሆኑት ጥያቄዎች ለሰጧቸው ምላሾች የመልስ እርማት ይስጧቸው፤ እንዲሁም ለአንድምታዊ ጥያቄዎች ለተሰጡት ምላሾች አጠቃላይ አስተያየት በመስጠት ወደ ቀጣዩ ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር አንድ ጥያቄ የቀረበ ሲሆን በሁለት መንገዶች በሚዘጋጁ የሰላጣ አይነቶች የሚታዩትን አንድነት እና ልዩነት እንዲገልጹ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ይህንን ጥያቄ ለማሰራት እንደ ክፍሉ ነባራዊ ሁኔታ ከ3 እስከ 5 ተማሪዎች የተካተቱባቸው ቡድኖችን ይመስርቱ፡፡
- ✓ ከዚያም ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎቹን ቃኝተው እርስዎ ሲያነቡ ማስታዎሻ እንዲይዙ ባሳሰቧቸው መሰረት በሁለቱ መንገዶች በተዘጋጁት ሰላጣዎች መካከል የሚታየውን አንድነትና ልዩነት በተመለከተ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ ለውይይታቸው የተወሰነ ጊዜ ከሰጧቸው በኋላ ከየቡድኖቹ አንድ አንድ ተማሪ እየመረጡ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ይህንን ተግባር የሚያሰሯቸው ሁለት ነገሮችን ማወዳደር እና ማነጻጸርን እንዲለማመዱ ነው፡፡
- ✓ በመሆኑም በዚህ ተግባር ከታዘዙት ጥያቄ በተጨማሪ ልዩ ልዩ ስእሎችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም ስእሎቹን እንዲያወዳድሩ እና እንዲያነጻጽሩ በማድረግ ያለማምዷቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ስራዎቻቸውን አቅርበው ከጨረሱ በኋላ የማጠቃለያ አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

## የምግብ አዘገጃጀት

ምግብ ለሰዎች ከሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች አንዱና ዋናው ሲሆን፣ ከዕፅዋት ወይም ከእንስሳት ይገኛል፡፡ ከተክሎች የሚገኘው ምግብ፣ የእህል፣ የአትክልትና የፍራፍሬ ምግቦችን ያካትታል፡፡ ከእንስሳት የሚገኘው ደግሞ፣ ስጋን፣ እንቁላልን፣ ወተትንና የወተት ተዋጽዖዎችን ይይዛል፡፡ ምግብ ከሚሰጠው ጠቀሜታ አኳያ፡- ገንቢ፣ ኃይልና ሙቀት ሰጪ እንዲሁም በሽታ ተከላካይ ተብሎ በሶስት ክፍል ይመደባል፡፡ ምግብን ሰዎች፣ ከአካባቢያቸው ዕፅዋትና እንስሳት ውጤቶች፣ እንደየባህልና ልማዳቸው በተለያየ መንገድ ያዘጋጁታል፡፡ እስኪ ሰላጣ እንዴት እንደሚዘጋጅ ቀጥለን እንመልከት፡፡

በአሁኑ ጊዜ በርካታ የሰላጣ ዓይነቶች ይታወቃሉ፡፡ የሀበሻ ሰላጣ፣ አረንጓዴ ሰላጣ፣ ፍሪዙ ሰላጣ፣ ቀይ ፍሪዙ ሰላጣ፣ የጀርመን ሰላጣ፣ የቻይና ሰላጣ ወዘተ. የሚባሉ የሰላጣ ዓይነቶች በየገበያ ቦታው ይገኛሉ፡፡ ርካሹና በቀላሉ የሚገኘው ግን የሀበሻ ሰላጣ ነው፡፡

ሰላጣ በብዙ መንገድ ማዘጋጀት እንችላለን፡፡ ዋናው የሰላጣ አዘገጃጀት ዘዴ፣ ሰላጣን ከተለያዩ አትክልት ጋር ከትፎ በማቀላቀል ማጣፈጫ ጨምሮ መመገብ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የተለመደው ሰላጣን ከቲማቲም ጋር ብቻ አደባልቆ በማዘጋጀት ለምግብነት መጠቀም ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ግን እንደኪያር፣ የፈረንጅ ቃሪያ፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ካሮትና የመሳሰሉትን አትክልት ከሰላጣ ጋር ጨምሮ ማዘጋጀት የተመረጠና ለጤናም ተስማሚ ነው፡፡

ዋና ዋና የምግብ ምንጮች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

ምግብ ሲዘጋጅ ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል?

እነዚህን ጥሬ ዕቃዎች በምንጠቀምበት ጊዜ በደንብ ማጠብ ይገባል፡፡ ሰላጣ ማዘጋጀት ቀላል ቢሆንም፣ ንጽህናና ጥንቃቄን ይፈልጋል፡፡ ሰላጣ ሳይበስል የሚበላ ስለሆነ፣ ሰላጣውን በደንብ ማጠብ ይገባል፡፡ ሰላጣው ከታጠበ በኋላ ንፁህ ጨርቅ ላይ በማድረግ ማጠንፈፍ የሚገባ ሲሆን፣ ይህም ሰላጣው ከማጣፈጫ (ድሬሲንግ) ጋር ሲቀላቀል እንዳይበላሽ ይረዳል፡፡

የሰላጣ ማጣፈጫ (ድሬሲንግ) የሚባለው፣ ለሰላጣው ጥፍጥናንና ጣዕምን የሚሰጠው ነው፡፡ የሰላጣ ማጣፈጫዎች ከተለያዩ ቅመማ ቅመሞች፣ ዘይቶች እና ጭማቂዎች የሚሰሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ ሰላጣን እንዳስፈላጊነቱ ከተለያዩ ማጣፈጫዎች ጋር እያቀያየሩ በማዘጋጀት መመገብ፣ የሰላጣ ምግብ እንዳይሰለቸንና ይበልጥ እንድንወደው ያደርጋል፡፡

ማጣፈጫዎችን በቅድሚያ ሰርተን፣ ፍሪጅ ውስጥ ወይም ቀዝቃዛ ቦታ በማስቀመጥ በፈለግነው ጊዜ እያነሳን መጠቀም ይቻላል፡፡ የሰላጣው ቅጠል እንዲሞትና ጣዕሙን እንዲያጣ ሊያደርገው ስለሚችል፣ ማጣፈጫዎችን ሰላጣው ላይ ጨምረን ለረጅም ጊዜ ማስቀመጥ አይገባም፡፡ ስለሆነም፣ ማጣፈጫውንና ሰላጣውን ማቀላቀል ያለብን ምግብ ሊቀርብ ሲል መሆን አለበት፡፡

ብዙ ሰዎች፣ ልጆች ሰላጣ መመገብ ያለባቸው አይመስላቸውም፡፡ ይሁን እንጂ ህፃናት ከሁለት ዓመታቸው ጀምሮ የተለያዩ ሰላጣዎችን በተለያዩ ዓይነት ማጣፈጫዎች በማዘጋጀት መመገብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የሁለት አመት ህፃናትን ጥሬ ሰላጣ መመገብ ካለብን፣ ሰላጣው በከፍተኛ ጥንቃቄና ንፅህናው ተጠብቆ መዘጋጀትና ደቀቅ ተደርጎ መከተፍ ይኖርበታል፡፡

በአጠቃላይ ሰላጣንም ሆነ ሌሎች ምግቦችን በንጽህና በማዘጋጀትና እንደአስፈላጊነቱም በማብሰል መመገብ ይገባል፡፡ ምግባችን ሲዘጋጅ፣ በተቻለ መጠን የእንስሳትንና የዕፅዋትን ውጤቶች ያካተተ እንዲሆን በማድረግ ማመጣጠን ይኖርብናል፡፡ የተመጣጠነ ምግብ አዘጋጅቶ መመገብ ጤናማ፣ ጠንካራና ደስተኛ እንድንሆን ያደርጋል፡፡

(ጆርዳና ኩሽና፣ ቅፅ-1፤ 2007፤ ገጽ-14 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

ምዘና፡-

- ✓ ያዳመጡት ምንባብ የያዘውን ሀሳብ በቃል ሲገልጹ መከታተል፡፡
- ✓ ስዕሎችን ሲያወዳድሩና ሲያጻጽሩ መከታተል፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ፡-

- ✓ አንድነትና ልዩነት ያላቸው ልዩ ልዩ ስዕሎች፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

የትምህርቱ አቀራረብ፡-

መምህር!

በዚህ ክፍል ማንበብን ለማስተማር በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበ ‹‹ጤናማ አመጋገብ›› የሚል ምንባብ ይገኛል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም ትምህርቱን እንደሚከተለው ያቅርቡ፡፡

### ቅድመ ንባብ

- ✓ ተማሪዎቹ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የሚሰሩት አንድ ተግባር ሲኖር ተግባሩን እንደሚከተለው በቃል ያሰሯቸው፡፡

ተግባር ፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ሁለት ጥያቄዎች ሲኖሩ ምንባቡ ስለያዘው ሀሳብ ፍንጭ እንዲያገኙ ይረዷቸዋል፡፡
- ✓ ይህንን ለማድረግም ተማሪዎቹ የአመጋገብ ስርዓትን በተመለከተ ከአሁን በፊት ያላቸውን እውቀት ተጠቅመው በቃል መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ምላሽ ተከትለው ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አያስፈልግዎትም፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ምላሽ ከተቀበሉ በኋላ ምንባቡን በተናጠል ድምጽ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

### የንባብ ሒደት

- ✓ ተማሪዎች በተናጠል ድምጽ ሳያሰሙ እያነበቡ መሆናቸውን እየተዘዋወሩ ያረጋግጡ፡፡

## አንብቦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበው እንደጨረሱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን በተግባራቱ መመሪያዎች መሰረት እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡ በዚህ ክፍል ሶስት ተግባራት በመማሪያ መጽሐፉ ቀርበዋል፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የቀረቡት ስድስት ጥያቄዎች በቀጥታ ከምንባቡ ውስጥ የወጡ የምንባቡን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት የሚመለሱ ናቸው፡፡
- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በቃላቸው መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፤ መልሶቻቸውንም ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ለጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ የሰጧቸውን መልሶች በመቀበልና የማስተካከያ ምላሾች በመስጠት ወደ ሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የቀረቡት አምስት ጥያቄዎች ሲሆኑ ምንባቡን ተመርኩዘው የሚሰሯቸው ቋንቋ ነክ ጥያቄዎች ናቸው፡፡
- ✓ በመጀመሪያ ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ በመጻፍ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፤ የሚሰጧቸው ምላሾች ምክንያታዊ መሆን እንደሚጠበቅባቸው ያሳስቧቸው፡፡
- ✓ ለምሳሌ በተራ ቁጥር ‹ሀ› የቀረበው ጥያቄ በመጀመሪያው አንቀጽ ስንት ዓረፍተነገሮች እንደሚገኙ የሚጠይቅ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ተማሪዎቹ መልስ ሲሰጡ የዓረፍተ ነገሮቹን ቁጥር ብቻ ሊጽፉ ይችላሉ፤ መልሳቸውን ሲቀበሏቸው ግን ዓረፍተነገሮቹን እየቆጠሩ እንዲያሳዩዎት ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን ከነመልሶቻቸው ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን ተቀብለው የቃል ግብረ መልስ በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 3፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ተማሪዎች የዚህ ክፍል ዓላማ የሆነውን አቀላጥፎ ማንበብ እንዲለማመዱ የሚያዝ ጥያቄ አለ፡፡
- ✓ አቀላጥፈው ማንበብን ሲለማመዱ ማገዣ ይሆናቸው ዘንድ በመማሪያ መጽሐፉ ሰንጠረዥ ቀርቦላቸዋል፤ ሰንጠረዡን በወረቀት ላይ እንዲያዘጋጁ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በትእዛዙ መሰረት ለማከናወን በመጀመሪያ ተማሪዎችን በጥንድ በጥንድ አድርገው ያቧድኗቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም የምንባቡን ሁለተኛ አንቀጽ ተራ በተራ ድምጽ እያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በጥንድ ከተቧደኑት ውስጥ አንድኛው ድምጽ እያሰማ ሲያነብ የሚገድፋቸውን ቃላት ሌላኛው ተማሪ ደግሞ ‹‹በመጀመሪያ ንባብ በትክክል ያልተነበቡ ቃላት ብዛት›› በሚለው የሰንጠረዡ ክፍል ታሊ በማድረግ (እዝባርን በመጠቀም) እንዲቆጥር ያድርጉ፡፡
- ✓ የመጀመሪያው ተማሪ አንብቦ ሲጨርስ ደግሞ ሁለተኛው ተማሪ በተራው ያነባል ሌላኛው ተማሪ ደግሞ ከላይ በቀረበው መንገድ ይቆጥራል፡፡
- ✓ ይህንን መመሪያ ሰጥተው ተማሪዎች ተግባሩን እንዲያከናውኑ ካደረጉ በኋላ ተማሪዎቹ በሚገባ እያከናወኑ መሆናቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ሰርተው ካጠናቀቁ በኋላ አጠቃላይ አስተያየትና ማጠቃለያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

ምዘና፡-

- ✓ የምንባቡን ሀሳብ ሲገልጹና አቀላጥፈው ሲያነቡ መከታተል

የተመረጠ ተግባር መልስ

ተግባር 1፡-

የሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ዐረፍተ ነገሮች ይዘት፣ ትክክል ከሆነ ‹‹እዉነት››፣ ስህተት ከሆነ ደግሞ ‹‹ሐሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. ሀሰት

2. ሀሰት

3. እውነት

4. ሀሰት

5. እውነት

6. እውነት

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ መስጠትን ይማራሉ፡፡ ትምህርቱን ለማከናወን ይረዳዎት ዘንድ በመማሪያ መጽሐፉ ሁለት ተግባራት የቀረቡ ሲሆን ትምህርቱን በሚከተለው መንገድ ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ መስጠትን በተመለከተ ባለፉት ክፍሎች የተማሯቸውን መሰረት በማድረግ አፈታታቸውን በምሳሌ አስደግፈው ያስረዷቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በመማሪያ መጽሐፉ ያሉትን ሁለት ተግባራት እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ክፍል ለአምስት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ እንዲፈልጉ በማዛመድ መልክ ቀርበውላቸዋል፡፡
- ✓ ተግባሩን በደብተራቸው ከጻፉ በኋላ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን በመቀበልና የማስተካከያ እርማት በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር አምስት ዓረፍተነገሮች የቀረቡ ሲሆን ለተሰመረባቸው ቃላት ዓውዳዊ ፍቺ እና መዝገበ ቃላዊ ፍቺ እንዲሰጡ ታዝዘዋል፡፡
- ✓ ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጫ ይሆን ዘንድም ከተግባሩ ስር ቃላቱን፣ ዓውዳዊ ፍቺዎቻቸውን እና መዝገበ ቃላዊ ፍቺዎቻቸውን የሚሰጡባቸው ክፍት ቦታዎችን የያዘ ሰንጠረዥ ቀርቦላቸዋል፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹንና ሰንጠረዡን በደብተራቸው ላይ እንዲጽፏቸውና መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ የተማሪዎቹን ምላሽ ተቀብለው እርማትና ማጠቃለያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ፡-

- ✓ የቃላትን መዝገበ ቃላዊና ዓውዳዊ ፍቺ የሚያሳዩና በተለያዩ ቀለማት የተቀለሙ ፍላሽ ካርዶች ወይም የሰንጠረዥ ቻርቶች፡፡

ምዘና፡-

- ✓ ለቃላት መዝገበ ቃላዊና ዓውዳዊ ፍቺዎች ሲሰጡ መከታተል፡፡

የተመረጡ ተግባራት መልስ፡-

ተግባር 1፡-

ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ረድፍ የቀረቡትን ቃላት በ ‹‹ለ›› ረድፍ ከሚገኘው መዝገበ ቃላዊ ፍችዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

1. መ   2. ሰ   3. ሐ   4. ሀ   5. ለ

ተግባር 2፡-

ከዚህ በታች በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት አውዳዊና መዝገበ ቃላዊ ፍቺ፣ በሠንጠረዡ ውስጥ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

| የተሰመረበት ቃል | የቃሉ አገባባዊ ፍቺ | የቃሉ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ |
|---|---|---|
| ማለፊያ | ጥሩ (የሚጣፍጥ) | መሄጃ (መሻገሪያ) |
| በላ | ገደለ | ተመገበ |
| ቃሪያ | ያልበሰለ (የማይረባ) | የሚያቃጥል የጓሮ አትክልት |
| በሳል | ጠቃሚ | ለመበላት ዝግጁ የሆነ |
| ቀጠፈ | ዋሸ | ቆረጠ |

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ሁለት ዐበይት የትምህርት ይዘቶችን ይማራሉ። ይዘቶቹም ሒደታዊ የአንቀጽ አጻጻፍ ስልት እና ስርዓተ ነጥቦች ናቸው። እነዚህን ትምህርቶች ለማስተማር ይረዳዎት ዘንድ የተወሰኑ ማስታዎሻዎችና ተግባራት በመማሪያ መጽሐፉ ቀርበውለዎታል። እንዲሁም ስርዓተ ነጥብን የተመለከተ አጭር ማስታዎሻ በመምህሩ መምሪያ ይቀርብልዎታል። የትምህርቱ ዓላማ ይሳካ ዘንድ ማስታዎሻዎቹን እና ተግባራቱን በመጠቀም የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሂደትና ቅደም ተከተል በመከተል ትምህርቱን ያቅርቡላቸው።

### ሒደታዊ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልት

- ✓ የመጀመሪያው የዚህ ክፍል ትምህርት ሒደታዊ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልት ነው። ይህንን ትምህርት ለማቅረብ ይረዳዎት ዘንድ በመማሪያ መጽሐፉ አጭር ማስታዎሻ እና አንድ ተግባር ቀርቦልዎታል።

- ✓ በመጀመሪያ ቀደም ባሉት ምዕራፎች የተማሯቸውን ገላጭና ተራኪ የአንቀጽ መጻፊያ ስልቶች በማስታዎስ የስልቶቹን ምንነት እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎቹን ምላሽ ተከትለውም ሒደታዊ ስልትን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኘውን ማስታዎሻ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ማስታዎሻውን ጽፈው እንደጨረሱ ሒደታዊ ስልትን በቀደሙት ምዕራፎች የተማሯቸው ስልቶች ጋር እያነጻጸሩና እያወዳደሩ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተወያይተው እንደጨረሱ ሀሳባቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ አቅርበው ከጨረሱ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበውን ምሳሌ በመጠቀም ገለጻና ማብራሪያ ያድርጉላቸው፤ አስፈላጊ ከሆነም በሒደታዊ ስልት የተጻፈ ሌሎች አንቀጾችን በማምጣት ግልጽ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ትምህርቱን አስረድተው ከጨረሱ በኋላ ከማስታዎሻው ስር የቀረበውን ተግባር እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የቀረበላቸውን ቢጋር ተጠቅመው ፍርፍር ለማዘጋጀት የሚከናወኑ ተግባራትን በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡና በመቀጠልም የተለያዩ የመሸጋገሪያ ቃላትን በመጠቀም በቢጋሩ ላይ ያስፈሯቸውን ሀሳቦች አቀነባብረው በአንቀጽ መልክ እንዲጽፏቸው ታዝዘዋል፡፡
- ✓ ይህንን ተግባር ከመስራታቸው በፊት እንደክፍሉ ነባራዊ ሁኔታ ከ3 እስ 5 ተማሪዎችን የያዙ ቡድኖችን ይመስርቱ፡፡
- ✓ በመቀጠልም በቡድናቸው እየተወያዩ ቢጋሩን እንዲያሟሉና ቢጋሩን ወደ ሂደታዊ አንቀጽ እንዲቀይሩ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ ተማሪዎቹ ተግባሩን በመስራት ላይ እያሉ እየተዘዋወሩ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ በተወካዮቻቸው አማካኝነት ለክፍል ጓኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ስራቸውን አቅርበው ከጨረሱ በኋላ ተገቢውን ግብረ መልስ በቃል ይስጧቸው፡፡
- ✓ ግብረ መልስ ከሰጡ በኋላ ማጠቃለያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

## ስርዓተ ነጥብ

- ✓ የዚህ ክፍል ሁለተኛው የትምህርት ይዘት ስርዓተ ነጥብ ነው፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ ይረዳዎት ዘንድ በመማሪያ መጽሐፉ የስርዓተ ነጥብ እና የምኅጻረ ቃል ምንነት በአጭሩ ተገልጿል፡፡
- ✓ ማስታዎሻውን በመጠቀም ትምህርቱን እንደሚከተለው ያቅርቡት፡፡
- ✓ በመጀመሪያ በቀደሙት የክፍል ደረጃዎች የተማሯቸውን በማስታወስ የሚያውቋቸውን የስርዓተ ነጥብ አይነቶችና አገልግሎቶቻቸውን በሰሌዳው ላይ እንዲጽፉ ያድረጓቸው፡፡
- ✓ የተወሰኑ ተማሪዎች ከጻፉ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ስርዓተ ነጥቦችን እና አኅጽሮተ ቃልን የተመለከቱ ማስታዎሻዎች በደብተራቸው እንዲጽፏቸው ያድርጓቸው፡፡ መምህር በክፍል ውስጥ አይነስውር ተማሪ ካለ በአንባቢ አማካኝነት ወደ ብሬል እንዲገለብጥ እድሉን ያመቻቹለት፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ማስታዎሻዎቹን ጽፈው ከጨረሱ በኋላ በተለያዩ ምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻና ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ማብራሪያውን ሲሰጡ የተማሪዎቹን የክፍል ደረጃ ባገናዘበ መልኩ የተወሰኑት የስርዓተ ነጥብ አይነቶች ላይ ያተኩሩ፡፡

- ✓ ምንም እንኳን በመማሪያ መጽሐፉ ስምንት የስርዓተ ነጥብ አይነቶች ቢኖሩም የእርስዎ ትኩረት ግን አራቱ ላይ ብቻ ይሁን።
- ✓ አራቱ የስርዓተ ነጥብ አይነቶችም ነጠላ ሰረዝ፤ አራት ነጥብ፣ የጥያቄ ምልክት እና አንድ ነጥብ ናቸው።
- ✓ ከእነዚህ ውጭ ያሉትን የስርዓተ ነጥብ አይነቶች የክፍል ደረጃቸው እያደገ ሲሄድ በሚገባ ስለሚማሯቸው ምንነታቸውን ከመግለጽ በዘለለ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ እንዳይገቡ።
- ✓ በዚህ መሰረት ትምህርቱን አስረድተው ከጨረሱ በኋላ ከማስታዎሻዎቹ ቀጥለው የቀረቡትን ተግባራት እንደሚከተለው ያሰሯው።

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ስርዓተ ነጥባቸው የተጓደሉ ዓረፍተነገሮች ቀርበዋል።
- ✓ ጥያቄዎቹን በደብተራቸው እንዲጽፏቸውና ተገቢዎቹን የስርዓተ ነጥብ አይነቶች በማስገባት ዓፍተ ነገሮቹ ሙሉ ሀሳብ እንዲያስተላልፉ እንዲያደርጓቸው ይዘዟቸው።
- ✓ ጥያቄዎቹን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ ስራዎቻቸውን በመሰብሰብ የጽሑፍ ግብረ መልስ ይስጧቸው።
- ✓ በመጨረሻም መልሶቹን በጋራ በመስራትና ማጠቃለያ በመስጠት ወደ ቀጣዩ ተግባር ይሸጋገሩ።

ተግባር 3፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የተለያዩ ስሞችንና ስያሜዎችን በአኅጽሮተ ቃል እንዲጽፉ ታዝዘዋል።
- ✓ ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ በመጻፍ አንድ ነጥብን ተጠቅመው በአኅጽሮተ ቃል እንዲጽፏቸው ያድርጉ።

- ✓ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን በመቀበልና በጋራ በመስራት ወደ ቀጣዩ ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 4፡-

በዚህ ተግባር በአኀጽሮተ ቃል የተጻፉትን በሙሉ መጠሪያቸው እንዲጽፉ ታዘዋል፡፡

- ✓ ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ በመጻፍ መልሳቸውን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

ተግባሩን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ ፣መልሶቻቸውን በመቀበል እርማት ይስጧቸው፡፡

- ✓ በመጨረሻም ማጠቃለያና አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የሂደታዊ አንቀጽ አጻጻፍን የያዘ ቢጋር
- ✓ ለክፍሉ ደረጃ የተገለጹትን አራት የስርዓተ ነጥብ አይነቶች እና አገልግሎቶቻቸውን የያዘ ቻርት፡፡
- ✓ ልዩ ልዩ አኀጽሮተ ቃላትንና ከነዝርዝር መጠሪያቸው የያዘ ቻርት

ምዘና

- ✓ በሒደታዊ ስልት አንቀጽ ሲጽፉ፣ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው ሲጠቀሙ እና ቃላትን በአኀጽሮተ ቃል ሲጽፉ መከታተል

ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

የትምህርቱ አቀራረብ

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የሚቆጠሩ እና የማይቆጠሩ ስሞችን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ ይረዳዎት ዘንድ በመማሪያ መጽሐፉ አጭር ማስታዎሻና ተግባራት ቀርበዋል፡፡ የትምህርቱ ዓላማ ይሳካ ዘንድ ማስታዎሻዎቹን እና ተግባራቱን ተጠቅመው በሚከተለው መንገድ ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ ቀደም ባሉት ክፍሎች የተማሯቸውን አስታውሰው ስለስም ምንነት የሚያውቁትን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ  የትምህርቱን ርዕስ በመግለጽ በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኘውን ማስታዎሻ ያስጽፏቸው፡፡
- ✓ ማስታዎሻውን ጽፈው ከጨረሱ በኋላ ስለርዕሰ ጉዳዩ በቡድን ተወያይተው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ አቅርበው ከጨረሱ በኋላ በምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻና ማብራሪያ በመስጠት በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት ተግባራት እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የተለያዩ የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞች በቢጋር መልክ የቀረቡ ሲሆን ስሞቹን በአይነታቸው እንዲመድቧቸው ታዝዘዋል፡፡
- ✓ በታዘዙት መሰረት ቢጋሩን በደብተራቸው ላይ በመጻፍ የሚቆጠሩትንና የማይቆጠሩትን ስሞች ለይተው እንዲያመለክቱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን በመቀበል እርማት ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ማጠቃለያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞችን የያዘ የሰንጠረዥ ቻርት

ምዘና፡-

- ✓ የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞችን መለየታቸውን መከታተል

የተመረጠ ተግባር መልስ፡-

ተግባር

ከዚህ በታች በቢጋሩ ውስጥ የተዘረዘሩትን ስሞች የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ በማለት መድቡ፡፡

| የሚቆጠሩ | የማይቆጠሩ |
|---|---|
| ዛፍ | ነፋስ |
| ጃንጥላ | ፍቅር |
| ሰዐት | ፍርሀት |
| ጠርሙስ | ወተት |
| አገልግል | እሳት |
| ቢራቢሮ | ዝናብ |
| ብርቱካን | |
| ኮከብ | |
| ልጅ | |
| መንደር | |
| ብስኩት | |

# አማርኛ

(፰) ክፍል

# ምዕራፍ ስምንት
# በኢትዮጵያ የሚገኙ የዱር እንስሳት

(18 ክፍለ ጊዜ)

የምዕራፉ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ ውስብስብ ቃላት በምእላድ እንዴት እንደሚከፋፍሉ ይገልጻሉ፡፡
- ✓ ውስብስብ ቃላትን ያነባሉ፡፡
- ✓ አወዳዳሪና አነጻጻሪ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ✓ ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ✓ ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን ይጠቀማሉ፡፡

ይዘት

- ✓ ካዳመጡት ውስጥ ያገኙትን አዲስ ስም መዘርዘር
- ✓ ጽሑፉን አንብበው ከሕይወታቸው ጋር ማዛመድ
- ✓ አንቀጽ ጽፎ ማወዳደርና ማነጻጸር
- ✓ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት
- ✓ ተሻጋሪና ኢ-ተሻጋሪ ግሶችን መለየት

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

## በቀቀኖችን ስሙን

የትምህርቱ አቀራረብ፡-

መምህር!

በዚህ ክፍል ምንባብን በማዳመጥ ሀሳቡን መግለጽን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማስተማር ይረዳዎት ዘንድ ‹‹በቀቀኖችን ስሙን›› የሚል ምንባብ ቀጥሎ ቀርቦልዎታል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም ትምህርቱን ለማቅረብ ቀጥሎ ያውን የመማር ማስተማር ሒደት ይከተሉ፡፡

## ቅድመ ማዳመጥ

- ✓ ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት በቅድመ ማዳመጥ ተግባር ስር ያሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲሰሯቸው ያድርጉ፡፡

ተግባር፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የሚነበብላቸው ምንባብ ስለምን እንደሚያወሳ ቀድመው እንዲገምቱ የሚያደርጓቸውን ሶስት ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ስለበቀቀን የሚያውቁትን፣ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ እንስሳትን፣ እንዲሁም ከሰው ጋር የሚኖሩ የዱር እንስሳት የሚያውቁ ከሆነ እንዲገልጹ የሚጠይቁ ናቸው፡፡
- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ መልስ ከሰጡ በኋላ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አይጠበቅብዎትም፡፡
- ✓ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ የሚነበብላቸውን ምንባብ በጥሞና እንዲያዳምጡ ያሳስቧቸው፡፡

## የማዳመጥ ሒደት

ተግባር፡-

- ✓ ተማሪዎቹ ለማዳመጥ ዝግጁ ከሆኑ በኋላ ረጋ ባለና ሁሉም ተማሪዎች ሊያደምጡዎት በሚችሉት ድምጸት ያንብቡላቸው፤ አስፈላጊ ከሆነም አንድ ጊዜ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ ምንባቡን ሲያነቡ መስማት የተሳናቸው ወይም የመስማት ውስንነት ያለባቸውን ተማሪዎች ባገናዘበ መንገድ ያቅርቡት፡፡

- ✓ በምንባቡ መሀል ላይ ያሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ በትክክል እያዳመጡ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ✓ እየተከታተሉዎት መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ምንባቡን ካቋረጡበት ቦታ ይቀጥሉ፡፡

### አዳምጦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበውላቸው እንደጨረሱ የአዳምጦ መረዳት ተግባራትን እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የቀረቡት ጥያቄዎች በቃል የሚመለሱ ሲሆኑ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ያለገደብ እንዲገልጹ የሚጠይቁ ናቸው፡፡
- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ መልስ ሲሰጡ በቃል ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹ የአንድምታዊ ጥቄዎች በመሆናቸው ከሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ መልስ ላይሰጥ ይችላል፡፡ በመሆኑም መልሶቻቸውን ሲቀበሉ ንግግራቸውን እንዲቀጥሉ ከማበረታታት ውጭ መልሳቸው ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን እንዳይገልጹ፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ምላሽ ተቀብለው ከጨረሱ በኋላ ማበረታቻ አስተያየት በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ካዳመጡት ምንባብ በቀጥታ የሚመለሱ የምርጫ ጥያቄዎች ናቸው፡፡
- ✓ ምንባቡን መሰረት አድርገው ለጥያቄዎቹ በጽሑፍ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎቹን ምላሽ ከተቀበሉ በኋላ የማስተካከያ ምላሽ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም የማጠቃለያ አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

### በቀቀኖችን ስሙን

በኢትዮጵያ በርካታ ብርቅዬ እንስሳት ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ሰባቱ ትልልቅ አጥቢ የዱር እንስሳት ሲሆኑ አስራ ሰባቱ ብርቅዬ አዕዋፍ ናቸው፡፡ ከነዚህ ብርቅዬ አዕዋፍ መካካል አንዱ ቢጫ ፊት በቀቀን በመሆኑ ኩራት ይሰማናል፡፡ እኛ አዕዋፍ ደማቅ ቀለማችንና ዝማሬያችን በአንድ ላይ ተዳምሮ በምንፈጥረው መልካም ስሜት፣ የሁሉንም ቀልብ የምንስብ የሰማይ ላይ ፈርጦች ነን፡፡

የእኛ በቀቀኖች ውበት የሰዎች ሁሉ መነጋገሪያ ነው፡፡ ገላችን እጅግ በተዋበና የተለያዩ ደማቅ ቀለማት ባሉት ላባ ያሸበረቀ ነው፡፡ እኛ በቀቀኖች በዓለም በርካታ ዝርያዎች አለን፡፡ ከዝርያዎቻችን መካከል መብረር የማይችሉም አሉ፡፡ በአመጋገባችን ከሁሉ በል እንስሳት እንመደባለን፡፡ ቆልማማ መንቆራችን ዓሳ፣ እንቁራሪት፣ አልቅት፣ ቀንድ አውጣ የመሳሰሉ የባህር እንስሳትን በቀላሉ ለመመገብ ይረዳናል፡፡ እንዲሁም ጥራጥሬና ፍራፍሬንም ያለችግር ለመብላት ያስችለናል፡፡ የላይኛው መንቆራችን እንደሰው ልጅ ጥፍር ታዳጊ ስለሆነ፣ ቁመቱ ሲረዝም እያኘክን እናሳጥረዋለን፡፡ በሁለት እግሮቻችን ላይ አራት አራት ጣቶች አሉን፤ ሁለቱ ከፊት ሁለቱ ደግሞ ከኋላ ይገኛል፡፡

እኛ የጫካ በቀቀኖች በአብዛኛው በሞቃታማ አካባቢ መኖርን እንመርጣለን፡፡ ነገር ግን አንዳንዶቻችን በቀዝቀዛና በረዷማ የአየር ጠባይ ውስጥ መኖር ይመቸናል፡፡ በቀቀኖች ጎጆዎቻችንን የዛፍ ግንድ በመቦርቦር፣ በዛፍ ቅርንጫፎች ላይ፣ በወንዝ ዳርቻዎችና በጉድጓድ ውስጥ ልንሰራ እንችላለን፡፡

ከአኗኗር ዘይቤያችን አንጻር በኅብረት መኖርን እንመርጣለን፡፡ ከ30 በላይ ሆነን፣ በአንድ ላይ እንኖራለን፡፡ ምግብ ፍለጋ፣ በአማካይ ከ20 እስከ 30 ሆነን በአንድ ላይ እንንቀሳቀሳለን፡፡ ወንድ በቀቀኖች የሕይወት አጋሮቻችንን ለማግኘት አስደሳች የሆኑ የዘፈንና የዳንስ ትርዒቶችን አናከናውናለን፡፡ የትዳር አጋር ከሆንን በኋላ በፍፁም አንለያይም፤ አብረን እንዘምራለን፤ አብረን እንመገባለን፡፡ ሴት በቀቀኖች እንቁላል ጥለን ስናቅፍ፣ ወንዱ የሚበላ ለቃቅሞ ይዞልን ይመጣል፡፡ ደስ እንላለን አይደል?

ከበቀቀን ተፈጥሯዊ ባህርያት ውስጥ የትኛውን የበለጠ ወደዳችሁት?

ከላይ ከቀረቡት በተጨማሪ ምን አይነት ባህርያት የሚኖራቸው ይመስላችኋል?

እኛ በቀቀኖች ጥሩ የማስታወስ ችሎታ ስላለን፣ በአካባቢያችን የሰማነውን ድምፅ መቅዳትና መልሰን ማሰማት የምንችል፣ ዕፁብ ድንቅ የወፍ ዝርያ ነን፡፡ ይሁን እንጂ፣ በርካታ ዝርያዎቻችን የመጥፋት አደጋ ተጋርጦብናል፡፡ መብረር የማይችሉትን ዝርያዎቻችንን የዱር ድመቶች እያደኑ ቁጥራችን እንዲመናመን አድርገውታል፡፡ ለሰው ልጆች መጫወቻ ሆነን ማገልገላችንም ለዝርያችን መጥፋት አንዱ መንስዔ ነው፡፡ በአካባቢያችን ያለውን ድምፅ መቅዳት በመቻላችን ሰዎች እንደመዝናኛ ስለሚቆጥሩን፣ በቤታቸው በማስገባት፣ በብረት ፍርግርግ ውስጥ እስከ ህይወታችን ፍፃሜ ያስቀምጡናል፡፡ ይህ ደግሞ አጋር ፈልገን እንዳንራባ ስለሚያደርገን፣ ለመመናመናችን ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡ እናሳዝናለን አይደል?

(የኢፌዴሪ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት፣ 2013 ዓ.ም.፣ ቴክሳይንስ መፅሄት፣ 7ኛ ዓመት 19ኛ ዕትም መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት የቀረበ)

ምዘና፡-

- ✓ ያዳመጡትን ምንባብ በቃል ሲገልጹ መከታተል፡፡

የተመረጠ ተግባር መልስ

ተግባር 2፡- ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. መ | 3. መ | 5. ሐ | 7. ለ |
| 2. ለ | 4. ለ | 6. ሐ | 8. መ |

ክፍል ሁለት፡- ንባብ

የትምህርቱ አቀራረብ፡-

መምህር!

በዚህ ክፍል ማንበብን ለማስተማር በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበ ‹‹የዱር እንስሳት ጥቅም›› የሚል ምንባብ ይገኛል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም ትምህርቱን እንደሚከተለው ያቅርቡ፡፡

## ቅድመ ንባብ

- ✓ ተማሪዎቹ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የሚሰሩት አንድ ተግባር ሲኖር ተግባሩን ተማሪዎች በቃል እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ሶስት ጥያቄዎች ሲኖሩ ምንባቡ የያዘውን ሀሳብ በማስመልከት ፍንጭ እንዲያገኙ የሚያደርጉ ጥያቄዎች ሲኖሩ በቃል መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ምላሽ ተከትለው ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አያስፈልግዎትም፡፡
- ✓ ምንባቡን ለማንበብ ዝግጁ ከሆኑ በኋላ በተናጠል ድምጽ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

## የንባብ ሒደት

- ✓ ተማሪዎች በተናጠል በለሆሳስ እያነበቡ መሆናቸውን እየተዘዋወሩ ያረጋግጡ፡፡

## አንብቦ መረዳት

- ✓ በአንብቦ መረዳት ስር ሶስት ተግባራት ሲኖሩ ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው እንደጨረሱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን እንደየ መመሪያዎቻቸው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር በሰንጠረዥ ውስጥ የሚገኝን የተጓደለ ሀሳብ እንዲያሟሉ የሚያዝ ጥያቄ ይገኛል፡፡
- ✓ የተጓደሉት ሀሳቦች የሚሞሉት ያነበቡትን ምንባብ መሰረት አድርገው ሲሆን የዱር እንስሳት የኗቸውን ልዩ ልዩ ጠቀሜታዎች እንዲገልጹ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ይህንን ጥያቄ ለመስራት አራት ጠቀሜታዎች ቀርበዋል፤ ተማሪዎቹም በእያንዳንዱ ሰንጠረዥ ስር የዱር እንስሳትን ጠቀሜታ እንዲገልጹ ተደርገዋል፡፡
- ✓ ለአራቱም ጠቀሜታዎች አንድ አንድ ምሳሌ የተሰጠ ሲሆን ምሳሌዎቹን መሰረት አድርገው ይሰሩ ዘንድ ከምንባቡ የወጡትን ተግባራት ተመርኩዘው ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ምሳሌዎቹን ካብራሩላቸው በኋላ ተማሪዎቹ ሰንጠረዡን ከነምሳሌዎቹ በደብተራቸው ላይ እንዲገለብጧቸውና መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ለጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ የሰጧቸውን መልሶች በመቀበልና የማስተካከያ ምላሾች በመስጠት ወደ ሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የቀረቡት አራት ጥያቄዎች ደግሞ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ሀሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ የሚያዙ አንድምታዊ ጥያቄዎች ናቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹ በአንድምታ የሚመለሱ እንደመሆናቸው ተማሪዎቹ የምንባቡን ሀሳብ በመገንዘብ ከቀደመ እውቀታቸው ጋር አዛምደው እንደሚመልሱ ይጠበቃል፡፡
- ✓ በመሆኑም ተማሪዎቹ የሚሰጧቸው ምላሾች እንዳላቸው የቀደመ እውቀት ወይም ልምድ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡
- ✓ እርስዎም በዚህ መሰረት ጥያቄዎቹን ተማሪዎቹ እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሶቻቸውን ሲቀበሏቸው ዋናው ትኩረትዎ ተማሪዎቹ የምንባቡን ሀሳብ ከልምዳቸው ጋር ማገናኘት መቻላቸው ላይ ነው፡፡
- ✓ በዚህም መሰረት ተማሪዎች ምላሻቸውን በቃል ሲሰጡ ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎቹን ምላሽ ተከትለውም አጠቃላይ አስተያየት ይስጧቸው፡፡

ተግባር 3፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር በቢጋር የሚሰራ ጥያቄ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ቀርቧል፡፡
- ✓ ቢጋሩ ተማሪዎች የሚያውቋቸውን የዱር እንስሳት በአይነት በአይነታቸው እንዲመድቡ የሚያዝ ነው፡፡
- ✓ ይህንን ጥያቄ ለመስራት ያመቻቸው ዘንድ በእያንዳንዱ የዱር እንስሳ አይነት ትይዩ ላይ አንድ አንድ እንስሳት ተጠቅሶላቸዋል፡፡
- ✓ የተሰጣቸውን ምሳሌ ካብራሩላቸው በኋላ ምሳሌውን በመንተራስ ተመሳሳይ እንስሳትን በአይነት በአይነታቸው እንዲሰድሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን ተቀብለው አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

ምዘና፡-

- ✓ የምንባቡን ሀሳብ ሲገልጹ መከታተል

ክፍል ሶስት፡- ቃላት

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ መስጠትን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ሁለት ተግባራት ቀርበዋል፡፡ ተግባራቱን በመጠቀም የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ተከትለው ትምህርቱን ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ ከአሁን በፊት በተማሩት መሰረት ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ የሚሰጡበትን መንገድ በምሳሌ አስደግፈው ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ በመቀጠል በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ተግባራት እንደ የመመሪያቸው በሚከተለው መልኩ ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ዓውዳዊ ፍቺ የሚሰጣቸው ቃላት በዓረፍተነገር ውስጥ ተካትተው ቀርበዋል፤ ቃላቱን ለመለየትም ተሰምረውባቸዋል፡፡
- ✓ ቃላቱ በዓረፍተነገሩ ውስጥ ያላቸውን ዓውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ እነዚህን ጥያቄዎችም ተግባር አንድን በሰሩበት መንገድ እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ለመልሳቸው እርማት በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር በቃላት ውስጥ የሚገኙ ሆህያት ቦታቸውን ሲቀያይሩ የሚያመጡትን የትርጉም ለውጥ እንዲያመለክቱ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ ይህንን ተግባር ለመስራት ያመቻቸው ዘንድ ምሳሌ ተሰጥቷቸዋል፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ጥያቄውን ከመስራታቸው በፊት ምሳሌውን በማሳየት ያብራሩላቸው፤ ቃላቱ ያጡትን የትርጉም ልዩነትም ያስመልክቷቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በደብተራቸው በመጻፍ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን ተቀብለው እርማትና ማጠቃለያ ከሰጡ በኋላ ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ፡-

- ✓ ቃላት በዓውድ ውስጥ እና ከዓውድ ውጭ ያላቸውን ፍቺዎች የሚያሳይ የሰንጠረዥ ቻርት

ምዘና፡-

- ✓ ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ ሲሰጡ መከታተል፡፡

ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በማውዳደርና ማነጻጸር ስልት አንቀጽ መጻፍን ይማራሉ፡፡ የትምህርቱ ዓላማ ይሳካ ዘንድ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሂደት ና ቅደም ተከተል በመከተል ትምህርቱን ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ በምዕራፍ ሁለት የተማሯቸውን በገለጻና በትረካ ስልት አንቀጽ መጻፍን በማስታወስ እንዲገልጹ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ምላሽ በመመርኮዝ ሁለቱን የአንቀጽ መጻፊያ ስልቶች የተመለከተ አጭር ክለሳ ያድርጉላቸው፤ የዚህ ክፍል ትምህርት የሆነውን የማወዳደርና የማነጻጸር ስልት ያስተዋውቋቸው፡፡
- ✓ የትምህርቱን ርዕስ በሰሌዳው ላይ በመጻፍ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበውን ማስታዎሻ በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ጽፈው ከጨረሱ በኋላ እንደ ክፍሉ ነባራዊ ሁኔታ ከ3 እስከ 5 ተማሪዎች ያሉባቸው ቡድኖችን በማደራጀት እንዲወያዩ ያድርጓቸው፤ በክፍል ውስጥ ማየት ወይም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በውይይቱና ማስታዎሻ በመጻፍ ተግባሩ ወቅት በምልክት ቋንቋ እና በንባብ የሚያግዟቸው ሰዎች መድቡላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ተወያይተው ከጨረሱ በኋላ የተወያዩበትን ሀሳብ በተወካዮቻቸው አማካኝነት በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሀሳባቸውን አቅርበው ከጨረሱ በኋላ የተማሪዎቹን ሀሳብ ተመርኩዘው በምሳሌዎች የተደገፈ ገለጻና ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ገለጻዎች ከጨረሱ በኋላ በዚህ ክፍል ስር የቀረቡትን ሶስት ተግባራት እንደሚያመችዎት በክፍል ስራ ወይም በቤት ስራ መልክ በቡድን ያሰሯቸው፡፡
- ✓ ተግባራቱን ለማሰራትም የሚከተለውን ሒደት ይከተሉ፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የቤትና የዱር እንስሳትን አንድነትና ልዩነት የሚገልጹበት ክብ ቢጋር ቀርቦላቸዋል፡፡

- ሁለቱ ክቦች በተገናኙበት ቦታ ላይ የሁለቱን አንድነት ፣ በማይገናኙባቸው ቦታዎች ደግሞልዩነታቸውን እንዲዘረዝሩ ያድርጓቸው፤ ይህንን ለማድረግም በምሳሌነት አንድነታውን የሚያሳይ አንድ ሀሳብ ፣ ልዩነታቸውን የሚያሳዩ ሁለት ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡
- ምሳሌዎቹን መነሻ በማድረግ ቢጋሩን እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡
- ሰርተው ከጨረሱ በኋላ በናሙናነት የሁለት ወይም የሶስት ቡድኖችን ስራ ያስቀርቡና ወደሚቀጥለው ተግባር ይሽጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ይህ ተግባር የሚሰራው የተግባር አንድ ስራቸውን በመመርኮዝ ነው፡፡
- መተግባር አንድ ያሟሏሉትን ቢጋር ተገቢዎቹን የመሸጋገሪያ ቃላት በመጠቀም አንቀጽ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎቹ አንቀጹን ጽፈው ከጨረሱ በኋላ በተግባር አንድ እድሉ ያልተሰጣቸው ሁለት ወይም ሶስት ቡድኖች በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡
- አቅርበው ከጨረሱ በኋላ ተገቢ ግብረ መልስ በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሽጋገሩ፡፡

ተግባር 3፡-

- በዚህ ተግባር ተማሪዎች የማወዳደርና የማነጻጸር ስልትን ተጠቅመው አንቀጽ እንዲጽፉ ታዘዋል፡፡
- በቀደሙት ተግባራት በተለማመዱት መሰረት የተሰጣቸውን መንደርደሪያ ሀሳቦች ወይም የራሳቸውን ሌላ ሀሳብ ተጠቅመው አንቀጹን እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ጽፈው ከጨረሱ በኋላ ቀደም ሲል እንዳደረጉት የተመረጡ አንቀጾችን በክፍል ውስጥ ያስቀርቧቸው፡፡

- ✓ በመጨረሻም ተገቢ ግብረ መልሶች እና አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት አንቀጽ ሊያስጽፉ የሚችሉ ሀሳቾችን የያዘ ቢጋር ወይም ቻርት፡፡

ምዘና

- ✓ በማወዳደርና ማነጻጸር ስልት አንቀጽ ሲጽፉ መከታተል፡፡

ክፍል አምስት፡- ሰዋስው


የትምህርቱ አቀራረብ

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን ይማራሉ፡፡ ትምህርቱን በሚገባ ለማቅረብ ይረዳዎት ዘንድ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ይከተሉ፡፡

- ✓ በመጀመሪያ ቀደም ባሉት ክፍሎች የተማሯቸውን አስታውሰው ስለግስ ምንነት የሚያውቁትን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶች የሚለውን ርዕስ በሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸው፡፡
- ✓ ከዚያም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበውን ማስታዎሻ ያስጽፏቸው፡፡
- ✓ ማስታዎሻውን ጽፈው እንደጨረሱ ከማስታዎሻውና ከተሰጡት ምሳሌዎች በመነሳት ስለ ተሻጋሪ ግሶች እና የማይሻገሩ ግሶች ያገኙትን ግንዛቤ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ የተወሰኑ ተማሪዎችን ምላሽ ከተቀበሉ በኋላ በምሳሌ የተደገፉ ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡

- ✓ ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን ሲያስረዷቸው ይዘቱ እንዳይወሳሰብባቸው ጥንቃቄ ያድርጉ፡፡
- ✓ ይህን ማለት ግሶችን በጠቅላላ ‹‹ተሻጋሪና የማይሻገሩ›› ብለው እንዳያጠቃልሏቸው አቅማቸውን ባገናዘበ መልኩ ተጨማሪ ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ይህንን ጉዳይ ግልጽ ለማድረግ የሚከተለውን አጭር ማስታዎሻ ይጠቀሙ፡፡

ግሶች በዓረፍተነገር ውስጥ በማሰሪያ አንቀጽነት የሚያገለግሉ ሲሆን የሚያስሩትም ድርጊትንና መሆንን የሚያመለክቱ ጉዳዮችን ነው፡፡ ድርጊትን የሚያመለክቱት ግሶች የድርጊት ግስ ሲባሉ መሆንንና መኖርን የሚያመለክቱት ግሶች ደግሞ የመሆን ግስ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶች ተብለው በሁለት የሚከፈሉት የድርጊት ግሶች ናቸው፡፡ ይህንን ሀሳብ በሚከተለው ቻርት መመልከት ይቻላል፡፡




- ✓ ከላይ የቀረበውን ማስታዎሻ መሰረት በማድረግ በተማሪዎቹ አቅም ልክ ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶች በድርጊት ግስ ስር የሚመደቡት እንደሆኑ ያስረዷቸው፡፡
- ✓ ይዘቱን በዚህ መንገድ በቀላሉ ከገለጹላቸው በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ በቀረቡት ሶስት ተግባራት ውስጥ የተካተቱትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ልዩ ልዩ ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን የያዘ ሰንጠረዥ የቀረበ ሲሆን የግሶቹን አይነት የሚገልጹባቸው ክፍት ቦታዎች ቀርበውላቸዋል፡፡
- ✓ ይህንን ተግባር በየቃላቱ ትይዩ ከቀረቡት ክፍት ቦታዎች የግሱን አይነት በሚገልጸው ቦታ የ‹‹√›› ምልክት በማስቀመጥ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሶቻቸውን ተቀብለው እርማት በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ልዩ ልዩ የድርጊት ግሶችን የያዙ ዓረፍተነገሮች የቀረቡላው ሲሆን ግሶቹን በማውጣት የሚሻገር ወይም የማይሻገር መሆናቸውን ለይተው እንዲገልጹ ተጠይቀዋል
- ✓ ጥያቄዎቹን ለመስራት ያመቻቸው ዘንድ ከጥያቄዎቹ አስቀድሞ ሁለት ምሳሌዎች ቀርበዋል፤ ምሳሌዎቹን ካብራሩላቸው በኋላ ጥያቄዎቹን በጽሑፍ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን በመቀበል እርማት ሰጥተው ወደ ቀጣዩ ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 3፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶች የቀረቡ ሲሆን ተማሪዎች አይነታቸውን በመግለጽ ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩባቸው ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ በዚህም መሰረት ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ለመልሶቻቸው ማስተካከያና ማጠቃለያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የግስ አይነቶችን ለይቶ የሚያሳይ ቻርት

ምዘና፡-

- ✓ ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን ሲለዩ መከታተል፡፡

የተመረጡ ተግባራት መልሶች፡-

ተግባር 1፡-

በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ የሚገኙትን ግሶች ተሻጋሪ ወይም የማይሻገሩ ግሶች መሆናቸውን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

ሀ. የማይሻገር    ሐ. ተሻጋሪ    ሠ. ተሻጋሪ    ሰ. የማይሻገር

ለ. የማይሻገር    መ. ተሻጋሪ    ረ. ተሻጋሪ

ተግባር 2፡-

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ላይ ያሉት ግሶች ተሻጋሪ ወይም የማይሻገሩ መሆናቸውን ለይታቸውሁ አመልክቱ፡፡

ሀ. ግስ - ገሰጻች    የግስ አይነት - ተሻጋሪ

ለ. ግስ - ጻፈ    የግስ አይነት - ተሻጋሪ

ሐ. ግስ - ተደሰተች    የግስ አይነት - የማይሻገር

መ. ግስ - ትወዳለች    የግስ አይነት - ተሻጋሪ

ሠ. ግስ - መጣች    የግስ አይነት - የማይሻገር

ረ. ግስ - አጥለቀለቀው    የግስ አይነት - ተሻጋሪ

ሰ. ግስ - ተክዛለች    የግስ አይነት - የማይሻገር

# አማርኛ

(፫) ክፍል

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# ባህላዊ ጨዋታዎች

(18 ክፍለ ጊዜ)

የምዕራፉ ዓላማዎች፡ ይህንን ምዕራፍ ተምረው ከጨረሱ በኋላ፡-

- ✓ ባህላዊ ጨዋታዎችን ይጫዎታሉ፡፡
- ✓ የስርዓተ ነጥብን አገባብና ትርጉም ተረድተው ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ ባለብዙ ቀለም ቃላትን ያጣምራሉ፡፡
- ✓ ደብዳቤ ይጽፋሉ፡፡
- ✓ የአሁን ጊዜ ግስን ይጠቀማሉ፡፡

ይዘት፡-

- ✓ አዳምጦ በባህላዊ ጨዋታዎች መሳተፍ
- ✓ ስለተለያዩ ጨዋታዎች አንብቦ ዘገባ ማቅረብ
- ✓ ደብዳቤ መጻፍ
- ✓ የአሁን ጊዜን ግስ ተጠቅሞ ዓረፍተነገር መመስረት

ክፍል አንድ፡ ማዳመጥና መናገር፡

## ባህላዊ ጨዋታዎችና አጨዋወታቸው

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

ቀጥሎ የማዳመጥና የመናገር ክሒልን ለማስተማር ‹‹ባህላዊ ጨዋታዎችና አጨዋወታቸው›› የሚል ምንባብ ቀርቧል፡፡ ትምህርቱን በሚከተሉት ቅደም ተከተሎችና አቀራረቦች ያከናውኑ፡፡

### ቅድመ ማዳመጥ

ተግባር፡-

- ✓ ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት በቅድመ ማዳመጥ ተግባር ስር ያለውን ሰንጠረዥ ተማሪዎቹ እንዲያዘጋጁ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሰንጠረዡ ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት እነሱም የማውቀው፣ ማወቅ የምፈልገው እና ያወቅኩት የሚሉ ናቸው፡፡
- ✓ ምንባቡን ከማንበብዎት በፊት ከአሁን በፊት የሚያውቋቸውን እና ማወቅ የሚፈልጓቸውን የባህላዊ ጨዋታ አይነቶች እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በተጨማሪም በመማሪያ መጽሐፉ የማዳመጥ ተግባር ስር የሚገኘውን ሰንጠረዥ እንዲያዘጋጁ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ በሰንጠረዡ ውስጥ ሶስት የባህላዊ ጨዋታ አጨዋወት አይነቶችን እንዲገልጹባቸው ክፍት ቦታዎች ቀርበውላቸዋል፡፡
- ✓ ሰንጠረዡን ካዘጋጁ በኋላ እርስዎ ሲያነቡ ተማሪዎቹ ማስታዎሻ እየያዙ እንዲያዳምጡ ያሳስቧቸው፡፡ በክፍሉ ውስጥ ዓይነ ስውር ተማሪ ካለ በሁለቱ ሰንጠረዦች የቀረቡትን ሀሳቦች የሚያነብላቸውና አጣማጅ የሚሆንላቸው ተማሪ ይመድቡላቸው፡፡

## የማዳመጥ ሂደት

ተግባር፡-

- ✓ የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱን ከጨረሱ በኋላ ተማሪዎች ማስታዎሻ እየያዙ እንዲያዳምጡ በማዘዝ ለሁሉም ተማሪዎች በሚሰማ ድምፅ ረጋ ብለው ያንብቡላቸው፡፡

በክፍል ውስጥ መስማት የተሳነው ተማሪ ካለ ምንባቡን በምልክት ቋንቋ የሚያሳየው ሰው ያዘጋጁለት ወይም በከንፈር በማንበብና መሰል ቴክኒኮች እንዲጠቀሙ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡

- ✓ በምንባቡ መሀል ላይ ያሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ በትክክል እያዳመጡ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ✓ በተጨማሪም ማንበብ ከመጀመርዎት በፊት እንዲያዘጋጁ ባዘዟቸው ሰንጠረዥ ውስጥ ጨዋታዎችን በዓይነት እንዲመድቡ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ እየተከታተሉዎት መሆናቸውን ካረጋገጡና ማስታዎሻ እየያዙ ሰንጠረዡን እንዲሞሉ ካደረጓቸው በኋላ ምንባቡን ካቋረጡበት ቦታ ይቀጥሉ፡፡
- ✓ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙት ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን በተመለከተ ተማሪዎች የሚጠይቁዎት ከሆነ የጨዋታዎቹን ምንነት በአጭሩ ቀጣዩን ማስታዎሻ በማየት ይግለጹላቸው፡፡

| |
|---|
| ጊጤ ጨዋታ፡- ሹል ዘንግ ወይም ጦር እየወረወሩ ኢላማ የመውጋት ውድድር |
| ቅምጦሽ፡- በጀርባ ታዝሎ ኳስ አርቆ መወርወርና ተጋላቢው ወርዋሪውን እንዳዘለ ሮጦ የመቅለብ ጨዋታ |
| ሽምጥ፡- በኳስ ከርቀት ያጎነበሰን ሰው አነጣጥሮ የመምታት ጨዋታ |
| ጮቤ፡- እየዘለሉ በሁለት እግር መቀመጫን የመምታት ጨዋታ |
| ማጋፈት፡- ተረከዝ ላይ ቁጢጥ ብሎ በመቀመጥ የመዝለል ጨዋታ |
| እንኳል እንኳል፡- ቁራጭ እንጨትን በዱላ የመቅላት (የመምታት) ጨዋታ |

## አዳምጦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበውላቸው እንደጨረሱ የአዳምጦ መረዳት ተግባራትን እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር፡-

- ✓ በመጀመሪያ የማውቀው፣ ማወቅ የምፈልገው እና ያወኩት በሚለው ሰንጠረዥ ውስጥ የጻፉትን መልስ ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ በዚህም የትኛውን የጨዋታ አይነት ማወቅ ፈልገው የትኛውን እንዳወቁና እንዳላወቁ እንዲገልጹ ማድረግ ይችላሉ፡፡
- ✓ በመቀጠልም በማድመጥ ጊዜ የያዙትን ማስታዎሻ መሰረት አድርገው በሶስቱ የባህላዊ ጨዋታ አይነቶች የሚመደቡትን የጨዋታ አይነቶች እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በሁለቱ ሰንጠረዦች ያሉትን ጥያቄዎች አሰርተው ከጨረሱ በኋላ በአዳምጦ መረዳት ተግባር ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ✓ በዚህ ተግባር አምስት ጥያቄዎች ሲኖሩ በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡
- ✓ በተግባሩ የቀረቡት ጥያቄዎች ሶስት ምድቦች ሲኖሯቸው ሁለቱ ጥያቄዎች (‹ለ› እና ‹ሐ›) በቀጥታ ከምንባቡ ሀሳብ የሚመለሱ፣ አንዱ (‹ሀ›) ከምንባቡ ውጭ አንድምታዊ ምላሽ የሚፈልግ፣ እንዲሁም ቀሪዎቹ ሁለት ጥያቄዎች (‹መ› እና ‹ሠ›) ባዳመጡት ምንባብ ውስጥ የቀረበውን የልጆች ጨዋታ በተግባር እንዲያከናውኑ የሚጠይቁ ናቸው፡፡
- ✓ እነዚህን ጥያቄዎች እንደጥያቄዎቹ ባህርያት በቃልና በተግባር ያሰሯቸው፡፡
- ✓ ከምንባቡ ለወጡት ሁለት ጥያቄዎች እና ከምንባቡ ውጭ በአንድምታ ለሚመለሰው አንድ ጥያቄ መልሳቸውን በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ እንዲሁም በተግባር ለሚሰሩት ሁለት ጥያቄዎች ‹‹ኳስ አበደች›› የተሰኘውን ባህላዊ የልጆች ጨዋታ በክፍል ውስጥ የአካል እንቅስቃሴውን ብቻ እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡

- ✓ በመቀጠልም በእረፍት ሠዓታቸው፣ በትምህርት ቤቱ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታ በተግባር እንዲጫወቱ ያበረታቷቸው፣በተቻለ መጠን በአካል ተገኝተውም ይከታተሏቸው ።
- ✓ በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው መልኩ በፈርጅ በፈርጃቸው ከፋፍለው ካሰሯቸው በኋላ የማጠቃለያ አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት።

## ባህላዊ ጨዋታዎችና አጨዋወታቸው

ኢትዮጵያ ሀገራችን የተለያዩ ብሄረሰቦች ሀገር ናት። በዚህም የተነሳ የአያሌ ባህላዊ ዕሴቶች ባለቤት ልትሆን ችላለች። ከነዚህ ባህላዊ ዕሴቶች መካከል በሀገራችን ልዩ ልዩ አካባቢዎች በልጆችና በአዋቂዎች የሚዘወተሩት ጨዋታዎች ይገኙበታል። ለአብነት ያህልም፡- ኪሳራ፣ ቀልሞ ጭጭ፣ እንኳል እንኳል፣ ዙሮ ገብ፣ ውሻ ውሾሽ፣ ገና የሚባሉትን ግልፅ ሕግ ያላቸው የቡድን ጨዋታዎች መጥቀስ ይቻላል።

በሀገራችን ልዩ ልዩ አካባቢዎች በአብዛኛው በአዋቂዎች የሚዘወተሩት ጨዋታዎች እንደሚከተለው በዓይነት በዓይነት ተከፋፍለው ቀርበዋል፡-

ሀ. ኃይልንና ልምምድን የሚጠይቁ፡- ፈረስ ግልቢያ፣ ውሀ ዋና፣ ዒላማ ተኩስ፣ አውሬ አደን፣ ጉግስ ጨዋታ፣ ዘንግ ውርወራ፣ ጊጤ ጨዋታ (ሹል ዘንግ ወይም ጦር እየወረወሩ የመውጋት ውድድር)፣ ገና ጨዋታ ፣ ምክት፣ ቅምጦሽ፣ ሽምጥ፣ ትግል፣ እርግጫ (የእግር ቦክስ)፣ ዝላይ፣ ሩጫ፣ ጅራፍ ግርፊያ፣ ጮቤ (እየዘለሉ በሁለት እግር መቀመጫን መምታት/፣ ጭፈራ፣/ውዘዋዜ፣ እስክስታ/፣ ማጋፊት…

ለ. ማሰላሰልንና ቅልጥፍናን የሚጠይቁ፡- ሠንጠረዥ፣ ገበጣ፣ አካንዱራ/የጦርነት ምሳሌ/

ሐ. የተፈጥሮ ስጦታን ወይም ዝንባሌን የሚጠይቁ፡- በገና መደርደር፣ ማሲንቆ መምታት፣ ክራር መግረፍ፣ ዋሽንት መንፋት እና እንቢልታ መንፋት

እነዚህ ጨዋታዎች የየራሳቸው የአጨዋወት ህግና ደንብ አላቸው፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ጨዋታዎች ‹‹ኳስ አበደች/ምክት››የሚባለውን ጨዋታ አጨዋወት እንደሚከተለው እናያለን፡፡ በመጀመሪያ በክር ጠብቃ የተሰፋችና የከረረች ኳስ ትዘጋጃለች፡፡ ከዚያም ሁሉም ተጫዋቾች ባሉበት አንዱ ኳሷን በመካከል ያነጥራታል፡፡ ኳሷን ቀድሞ የቀለባት ተጫዋች መቺ ሆኖ ይዘጋጃል፡፡ ቀጥሎም አንጣሪ የነበረው ተጫዋች፣ እጆቹን አገጣጥሞ፣ ከግንባሩ ላይ መክቶ፣ ‹‹ያውልህ›› በማለት፣ተመቺ ለመሆን ይዘጋጃል፡፡ መቺው አንጣሪውን ከመታው በኋላ ኳሷ ነጥራ፣ ከመቺው እጅ የገባች እንደሆነ፣ መካቹን ደግሞ ይመታዋል፡፡ ነገር ግን መካቹ ወይም ሌላ ተጫዋች ኳሷን ከያዘ፣ በመጀመሪያ መቺ የነበረው ተጫዋች ተራውን መካች ይሆንና ጨዋታው ይቀጥላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ‹‹ኳስ አበደች ›› እያሉ፣ እስኪደክማቸው ድረስ ይጫወታሉ፡፡

በአጠቃላይ የሀገራችን ባህላዊ ጨዋታዎች፣ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከታወቁትና ከሚዘወተሩት ተወዳጅ ዘመናዊ ጨዋታዎች ጋር የሚመሳሰሉበት በርካታ ገጽታ አላቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ ከላይ አጨዋወቱ በዝርዝር የቀረበው ‹‹ኳስ አበደች››የሚባለው ጨዋታ፣ ‹‹ቤዝ ቦል›› በመባል ከሚታወቀው የፈረንጆች ጨዋታ ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል፡፡ በተጨማሪም ‹‹ገና›› የሚባለው ጨዋታ፣ ‹‹ሆኪ›› ከሚባለው ጨዋታ ጋር አንድነት አለው፡፡ በመሆኑም፣ ባህላዊ ጨዋታዎቻችን እንዳይዘነጉ ብናደርጋቸውና ብናዘምናቸው በርካታ ጠቀሜታ ሊያስገኙ ይቻላሉ፡፡

(የብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀል ስብስብ ሥራዎች 2007 ዓ.ም ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

ምዘና፡-

- ✓ ያዳመጡትን ምንባብ በቃል ሲገልጹና በተግባር ሲያከናውኑ መከታተል፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያዎች

- ✓ ‹‹ኳስ አበደች›› የተባለውን ባህላዊ የልጆች ጨዋታ ለመጫወት የሚጠቅም በወረቀት፣ በጨርቅ ወይም በላስቲክ የተሰራ ኳስ፡፡

ክፍል ሁለት፡- ንባብ

የትምህርቱ አቀራረብ፡-

መምህር!

በዚህ ክፍል ማንበብን ለማስተማር በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበ ‹‹ባህላዊ የልጆች ጨዋታ›› የሚል ምንባብ ይገኛል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም ትምህርቱን እደሚከተለው ያቅርቡት፡፡

## ቅድመ ንባብ

- ✓ ተማሪዎቹ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የሚሰሩት አንድ ተግባር ሲኖር ተግባሩን በቃል ያሰሯቸው፡፡

ተግባር፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ሶስት ጥያቄዎች ሲኖሩ ምንባቡ የያዘውን ሀሳብ በማስመልከት ፍንጭ እንዲያገኙ የሚያደርጉ ናቸው፤ ጥያቄዎቹን በቃል መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹም ስዕሉን በመመልከት የምንባቡን ሀሳብ መገመትን፣ የሚያውቋቸውን ጨዋታዎች መግለጽን እና ጨዋታዎች ያሏቸውን ጠቀሜታዎች መግለጽን የሚጠይቁ ናቸው፡፡

- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በቃል መልስ ሲሰጡ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አይጠበቅብዎትም፡፡
- ✓ በተጨማሪም በመማሪያ መጽሐፉ የንባብ ጊዜ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን የሚያሰፍሩበት ሰንጠረዥ ይገኛል፡፡
- ✓ ምንባቡን ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት ሰንጠረዡን በደብተራቸው እንዲያዘጋጁ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ምንባቡን ድምጽ ሳያሰሙ እንዲያነቡና እንግዳ ቃላት ሲገጥሟቸው ‹‹ቃል›› በሚለው የሰንጠረዡ ክፍል እንዲጽፏቸው ያድርጉ፡፡

## የንባብ ሂደት

- ✓ ተማሪዎች በተናጠል ድምጽ ሳያሰሙ እያነበቡ መሆናቸውን እየተዘዋወሩ ያረጋግጡ፡፡
- ✓ የሚገጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት እየጻፉ መሆናቸውንም ይከታተሉ፤ በክፍል ውስጥ ዐይነ ስውር ተማሪ ካለ ምንባቡን የሚያነብለትና አዳዲስ ቃላትን በሰንጠረዥ የሚጽፍለት ሰው ይመድቡለት፡፡

## አንብቦ መረዳት

- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ የአንብቦ መረዳት ክፍል ሶስት ተግባራት ይገኛሉ፡፡
- ✓ ምንባቡን አንብበው እንደጨረሱ በተግባራቱ መመሪያዎች መሰረት ጥያቄዎቹን እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር በጽሑፍ የሚመለሱ ስድስት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹ በምንባቡ ሀሳብ መሰረት እና በአንድምታ የሚመለሱ ናቸው፡፡
- ✓ በቀጥታ በምንባቡ ሀሳብ መሰረት የሚመለሱት ጥያቄዎች በተራ ቁጥር 1፣ 3 እና 5 የቀረቡት ሲሆኑ በአንድምታ የሚመለሱት ደግሞ በጥያቄ ቁጥር 2፣ 4 እና 6 የቀረቡት ናቸው፡፡

- ✓ በመሆኑም ከምንባቡ በቀጥታ ለሚመለሱት ጥያቄዎች በምንባቡ ሀሳብ ተገድበው መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ እንዲሁም ከምንባቡ ውጭ ላሉት አንድምታዊ ጥያቄዎች ያለምንም ገደብ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጡ ምላሾች አንድ አይነት ላይሆኑ ይችላሉ፤ ተማሪዎች እንዳላቸው የቀደመ እውቀት የተለያዩ መልሶች ሊሰጡ ስለሚችሉ ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን በጽሑፍ መልስ ከሰጡ በኋላ መልሶቻቸውን ተቀብለው ተገቢ የቃል ግብረ መልስ እና እርማት በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፦

- ✓ በዚህ ተግባር የቀረበው ጥያቄ በቢጋር የቀረበ ሲሆን በጽሑፍ የሚመለስ ነው፡፡
- ✓ ጥያቄው ባደመጡት ምንባብ የተገለጹትን በአጫሩ እና በረጅሙ የሚዜሙ ባህላዊ የልጆች ጨዋታዎችን በአይነታቸው እንዲዘረዝሩ ይጠይቃል፡፡
- ✓ ይህንን ጥያቄ ከመስራታቸው በፊት በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበውን የቢጋር ሰንጠረዥ በደብተራቸው እንዲያዘጋጁ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በሁለቱ የባህላዊ ጨዋታዎች አይነት የሚመደቡትን እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ጽፈው ከጨረሱ በኋላ መልሶቻቸውን በመቀበልና እርማት በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 3፦

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ሶስት ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡
- ✓ ከሶስቱ ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱ ቋንቋ ነክ ጥያቄዎች ሲሆኑ አንዱ ጥያቄ ደግሞ የተግባር ጥያቄ ነው፡፡

- ✓ ቋንቋ ነክ ከሆኑት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ በምንባቡ ውስጥ ያሉትን የስርዓተ ነጥብ አይነት እንዲያወጡና አገልግሎቶቻቸውንም እንዲገልጹ የሚጠይቅ ሲሆን ቀሪው አንድ ጥያቄ ደግሞ ስለሚያውቁት አንድ ጨዋታ አተገባበር በዘገባ መልክ እንዲጽፉ የሚጠይቅ ነው፡፡
- ✓ እንዲሁም አንዱ የተግባር ጥያቄ የሚያውቁትን አንድ ጨዋታ በክፍል ውስጥ በተግባር እንዲጫወቱ የሚያዝ ጥያቄ ነው፡፡ በመሆኑም፣ በተማሪዎቹ የሚቀርበው ጨዋታ በክፍል ውስጥ ለማቅረብ የሚመች መሆኑን አረጋግጠው፣ መረባበሽን በማይፈጥር መልኩ ተግባሩን ያስተግብሩ፡፡
- ✓ በጥያቄዎቹ ትእዛዝ መሰረት ለጥያቄዎቹ ምላሽ ከሰጡና በተግባር ካሳዩ በኋላ ለመልሳቸው እርማትና ለተግባራቸው አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

ምዘና፡-

- ✓ የምንባቡን ሀሳብ ሲገልጹና በተግባር ሲያሳዩ መከታተል

ክፍል ሶስት፡- ቃላት

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን መነጠልና ማጣመርን እና የአንቀጽ ክፍት ቦታዎች ማሟላትን ይማራሉ፡፡ ትምህርቱን ለማቅረብ ያግዝዎት ዘንድ በመማሪያ መጽሐፉ ሁለት ተግባራት ቀርበዋል፡፡ ተግባራቱን በመጠቀም ትምህርቱን በሚከተለው መንገድ ያቅርቡላቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የተነጣጠሉ ቃላትን እንዲያጣምሩ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡

- ✓ ጥያቄዎቹን ከማሰራትዎ በፊት ቃላትን ነጥሎና አጣምሮ ማንበብን የተመለከተ አጭር ክለሳ ያድርጉላቸው፤ በተግባሩ መጀመሪያ የሚገኙትን ምሳሌዎች ሰርተው ያሳይዋቸው፡፡
- ✓ በመቀጠል ጥያቄዎቹን በደብተራቸው እንዲጽፉ ካደረጉ በኋላ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ መልሳቸውን ተከትለው እርማት ከሰጡ በኋላ ወደሚቀጥለው ተግባር ይቀጥሉ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የተጓደሉ ቃላት ያሉበት አንቀጽ ቀርቧል፤ ከአንቀጹ በላይም በተጓደሉት የአንቀጹ ቦታዎች የሚገቡ ቃላት አሉ፡፡ ተማሪዎቹ እነዚህን ቃላት በክፍት ቦታዎቹ እንዲያስገቡ ተጠይቀዋል፡፡
- ✓ አንቀጹን በደብተራው እንዲጽፉና ክፍት ቦታዎቹን እንዲያሟሉ ያድርጓቸው
- ✓ ተማሪዎቹ መልስ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሶቻቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም የመልስ እርማት እና የማጠቃለያ ሀሳብ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ፡-

- ✓ የተነጣጠሉና የተጣመሩ ቃላትን የያዘ ፍላሽ ካርድ ወይም የሰንጠረዥ ቻርት

ምዘና፡-


- ✓ ቃላትን በሚገባ ማጣመራቸውንና አንቀጹን መሟላታቸውን ማረጋገጥ፡፡

ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ደብዳቤ መጻፍን ይማራሉ፡፡ የትምህርቱ ዓላማ ይሳካ ዘንድ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሂደትና ቅደም ተከተል በመከተል ትምህርቱን ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ ስለደብዳቤ የሚያውቁትን ነገር ይጠይቋቸውና መልሶቻቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኘውን ማስታዎሻና ምሳሌ ያጽፏቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ጽፈው እንደጨረሱ በምሳሌ የተደገፈ ገለጻና ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ትምህርቱን ተጨባጭ በሆነ አቀራረብ ለማስተማር ይረዳዎት ዘንድ የደብዳቤን ውስጣዊ ክፍሎች እና በፖስታው ፊትና ጀርባ የሚቀርቡትን ጉዳዮች የሚያሳዩ ቻርቶችን ይጠቀሙ፡፡
- ✓ የደብዳቤን ውስጣዊ ክፍሎች በቻርት ለማዘጋጀት ይረዳዎት ዘንድ በመማሪያ መጽሐፉ ያለውን ናሙና ይጠቀሙ፡፡ እንዲሁም የፖስታውን ውጫዊ መዋቅር በቻርት ለማዘጋጀት የፖስታው ገጽታ ቀጥሎ ቀርቦልዎታል፡፡



- ✓ ከላይ የቀረበውን የፖስታ ናሙና እና በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበውን የደብዳቤ ክፍሎች በቻርት መልክ አዘጋጅተው ትምህርቱን በተጨባጭ ያቅርቡት
- ✓ በመቀጠልም በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ሁለት ተግባራት እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በተግባሩ ስር አምስት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን፣ በጽሑፍ የሚመለሱ የአጭር መልስ መጻፍ ጥያቄዎች ናቸው፡፡
- ✓ ከአምስቱ ጥያቄዎች አራቱ (ከ‹ሀ› እስከ ‹መ›) የተለያዩ የደብዳቤ ክፍሎች የተመለከቱ ሲሆኑ ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ እንዲሁም ቀሪው አንድ ጥያቄ (‹ሠ›) የሰላምታ ደብዳቤ እንዲጽፉና ለተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያዛል፡፡
- ✓ በዚህም መሰረት ተማሪዎቹ ለአንድ ጓደኛቸው ደብዳቤ እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ ደብዳቤውን ጽፈው እንደጨረሱ ለሶስት ወይም አምስት ተማሪዎች ዕድል በመስጠት ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሁሉም ተማሪዎች የደብዳቤ ክፍሎችን በሚገባ ማካተታቸውንና ሀሳቸውን በደብዳቤው መግለጻቸውን እየገመገሙ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም የማጠቃለያ ሀሳብ በመስጠት ወደ ቀጣዩ ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ስድስት የስርዓተ ነጥብ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን ከማሰራትዎት በፊት ስርዓተ ነጥብን የተመለከተ አጭር ክለሳ ያድርጉላቸው፡፡

- ✓ በመቀጠልም በደብተራቸው ላይ በመጻፍ መልስ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ መልሶቻቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ መልስ ሰጥተው ከጨረሱ በኋላ ለመልሶቻቸው እርማት ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም የማጠቃለያ ሀሳብ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ የደብዳቤ ውስጣዊ ክፍሎችን የያዘ ቻርት
- ✓ የፖስታን ገጽታ የሚያሳይ ቻርት

ምዘና

- ✓ ደብዳቤ ሲጽፉና ስርዓተ ነጥቦችን በትክክለኛ ቦታቸው ሲጠቀሙ መከታተል፡፡

ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

የትምህርቱ አቀራረብ

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ስለአሁን ጊዜ ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ ይረዳዎት ዘንድ በመማሪያ መጽሐፉ ማስታዎሻና መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ ማስታዎሻውንና ተግባራቱን በመጠቀም ትምህርቱን እንደሚከተው ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ ግስን በተመለከተ የሚያውቁትን እንዲገልጹ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም የግስ ጊዜን የሚመለከተውን ማስታዎሻ ያስጽፏቸው፡፡
- ✓ ጽፈው እንደጨረሱ ምሳሌዎቹን ተጠቅመው ገለጻና ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኙትን ሁለት ተግባራት ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር በሀላፊ ጊዜ እና በትንቢት ጊዜ የቀረቡ ልዩ ልዩ ዓረፍነገሮች ቀርበውላቸዋል፤ ግሶቹን ወደ አሁን ጊዜ እንዲቀይሩ ታዘዋል፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን ለመስራት ያመቻቸው ዘንድ ከጥያቄዎቹ በፊት የቀረቡትን ምሳሌዎች አብራርተው በመስራት ያሳዩዋቸው፡፡

- ✓ በመቀጠልም ጥያቄዎቹን በደብተራው ላይ በመጻፍ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ መልስ ሰጥተው ከጨረሱ በኋላ መልሶቻቸውን በመቀበል እርማት ሰጥተው ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ግሶች ቀርበውላቸው፤ ወደ አሁን ጊዜ በመቀየር በቀየሯቸው ግሶች ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ታዘዋል፡፡
- ✓ ከጥያቄዎቹ በፊት ምሳሌዎች ቀርበዋል፡፡ ምሌዎቹን አብራርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ በመጻፍ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ መልስ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ ምላሻቸውን በመቀበል እርማት ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ማጠቃለያ በመሥጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ ልዩ ልዩ የአሁን ጊዜ ግሶችን የያዙ ዐረፍተ ነገሮች ቻርት

ምዘና፡-

- ✓ ግሶችን ወደ አሁን ጊዜ ሲቀይሩ መከታተል

# አማርኛ

(፩) ክፍል

# ምዕራፍ አስር ስነቃል

(18 ክፍለ ጊዜ)

የምዕራፉ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ ስነቃሎችን አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- ✓ ራሳቸውን መግለፅ ይለማመዳሉ፡፡
- ✓ አንድ ታሪክ በማንበብ ታሪኩን ይገልጻሉ፡፡
- ✓ የራሳቸውን ህይወት ታሪክ ይጽፋሉ፡፡
- ✓ የስነጽሁፍ አላባውያንን ይገልፃሉ፡፡

ይዘት

- ✓ በማዳመጥና ከራሳቸው ልምድ በመነሳት ታሪክ መተረክ
- ✓ ታሪክን አንብቦ በቃል መተረክ
- ✓ የሕይወት ታሪክ መጻፍ
- ✓ ቃልን መነጠልና ማጣመር
- ✓ ርቱዕና ኢ-ርቱዕ ተሳቢዎችን መለየት

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

## ዕንቆቅልሽ

የትምህርቱ አቀራረብ፡-

መምህር!

በዚህ ክፍል ስነቃሎችን አዳምጦ ምላሽ መስጠትን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማስተማር ይረዳዎት ዘንድ ‹‹ዕንቆቅልሽ›› የሚል ምንባብ ቀጥሎ ቀርቦልዎታል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም ትምህርቱን ለማቅረብ ቀጥሎ ያለውን የመማር ማስተማር ሒደት ይከተሉ፡፡

### ቅድመ ማዳመጥ፡-

- ✓ ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት በቅድመ ማዳመጥ ተግባር ስር ያሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲሰሯቸው ያድርጉ፡፡

ተግባር፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የሚነበብላቸው ምንባብ ስለምን እንደሚያወሳ ቀድመው እንዲገምቱ የሚያደርጓቸውን ሁለት ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹ፣ ስለዕንቆቅልሽና አጨዋወቱ የሚያውቁትን እንዲናገሩና፣ እንዲሁም ስለስነቃል ምንነት የሚጠይቁ ናቸው፡፡
- ✓ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ መልስ ከሰጡ በኋላ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አይጠበቅብዎትም፡፡
- ✓ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ የሚነበብላቸውን ምንባብ በጥሞና እንዲያዳምጡ ያሳስቧቸው፡፡

### የማዳመጥ ሒደት

ተግባር፡-

- ✓ ተማሪዎቹ ለማዳመጥ ዝግጁ ከሆኑ በኋላ ረጋ ባለና ሁሉም ተማሪዎች ሊያዳምጡዎት በሚችሉት ሁኔታ ያንብቡላቸው፤ አስፈላጊ ከሆነም አንድ ጊዜ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡

- ✓ ምንባቡን ሲያነቡ መስማት የተሳናቸው ወይም የመስማት ውስንነት ያለባቸውን ተማሪዎች ባገናዘበ መንገድ ያቅርቡት፡፡
- ✓ በምንባቡ መሀል ላይ ምንባቡ ውስጥ ያሉትን ዕንቆቅልሾች እየጠየቁና መልሱን ተማሪዎች እንዲሞክሩ ዕድል እየሰጡ፣ ሙሉውን ምንባብ ያንብቡላቸው፡፡

### አዳምጦ መረዳት

- ✓ ምንባቡን አንብበውላቸው እንደጨረሱ የአዳምጦ መረዳት ተግባራትን እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር የቀረቡት ጥያቄዎች በአብዛኛው ምንባብ ተኮርና በቃል የሚመለሱ ስለሆኑ፣ ተማሪዎቹን እየጠየቁ የቃል ምላሽ ይቀበሏቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ምላሽ ተቀብለው ከጨረሱ በኋላ ማበረታቻና አስተያየት በመስጠት ወደሚቀጥለው ተግባር ይሸጋገሩ፡፡

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ስር፣ የተማሪዎቹን የመናገር ክሂል ለማዳበር ሲባል፣ በጥንድ እንዲሰሩ ሆነው፣ የቀረቡ ተግባራት አሉ፡፡ እነዚህን ተግባራት ተራ በተራ በቂ ጊዜ በመስጠት ያሰሯቸው፡፡
- ✓ የመጀመሪያው ዕንቆቅልሽ መጫወት ነው፡፡ በመሆኑም ጥያቄውን የማይመልሰውን ልጅ የእንቆቅልሽ አጨዋወት ሂደትን ተከትሎ፣ ሀገር በመሰጣጣት ስርዓት ጠብቀው፣ ተማሪዎቹ እንዲጫወቱ ዕድል ይስጧቸው፡፡
- ✓ ሁለተኛው ተግባር ራስን መግለጽ ስለሆነ፣ በመጀመሪያ እርስዎ አርአያ በመሆን፣ ለተማሪዎች ስለራስዎ በመግለፅ ያሳይዋቸው፡፡

- ✓ ይህን ተግባር በጥንድ ሰርተው ከጨረሱ በኋላ፣ የተወሰኑ ተማሪዎች ቆመው ለክፍል ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲገልፁ ዕድል ይስጧቸው፡፡
- ✓ እየተዘዋወሩ በማየትም አስፈላጊውን እገዛና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም የማጠቃለያ አስተያየት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

## ዕንቆቅልሽ

ዕንቆቅልህ/ሽ የሚለው ቃል ዐንቆቅሆ ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን፣ ዐንቆቅሆ ማለት እንቁላል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ እንደ ዕንቁላል ድፍን የሆነ፣ ፍቺው ያልታወቀ፣ መመርመርን የሚጠይቅ፣ ፈተና አመጣሁብህ ማለት ነው፡፡

ዕንቆቅልህ/ሽ፣ የእዕምሮ ንቃትን ይጠይቃል፤ ተጠያቂው ወይም ተፈታኙ ሰው በተወሰነ ሠዓት የጥያቄውን ፍቺ ማግኘት አለበት፡፡ አለበለዚያ፣ አገር መስጠትና መሰደብ ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን በተወሰነ ደቂቃ ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን ፍቺ ያገኘ እንደሆነ፣ አገር ከመስጠትና ከመሰደብ ይድናል፤ የአዕምሮ ዝቅተኛነትም አይሰማውም፡፡

ዕንቆቅልሽ ሥዕላዊ ምርመራን ይፈልጋል፡፡ ጠያቂው የረቀቀ የበሰለ፣ ምስጢር ያዘለ፣ ምሳሌን ያቀርባል፡፡ ተጠያቂው ደግሞ ከምሳሌው ጋር የሚነፃጸሩትን ነገሮች ሁሉ እያሰበ፣ ትክክለኛ ከሆነ መልስ፣ እስኪደርስ፣ ማውጣት፣ ማውረድና መመርመር ይኖርበታል፡፡

በትግል አቅምን በመገመት ጉልበትን መፈተን እንደሚቻል ሁሉ፣ በዕንቆቅልሽም የአዕምሮን ንቃትና ኃይል ማወቅ ይቻላል፡፡ ሰው ሁሉ አንድ ዓይነት አይደለም፤ አንዱ ከሌላው የሚሻልበት ጉዳይ ይኖራል፡፡ አንዱ በአንደኛው ነገር ንቁ ሆኖ፣ በሌላው ደግሞ ሊደክም ይችላል፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ልጆች፣ ዕንቆቅልሽ በመጠየቅና በመመለስ የተለየ ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

ዕንቆቅልሽ ጊዜን የሚጠይቅ የምርመራ ፈተና ነው። ይሁን እንጂ፣ጥያቄው በተወሰነ ደቂቃ ውስጥ መመለስ አለበት። ስለሆም፣ የዕንቆቅልሹ አቅራቢ ‹‹መሽብህ፤ ዕንቆቅልሼ ጠነዛብህ፤ ዋለብህ አደረብህ፤ አገር ስጠኝ›› እያለ፣ ተጠያቂውን ይወተውተዋል፤ ያዋክበዋል።

ተጠያቂው ዕንቆቅልሹን መፍታት ያቃተው እንደሆነ፣ ለጠያቂው አገር ይሰጣል። በዚህም መሸነፋን ስለሚገልጥ፣ የአዕምሮ ዝቅተኛነት ይሰማዋል። ጠያቂው ደግሞ በበኩሉ ይደሰታል፤ ይኩራራል። አገር አነሰኝ ጨምርልኝ እያለ ተጠያቂውን ያስገድደዋል። የሚመኘውንና የፈለገውን አገር ካገኘ በኋላ ‹‹እዚያ ተቀምጨ ምን አጥቼ፣ ሁሉ በእጄ ሁሉ በደጄ፣ እንዳልሰድብህ ወንድሜ፣ እንዳልተውህ ጠላቴ …›› እያለ ይወቅሰዋል።

‹‹እኔ ጌታህ ስሆን አንተ ደግሞ አሽከሬ፣ እኔ በሠንጋ በበቅሎ ሆኜ ስሄድ፣ አንተ አሽከሬ ደግሞ በገጣባ አህያ ተቀምጠህ ትከተለኛለህ፣…›› እያለ፣ የተሸናፊውን ዝቅተኛነት ያስረዳዋል።

ከዚህ አነጋገር ታላቅ ምሥጢር እናገኛለን። ይኸውም በአዕምሮ ያልጎለመሰ፣ የማሰብ ኃይሉ ከጓደኛው ያነሰ ሁሉ፣ የሌሎች የበታች ሆኖ እንደሚቀር ያመለክታል። ለጉልበት ስራ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ቢሆንም፣ የማስተዋል ንቃትና የመንፈስ ብርታትም አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ያሻል። እስኪ ደግሞ አሁን የተወሰኑ ዕንቆቅልሾችን በምሳሌነት እንመልከት፡-

1. ጠያቂ፡- ዕንቆቅልህ?

   ተጠያቂ፡- ምን አውቅልህ?

   ጠያቂ፡- ላዩ ሰርዶ፣ ውስጡ ብርንዶ፤

   ተጠያቂ፤- ቀይ ሽንኩርት፣ ነው።

ማብራሪያ፡- በልጣጭ የተሸፈነ ሸንኩርት፣ ሲገልጡት እንደሚያስደስት፣ በሩቁ፣ በአቋሙ ወይም በአለባበሱ አልባሌ የሆነ ሰውም፣ ቀረብ ተብሎ ሲታይና ሲመረመር ብዙ ቁም ነገር ሊገኝበት ይችላል፡፡

2. ጠያቂ፡- ዕንቆቅልህ?

ተጠያቂ፡- ምን አውቅልህ?

ጠያቂ፡- ሲወለድ ይጠቁር፣ ሲያረጅ ይቀላ

ተጠያቂ፡- በርበሬ ነው፡፡

ማብራሪያ፡- በርበሬ ወይም ቃሪያ ለጋ እያለ ደማቅ አረንጓዴ ሲሆን፣ እየበሰለ ሲሄድ ግን እየቀላ ይሄዳል፡፡

3. ጠያቂ፡- ዕንቆቅልህ?

ተጠያቂ፡- ምን አውቅልህ?

ጠያቂ፡- በትልቅ ምጣድ ላይ ትንሽ እንጎቻ፤

ተጠያቂ፤- ጨረቃ ናት፡፡

ማብራሪያ፡- ጨረቃ ሙሉ በሆነች ጊዜ፣ለሊት፣ በጠራ ሰማይ ላይ ሲመለከቷት፣ በሰፊ ምጣድ ላይ የተጋገረ፣ ዕንጎቻ ስለምትመስል፣ ሰማዩ በምጣድ፣ ጨረቃዋ በእንጎቻ ተመስለዋል፡፡

4. ጠያቂ፡- ዕንቆቅልህ?

ተጠያቂ፡- ምን አውቅልህ?

ጠያቂ፡- እንደእንጀራ ንብርብር፣ እንደነብር ዝንጉርጉር

ተጠያቂ፡- መጽሐፍ ነው፡፡

ማብራሪያ፡- የመጽሐፍ ገፆች የተነባበሩ ሲሆኑ፣ ሁሉም ገፆች ላይ ስለሚፃፍባቸው ተኽኅርጉረው ይታያሉ፡፡

5. ጠያቂ፡- ዕንቆቅልህ?

ተጠያቂ፡- ምን አውቅልህ?

ጠያቂ፡- ጉድ መጣ፤ ጉድ መጣ፤ ገንፎ ዛፍ ላይ ወጣ

ተጠያቂ፡- ሙዝ ነው፡፡

ማብራሪያ፡- ሙዝ ከተክል የሚገኝ የፍራፍሬ ዓይነት ቢሆንም፣ አላላሙ የእህል ቅቤን ስለሚመስል በገንፎ ተመስሏል፡፡

(የብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀል ስብስብ ሥራዎች፣ ባለን እንወቅበት፤ 2007 ዓ.ም፡፡ ገፅ 32-38፡፡ ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

ምዘና፡-

- ✓ ስነቃል አዳምጠው ምላሽ ሲሰጡ መከታተል፡፡
- ✓ ራሳቸውን በትክክል መግለፅ መቻላቸውን መከታተል፡፡

ክፍል ሁለት፡- ንባብ

የትምህርቱ አቀራረብ፡-

መምህር!

በዚህ ክፍል ማንበብን ለማስተማር በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበ ‹‹ተረት›› የሚል ምንባብ ይገኛል፡፡ ምንባቡን በመጠቀም ትምህርቱን እደሚከተለው ያቅርቡ፡፡

ቅድመ ንባብ

- ✓ ተማሪዎቹ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የሚሰሩት አንድ ተግባር ሲኖር ተግባሩን ተማሪዎች በቃል እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር ፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ሶስት ጥያቄዎች ሲኖሩ ምንባቡ የያዘውን ሀሳብ በማስመልከት ፍንጭ እንዲያገኙ የሚያደርጉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹን በመጠየቅ በቃል መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

የተማሪዎችን ምላሽ ተከትለው ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አያስፈልግዎትም፡፡

የንባብ ሒደት

- ✓ ተማሪዎች ሠንጠረዡን በደብተራቸው ላይ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠልም ምንባቡን በተናጠል በለሆሳስ እያነበቡ፣ ሠንጠረዡን እንዲሞሉ ይዘዟቸውና እየተዘዋወሩ ክትትልና ድጋፍ ያድርጉ፡፡

አንብቦ መረዳት

- ✓ በአንብቦ መረዳት ስር ሁለት ተግባራት አሉ፡፡
- ✓ በመጀመሪያ ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው እንደጨረሱ፣ ሠንጠረዡ ውስጥ የሞሉትን እንዲያነቡ ይጠይቋቸው፡፡ በርከት ላሉ ተማሪዎች ዕድል በመስጠት ያሳትፏቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም በአንብቦ መረዳት ስር የቀረቡትን ተግባራት እንደየ መመሪያዎቻቸው ያሰሯቸው፡፡

ተግባር 1፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር ከ‹‹ሀ-ቀ›› የተዘረዘሩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡
- ✓ ጥያቄዎቹን ተራ በተራ በቃል እየጠየቁ፣ ከተማሪዎቹ የቃል ምላሽ ይቀበሉ፡፡

- ✓ ‹‹ሰ›› ላይ ያለው ጥያቄ የስነ ቃል ዓይነቶችን እንዲዘረዝሩ የሚጠይቅ ስለሆነ፣ ተማሪዎቹ የሚያውቋቸውን የስነ ቃል ዓይነቶች እንዲዘረዝሩ ያበረታቷቸው። መልሳቸውን ተቀብለው፣ ሠሌዳው ላይ ይጻፉላቸው። ተማሪዎቹ ከዘረዘሯቸው በተጨማሪ እርስዎም ለተማሪዎቹ ደረጃ በሚመጥን መልኩ፣ ተጨማሪ ይጥቀሱላቸው። የስነቃልን ምንነትና ባህሪውንም በመጠኑ ይግለፁላቸው።
- ✓ ‹‹ሸ›› ላይ ስለእንካሰላንትያ የቀረበ ጥያቄ አለ። ምንባቡ ውስጥ ስለ እንካሰላንትያ በዝርዝር የቀረበ ነገር የለም። ተማሪዎቹ የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው የሚያውቁትን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። እርስዎ የሚያውቁትንም ያጋሯቸው። በተለይም ቤት እየመቱ ግጥም የመግጠም ችሎታን ለማዳበር ያለውን ጠቀሜታ ያብራሩላቸው። የእንካሰላንትያ አጨዋወትን የሚያውቁ ተማሪዎች ካሉ በመጋበዝ አጨዋወቱን ለሌሎች ተማሪዎች በተግባር እንዲያሳዩ ይጋብዙ።
- ✓ ‹‹ቀ›› ላይ ያለው ጥያቄ፣ በምንባቡ ውስጥ የቀረበውን ተረት ለጓደኛቸው እንዲተርኩ ስለሆነ፣ ይህን ተግባር ተማሪዎች የተረት አነጋገር ስርዓትን ተከትለው እንዲተገብሩ ይዘዟቸው፣ ይከታተሏቸው። እንደአመቺነቱም ሌላ ተረት እንዲናገር ቢያንስ ለአንድ ተማሪ ዕድል ይስጡ።

ተግባር 2፡-

- ✓ በዚህ ተግባር ስር የልቦለድ አላባውያንን ቀለል ባለ መንገድ በአዛምድ መልክ ለተማሪዎቹ ለማስተዋወቅ ይሞከራል። በመሆኑም፣ በምንባቡ ውስጥ የቀረበውን ተረትና በቅድመ ማንበብ ተግባር ስር የሞሉትን ሠንጠረዥ መሰረት በማድረግ፣ ስለልቦለድ አላባውያን ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልክ ቀለል ያለ ገለጻ ለተማሪዎቹ ይስጡ።

- ✓ በመቀጠልም ተማሪዎቹ በመጽሐፋቸው ላይ ስለልቦለድ አላባውያን የሚያሳየውን ስዕላዊ መግለጫ በደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ ከዚያም የአዛምድ ጥያቄውን ደብተራቸው ላይ ፅፈው፣ መልሱን በመስራት እንዲያሳዩ ተማሪዎቹን ይዘዙ፤ አሰራራቸውን በመዘዋወር ይከታተሉ፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉ፡፡
- ✓ የተማሪዎቹን ምላሽ በመገምገም አስፈላጊውን እርማት በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃልሉት፡፡

ምዘና፡-

- ✓ ስርዓት ተከትለው ተረት ሲተርቱ መከታተል
- ✓ በተረቱ ውስጥ ያሉ አላባውያንን ለይተው ሲገልፁ መከታተል

ክፍል ሶስት፡- ቃላት

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን እየነጣጠሉና እያጣመሩ ማንበብን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት ለማቅረብ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ሁለት ተግባራት ቀርበዋል፡፡ ተግባራቱን በመጠቀም የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ተከትለው ትምህርቱን ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ ከአሁን በፊት በተማሩት መሰረት ቃላትን እየነጣጠሉና እያጣመሩ ማንበብን በምሳሌ አስደግፈው ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ለዚህ ተግባር በመማሪያ መጻሐፉ ላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች ይጠቀሙ፤ እንደአስፈላጊነቱም ተጨማሪ ምሳሌ ይስጧቸው፡፡ ይሁን እንጂ ጥልቅ የምዕላድ ፅንሰሀሳብ ትንተና ውስጥ መግባት ለተማሪዎቹ ደረጃ ስለማይመጥን፣ ጥንቃቄ ያድርጉ፡፡

- ✓ በመቀጠል በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ተግባራት እንደየመመሪያቸው በሚከተለው መልኩ ያሰሯቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም እርማትና ማጠቃለያ ይስጡ፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ፡-

- ✓ ተነጣጥለውና ተጣምረው የተጻፉ ቃላት የያዙ ካርዶችወይም ቻርት

ምዘና፡-

- ✓ ቃላትን ነጣጥለውና አጣምረው ሲያነቡ መከታተል፡፡

ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

መምህር!

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የሕይወት ታሪክ መጻፍን ይማራሉ፡፡ የትምህርቱ ዓላማ ይሳካ ዘንድ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሂደትና ቅደም ተከተል በመከተል ትምህርቱን ያቅርቡላቸው፡፡

- ✓ በመጀመሪያ ስለሕይወት ታሪክ የሚያውቁትን እንዲገልጹ እድል ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ምላሽ በመመርኮዝ እና በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያለውን አጭር ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ስለሕይወት ታሪክ ምንነትና አጻጻፍ የተመጠነ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ናሙና ቅርጽ ተብሎ የቀረበውን ያልተሟላ ሕይወት ታሪክ በግለሰብ ሕይወት ታሪክና በግለ ታሪክ እያሚሉ ያሳዩዋቸው፡፡
- ✓ ናሙናውን ለአንድ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ የሕይወት ታሪክ በሚስማማ መልክ ቀይረው በማሳየት፣ ቀለል አድረገው ያስረዷቸው፡፡

- ✓ ቀጥሎም በመጀመሪያ በተግባር 1 ላይ በታዘዘው መሠረት የራሳቸውን የሕይወት ታሪክ እንዲጽፉ ይዘዟቸው፣ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ ፈቃደኛ ተማሪዎች ካሉ የጻፉትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ይጋብዙ፡፡ ከሌሉ ግን ማንንም <u>እንዳያስገድዱ ይጠንቀቁ</u>፤ ምክንያቱም የተማሪዎች መሳቂያ እንሆናለን ብለው፣ የሚሳቀቁ ተማሪዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ፤ በተለይም ደግሞ ከአባታቸውና ከእናታቸው ስም ጋር በተያያዘ፡፡
- ✓ በመቀጠልም፣ በጥያቄ ቁጥር ‹ለ› ላይ ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው የአንዱን የህይወት ታሪክ እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ ለዚህም እንዲረዳቸው ተማሪዎቹ አስቀድመው የመረጡትን የቤተሰባቸውን አባል ቃለ መጠይቅ በማድረግ ማስታወሻ ማዘጋጀት እንዳለባቸው ያስገንዝቧቸው፡፡ ማስታወሻ ሲይዙም በአጭር በአጭሩ መዝግበው መያዝ ያለባቸውን ነጥቦች ይጠቁሟቸው፡፡ በተቻለ መጠን ቃል በቃል እየጠየቁ እንዳይጽፉ ያሳስቧቸው፡፡
- ✓ እዚህም ጋር ለማንበብ ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎች ካሉ ብቻ፣ የጻፉትን የሕይወት ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ይጋብዙ፡፡
- ✓ በመጨረሻም፣ የተማሪዎቹን ጽሁፍ አንብበው አስፈላጊውን እርማት በመስጠት ትምህርቱን ያጠናቁ፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

- ✓ በሕይወት ታሪክ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸውን ዐበይት ነጥቦች የያዘ የቢጋር ሠንጠረዥ ወይም ቻርት፡፡

ምዘና

- ✓ የሕይወት ታሪክ ሲጽፉ መከታተል፡፡

ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር

በዚህ ክፍል ተማሪዎች ርቱዕና ኢ-ርቱዕ ተሳቢን መለየትን ይማራሉ፡፡ ትምህርቱን በሚገባ ለማቅረብ ይረዳዎት ዘንድ የሚከተለውን የመማር ማስተማር ሒደት ይከተሉ፡፡

- ✓ በመጀመሪያ ቀደም ባሉት ክፍሎች የተማሯቸውን እንዲያስታውሱ ስለዐረፍተ ነገር ተዋቃሪዎች የሚያውቁትን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ርቱዕና ኢ-ርቱዕ ተሳቢን መለየት የሚለውን ርዕስ በሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸው፡፡
- ✓ ከዚያም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበውን ርቱዕና ኢ-ርቱዕ ተሳቢን ስለመለየት የቀረበውን ማስታዎሻ እንዲፅፉ በቂ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ማስታዎሻውን ጽፈው እንደጨረሱ ከማስታዎሻውና ከተሰጡት ምሳሌዎች በመነሳት ርቱዕና ኢ-ርቱዕ ተሳቢን ስለመለየት ያገኙትን ግንዛቤ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ የተወሰኑ ተማሪዎችን ምላሽ ከተቀበሉ በኋላ በምሳሌ የተደገፈ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ርቱዕና ኢ-ርቱዕ ተሳቢን ስለመለየት ሲያስረዷቸው ጠለቅ ያለ ስዋሰዋዊ ትንታኔ ላለመስጠት ጥንቃቄ ያድርጉ፡፡
- ✓ ይህን ማለት ሁሉም ዐረፍተ ነገሮች ርቱዕና ኢ-ርቱዕ ተሳቢ አላቸው ብለው እንዳያጠቃልሉ አቅማቸውን ባገናዘበ መልኩ ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተግባራቱን ከመስራታቸው በፊት አሰራሩ የበለጠ ግልፅ እንዲሆንላቸው፣ ለየተግባራቱ ለአብነት የቀረቡትን ምሳሌዎች በእርጋታ ያስረዷቸው፡፡
- ✓ በተለይም ደግሞ ባለቤትን፣ርቱዕ ተሳቢንና ኢ-ርቱዕ ተሳቢን ለመለየት የሚረዱትን ቁልፍ ጥያቄዎች አጠቃቀም ያስረዷቸው፡፡

✓ አብዛኛውን ጊዜ ርቱዕ ተሳቢዎች ላይ ‹‹-ን›› የምትል ቅጥያ ምዕላድ እንደምትኖርና ኢ-ርቱዕ ተሳቢ ላይ ደግሞ ‹‹ለ-›› የምትል ቅጥያ ምዕላድ እንደምትኖር ይጠቁሟቸው፡፡

✓ ይዘቱን በዚህ መንገድ በቀላሉ ከገለጹላቸው በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ በቀረቡት ሁለት ተግባራት ውስጥ የተካተቱትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ

✓ መሰረታዊ የዐረፍተ ነገር ተዋቃሪዎችን የሚያሳይ ቻርት

ምዘና፡-

✓ ርቱዕ ተሳቢንና ኢ-ርቱዕ ተሳቢ ሲለዩ መከታተል፡፡

የተመረጡ ተግባራት መልሶች፡-

ተግባር 1

ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ተሳቢዎች ርቱዕ ተሳቢ እና ኢ-ርቱዕ ተሳቢ በማለት ለዩ፡፡

| | የተሰጠ ዐረፍተ ነገር | ርቱዕ ተሳቢ | ኢ-ርቱዕ ተሳቢ |
|---|---|---|---|
| | መምህሩ ለተማሪው መጽሐፍ ሸለመው፡፡ | መጽሐፍ | ተማሪው |
| ሀ | ጀማል ለጓደኛው ሠላምታ አቀረበ፡፡ | ሠላምታ | ጓደኛው |
| ለ | ወፏ ለጫጩቶቿ ምግብ አመጣች፡ | ምግብ | ጫጩቶቿ |
| ሐ | ዓይናለም ለሰሚራ ስጦታ አበረከተች፡፡ | ስጦታ | ሰሚራ |
| መ | የአካባቢው ኗሪ ለልማት ገንዘብ አዋጣ፡፡ | ገንዘብ | ልማት |
| ሠ | አልማዝ ኳሷን ለፈይሰል አቀበለች፡፡ | ኳሷ | ፈይሰል |

## ዋቢዎች

### ምዕራፍ አንድ


አለማየሁ ዋሴ (2012)፡፡ ሰበዝ፡፡ አዲስ አበባ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት፡፡

አማረ ማሞ (1976)፡፡ የቀለም ጠብታ፡፡ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፡፡

ዳንኤል ክብረት (2008)፡፡ የሚከራዩ እማት፡፡ አዲስ አበባ፣ አግዮስ ማተሚያ ቤት፡፡


### ምዕራፍ ሁለት


ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ (2002)፡፡ የአማርኛ መርጃ መጽሐፍ፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ጌታሁን አማረ (2007)፡፡ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ (13ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡


### ምዕራፍ ሶስት


በአፋር ብሐየራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ (2006)፡፡ የአፋር ባህላዊ እሴቶች፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ባዬ ይማም (2002)፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ታሪኩ ፋናታዬ (2008)፡፡ አማርኛ ሁሉ ለሁሉ፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት፡፡

አሌክስ አብርሃም (2011)፡፡ ዙቤይዳ (11ኛ ዕትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት

የዳውሮ ዞን ባል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ (2008)። ዎንታ መጽሔት፣ ቁጥር 11። አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት።

ዳኛቸው ወርቁ (1977)። የጽሑፍ ጥበብ መምሪያ። አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

## ምዕራፍ አራት

ባዬ ይማም (2002)። አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን (2013)። አዲስ ፖሊስ መጽሔት፣ ቁጥር 10። አዲስ አበባ (ማተሚያ ቤት ያልተገለጸ)።

ጌታሁን አማረ (2007)። የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ (13ኛ እትም)። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

## ምዕራፍ አምስት

ባዬ ይማም (2002)። አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

አለማየሁ ዋሴ (2008)። እመጓ። አዲስ አበባ፣ ያሬድ ማተሚያ ቤት።

## ምዕራፍ ስድስት

ሰለሞን ሀለፎም (1997)። የድርሰት አጻጻፍ። አዲስ አበባ፣ብራና ማተሚያ ቤት።

ጌታሁን አማረ (2007)። የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ (13ኛ እትም)። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

## ምዕራፍ ሰባት

ሰለሞን ሀለፎም (1997)፡፡ የድርሰት አጻጻፍ፡፡ አዲስ አበባ፣ብራና ማተሚያ ቤት፡፡

በጋሻው (2012)፡፡ ውፍረት (ያልታተመ)፡፡

ጆርዳና (2007)፡፡ የምግብ አዘገጃጀት ቁጥር አንድ፡፡ አዲስ አበባ፣ ሰሊሆም ማተሚያ ቤት፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

ባዬ ይማም (2002)፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ሀብት ገጽታ (2010)፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ያሬድ እንግዳ (2013)፡፡ ቴክ ሳይንስ መጽሔት፣ 7ኛ ዓመት፣ 19ኛ እትም፡፡ አዲስ አበባ፣ የኢፌዴሪ ቴክኖሎጅና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት፡፡

ደረጀ ገብሬ (2007)፡፡ ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ (3ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አቢጌት ማተሚያ ቤት፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ

ማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል (2007)፡፡ የብላቴን ጌታ ማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል ስብስብ ስራዎች፡፡ (ማተሚያ ቤት ያልተገለጸ)፡፡

ባዬ ይማም (2002)፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ዘሪሁን አስፋው (2004)፡፡ የስነ ጽሑፍ መሰረታዊያን፡፡ አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ደረጀ ገብሬ (2007)፡፡ ተግባራዊ የጽሕፈት መማያ (3ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አቢጌት

ማተሚያ ቤት፡፡

## ምዕራፍ አስር

ማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል (2007)፡፡ የብላቴን ጌታ ማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል ስብስብ ስራዎች፡፡ (ማተሚያ ቤት ያልተገለጸ)፡፡

ባዬ ይማም (2002)፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ዘሪሁን አስፋው (2004)፡፡ የስነ ጽሑፍ መሰረታዊያን፡፡ አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)አምስተኛ ክፍል አንደኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት

**ምዕራፍ አንድ ፡- ጓደኝነት (18ክፍለ ግዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምእራፍ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ስለ ጓደኝነት ያላቸውን አመለካከት አዳምጠው ያንጸባርቃሉ፡፡
- ጽሁፉን አንብበው መልክቱን ይገልጻሉ፡፡
- ከጓደኞቻቸው ጋር እንዴት ጊዜ እንደሚያሳልፉ በቀላል አረፍተ ነገር  አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- የወልና የተጸውኦ ስሞችን ይለያሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው የተረዱትን ይገልጻሉ፡፡<br>➢ የለሆሳስ ንባብ ዘዴን ተጠቅመው የምንባቡን ዋና መልዕክት ያወጣሉ፡፡<br>➢ ለቃላትተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡<br>➢ የአንቀጽ ክፍሎችን ይለያሉ፡፡<br>➢ የተጸውኦና የወል ስሞችን ይለያሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ ቃላት<br>➢ ጽህፈት<br>➢ ሰዋሰው | ተማሪዎች ሰዎች ትርፍ ጊዜያቸውን እንዴት እንደሚሳልፉ የሚያወሩትን አዳምጠው የራሳቸውን የውሎ ማስታወሻ እንዲጽፉ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎች እራሳቸውን ለመምህራቸው እንዲያስተዋውቁ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎች ከዕለት ውሏቸው ጋር ተያያዥ የሆኑ ነገሮችን ለመግለጽ ደጋግመው በማንበብ ማህበራዊ አገላለጽን እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡(ሰላምታ፣ጭውውት...)<br>ተማሪዎች ከትምህርቱ በፊትና በኋላ የአንቀጽ ክፍሎችን እንዲለዩ ማድረግ፡፡ተማሪዎች ስፖርታዊ ምስሎችንና የመዝናኛ ጨዋታዎችንከተሰጣቸውቃላትጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ፡፡ | ➢ ተማሪዎችጽሁፎችን አንብበው ሰዎች ትርፍ ግዜያቸውን እንዴትእንደሚያሳልፉ የሚቀርቡትን መከታተል፡፡<br>➢ ተማሪዎች በትርፍ ግዜያቸው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት መጻፋቸውን መከታተል፡፡<br>➢ ተማሪዎች ምንባቡ ላይ የተገለጸውን ሃሳብ መሰረት በማድረግ የአንድ ሳምንት የዕለት ውሎ ዘገባ እንዲጽፉ በማድረግ መከታተል፡፡ |

**ምዕራፍ ሁለት፡-ጽዳትና ንጽህና (18 ክፍለ ግዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የሚነበብላቸውን አዳምጠው ይመልሳሉ፡፡
- ሰዎች ንጽህናቸውን ለመጠበቅ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ይገልጻሉ፡፡
- ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ በትክክል ያነባሉ፡፡
- መጣኝ ርዕስ በመምረጥ አጭር አንቀጽ ይጽፋሉ ፡፡
- በአዳዲስ የይዘት ቃላት ላይ ይወያያሉ፡፡
- የድምጾችና ምዕላዶችን መዋቅር ይገነዘባሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ በቡድን ስራ ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡<br>➢ የክፍል ደረጃውን በመጠነ መልኩ አስተካክለው ያነባሉ፡፡<br>➢ አጭር አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡<br>➢ አዳዲስ ቃላትን መሰረት አድርገው ይወያያሉ፡፡<br>➢ ባለብዙ ቅጥያ ምዕላድና ድምጾችንበመነጠልና በማጣመር ቃላትን ይለያሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | የቡድን ውይይት፡- ተማሪዎች ሰዎች የሚሰሩትን በቡድን ውይይት ውስጥ በመሳተፍ እንዲገልጹ ማድረግ፡፡<br>አንድን ጽሁፍ በየእለቱ በማንበብ ንጽህናን በተመለከተ ሰዎች የሚያከናውኗቸውን ተግባራት እንዲገልጹ ማድረግ፡፡<br>በክፍል ውስጥ ምን ምን ጉዳዮች እንዳከናወኑ እንዲገልጹ ማድረግ፡፡<br>በጥንድ በመሆን እየተወያዩ የመረጃ ክፍተትን እዲያሟሉ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎች ጽዳትን በተመለከተ የሚያከናውኑትን | ➢ ተማሪዎች የቡድን ውይይቱ በምን ላይ ያተኮረ እንደሆነ በማዳመጥ ደግመው እንዲገልጹ ማድረግ፡፡<br>➢ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ታሪክ በማንበብ ታሪኩን መሰረት ያደረጉ ተግባራትንና ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ፡፡<br>➢ ሰዎች ንጽህናቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ አጭር አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ፡፡ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | ተግባር በምልክት አዲገልጹ ማድረግ፡፡ | ➢ ተማሪዎች ከጽሁፉ ውስጥ አዳዲስ ጭብጦችን መለየታቸውንናየአዳዲስ ቃላት እውቀትክምችታቸውን ስለማዳበራቸው መከታተል፡፡ |

**ምእራፍ ሶስት፡-ልማድ(18 ክፍለግዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- አንድን ታሪክ አዳምጠው ይተርካሉ፡፡
- ተገቢውን ድምጸት ጠብቀው ጽሁፉን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያነባሉ፡፡
- የአንቀጽ አይነቶችን ይለያሉ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ተውሳከ ግሶችን ይለያሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-<br>➢ አዳምጠው ታሪኩንይተርካሉ፡፡<br>➢ ተገቢውን ድምጸት ጠብቀው ጽሁፉን ድምጻቸውን ከፍ አርገው ያነባሉ ያነባሉ፡፡<br>➢ የአንቀጽ አይነቶችን ይለያሉ፡፡<br>➢ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡<br>➢ በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ተውሳከ ግሶችን ይለያሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | ተማሪዎች አንድ ምልልስን በማዳመጥ የልማድን ምንነት እንዲገልጹ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሁፍ ውሰጥ ያልገባቸውንና ግልጽ እንዲሆንላቸው የሚፈልጉት እንዲጠይቁ ማበረታታት፡፡<br>በጥያቄና መልስ ማስተማሪያ ዘዴ እንዲማሩ ማመቻቸት፡፡በድህረ ንባብ ጊዜ አራት መመሪያ ሰጥቶ በሰንቱ ላይ መጻፍ፡፡<br>አስበው መልሱን ከዓረፍተ ነገር ውስጥ እንዲፈልጉ ማድረግ | ➢ ተማሪዎች ስለልማዳዊ እቃዎች አዳምጠውአገልግሎታቸውን እነዲገልጹ ማድረግ፡፡<br>➢ መምህሩ ሁለት ምልልሶች ካነበቡ በኋላ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በመለየትእንዲጠቀሙባቸው ማድረግ፡፡<br>➢ ተማሪዎች ስለ ጠቃሚና ጎጂ ልማዶች እንዲጽፉ በማድረግ መከታተል፡፡ |

**ምዕራፍ አራት፡-የትራፊክ ደህንነት (18 ክፍለ ግዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ምልልስ አዳምጠው አስፈላጊነቱን ይገልጻሉ፡፡
- የተለያዩ የማዳመጥ ስልቶችንተጠቅመውለተነበበላቸው ጽሁፍ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡
- ማህበራዊ አገላለጾችን ይጠቀማሉ ፡፡
- አንቀጽ አንብበው ጭብጡንና አስፈላጊነቱን ይገልጻሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማሪያ ስልቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-<br>➢ ለክፍል ደረጃው ታስበው የተቀረጹ ነገሮችን ያዳምጣሉ፡፡<br>➢ ያነበቡትን ጽሁፍ ዋና መልክት ይገልጻሉ፡፡<br>➢ ከጽሁፉ የወጡ ጥያቄዎችን አዳምጠው ይመልሳሉ፡፡<br>➢ ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ይጽፋሉ፡፡<br>➢ የባህሪ ተውሳከ ግሶችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋስው | ተማሪዎች አንድን ከትራፊክ አደጋ ጋር የተያያዘ ምስል ተመልክተው የተረዱትን እንዲገልጹ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎች ስለትራፊክ ህጎች በጥያቄና መልስ ከተወያዩ በኋላ በመንገድ ላይ የሚያደርጉትን ጥንቃቄ እንዲገልጹ ማድረግ፡፡<br>መምህሩ ቀላል ምልልሶችን ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎች የመጀመሪያውን ግማሽ አረፍተ ነገርን ከቀጣዩ ግማሽ ዓረፍተ ነገር ጋር ያዛምዳሉ<br>ተማሪዎች ከስራቸው የተሰመረባቸውን ስድስት ቃላት ትርጉም በመገመት ተመሳሳያቸውን እንዲሰጡ ማድረግ፡፡<br>➢ ተማሪዎች የያንዳንዱን አንቀጽ ዋና መልክት ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ | ➢ መምህሩ ለተማሪዎች የትራፊክ ደህንነትን የሚያሳይ ስዕል ሲያሳዩዋቸው ተማሪዎች የተገነዘቡትን መመለሳቸውን ማርጋገጥ፡፡<br>➢ ተማሪዎች ለክፍሉ የተዘጋጁ ጽሁፎችን አንብበው ምን ያህል እንደተረዱ ራሳቸውን እንዲመዝኑ ማድረግ፡፡<br>➢ ተማሪዎች ስለ ትራፊክ ደህንነትዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ማድረግ፡፡<br>➢ ተማሪዎች የግብዣቃላትን |

| ብቃት | ይዘት | የመማሪያ ስልቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | | መሰረት አድርገው የተመሰረቱ ዓረፍተነገሮችን እንዲያነቡ ማድረግ። |

**ምዕራፍ አምስት፡-አካባቢ እንክብካቤ (18ክፍለ ግዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የቀደመ እውቀታቸውን ከአሁኑ ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- መዝገበ ቃላትን ተጠቅመው የቃላትን ድምጽአሰዳደር ትርጉማቸውንና ግንኙነታቸውን ያረጋግጣሉ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ የቀለም መለያ ምልክቶችን ይጠቀማሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ ያዳመጡትን በቃል ይተርካሉ፡፡<br>➢ ምእላዶችን በማጣመርና በመነጠል ያነባሉ፡፡<br>➢ **ከአንቀጽውስጥ ሀይለቃሉን ይለያሉ፡፡**<br>➢ **በአረፍተ ነገር ውሰጥ ብዙና ነጠላ ቁጥር ስሞችን ይለያሉ፡፡** | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃል<br>➢ ሰዋሰው | ተማሪዎች በምስል የተገለጹ ነገሮችን የሚወክሉ ቃላትን ከጽሁፍ ውስጥ በመፈለግ ይመልሳሉ፡፡<br>ለተማሪዎችእራሳቸውን ችለው እንዲያነቡ እድል መስጠት ምክንያቱም ይህ ዘዴ የአዳዲስ ቃላት ክምችታቸውን ያዳብርላቸዋል፡፡<br>ተማሪዎች የጽሁፉን መልዕክት በመገንዘብ ራሳቸውን መመዘናቸውን ይቀጥላሉ፡፡<br>መምህር፡-ተማሪዎች አንቀጽ አንብበው የአንቀጽን ሃይለቃል እንዲለዩ ያበራቷቸው፡፡ በቅድሚያ እርስዎ አንድ ምሳሌ ያሳዩአቸው<br>መምህር በዓረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ስሞችና ግሶችን መሰረት አድርገው የትኛው ነጠላ የትኛው ደግሞ ብዙ ቁጥር እንደሆነ ያሳዩአቸው፡፤ ተማሪዎች እርስዎን ተከትለው በጥንድና በቡድን እንዲሰሩና በራሳቸውም እንዲተራረሙ ያድርጓቸው | ➢ አጫጭርማስታወሻዎችን በመስጠት ተማሪዎች በግል እና በቡድን የሰሯቸውን መመልከት፡፡<br>➢ የሰሩትን ማቅረብ በዚህ ወቅት ተማሪዎችበራሳቸው ያዘጋጁዋቸውን ቃላት ለተማሪዎችየማቅረብ እድል ያገኛሉ፡፡<br>➢ የጥንድ ግምገማ ተማሪዎች ከመምህራቸው በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት እርስ በርስ ይተራረማሉ መምህሩም እርስ በርስ የተራረሙበትን ወረቀት በመሰብሰብ መሻሻላቸውን ይገመግማል |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዝና |
| --- | --- | --- | --- |
| | | | ➢ ለክፍል ደረጃው በቀረበው ጽሁፍ ውስጥ በግራፍ የተደራጁ መረጃዎችን በመጠቀም የተደራጀ ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡ |

አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)አምስተኛ ክፍል ሁለተኛ መንፈቅ ዓመት መርኃ ትምህርት

**ምዕራፍ ስድስት፡-ጸረ- አደንዛዥ እጾችና ንጥረ ነገሮች (18ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ➢ አዳምጠው አደንዛዥ እጽን እንዴት መዋጋት እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡
- ➢ ጽሁፉ ስለምን እንደሆነ ይገምታሉ፡፡
- ➢ ምልክቶችንና መግለጫዎችን በማንበብ የጽሁፉን መልዕክት ይረዳሉ፡፡
- ➢ የሽግግር ቃላትን ይለያሉ፡፡
- ➢ ለቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የማስተማሪያ ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-<br>➢ አዳምጠው ቀለሞችን ይለያሉ፡፡<br>➢ የሚነበበው ጽሁፍ ስለምን እንደሆነ ይገምታሉ፡፡<br>➢ ለቃላት አገባባዊ ፍቺ ይሰጣሉ<br>➢ የሽግግር ቃላትን ተጠቅመው አንቀጽ ይመሰርታሉ፡፡<br>➢ ግሰና ስምን | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ ቃላት<br>➢ መጻፍ<br>➢ ሰዋሰው | ተማሪዎች ካነበቡት ውስጥ ግራ ያጋባቸውንና ግልጽ ያልሆነላቸውን በተጨማሪ እንዲፈልጉ ማድረግ፡፡<br>በግልጽ የቀረበላቸውን ጥያቄ በቀጥታ እንዲመልሱ ማድረግ<br>አንቀጽ ሲጽፉ የንግግር ድምጾችን አያዦችንና ሀረጎችን እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡<br>ከአንድ አረፍተ ነገር በላይ የሚጠይቁ መረጃዎችን እያሰላሰሉ ከጽሁፍ ውስጥ በመፈለግ እንዲመልሱ ማድረግ፡፡<br>በድህረ ንባብ አራት አይነት ያላቸው ጥያቄዎች ይጻፉ (መልሳቸው አንድ የተለየ ዓረፍተነገር ውስጥ ይገኝ)አላማው<br>የቃላት አገባብን መሰረት ያደረገ ይሁን<br>መምህር ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ አያያዥ ቃላት መጠቀማቸውን ይመለከቱ፡፡ መጠቀማቸውን ( ቋንቋውን መሰረት ያደረገተሽጋጋሪ ምእላዶችን) | ➢ ባለፈው ከተማሩት ውስጥ የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡<br>➢ የተለያዩ ባለቀለም ካርዶችን በመጠቀም ለሚጠየቁት ጥያቄ መልስ ይሰጣሉ፡፡<br>ለምሳሌ እስማማለሁ፣አልስማማም ወዘተ… |

| ብቃት | ይዘት | የማስተማሪያ ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተጠቅመው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡ | | መምህር ተማሪዎችን ማሰብና መፈለግ በሚለው አካሄድ (መለሱ ጽሁፍ ውሰጥ ሆኖ ነገር ግን መረጃው ከአንድ በላይ አረፍተነገር እንዲኖረው አድርገው ይዘዙ) | |

**ምዕራፍ ሰባት ፡-ምግብ (18 ክፍለ ግዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- አንድን ገላጭ ጽሁፍ አዳምጠው መልእክቱን ይገልጻሉ፡፡
- ስርኣተ ነጥቦችን ይጠቀማሉ፡፡
- አስተካክለው ያነባሉ፡፡
- ሂደታዊ ተንታኝ አንቀጾችን ተረድተው ይገልጻሉ፡፡
- የምእላድ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንግዳ ቃላትን ያነባሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማሪያ ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-<br>➢ የቀረበውን ጽሁፍ አዳምጠው ሃሳቡንበማወዳደርና በማነጻጸርይገልጻሉ፡፡<br>➢ ሂደታዊ አንቀጾችን በመጻፍ ያነባሉ፡፡<br>➢ ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡<br>➢ የሚቆጠሩናየማይቆጠሩ ስሞችንለይተው ይናገራሉ፡፡ | ➢ ማዳመ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን ለጓደኞቻቸው እንዲያጋሩ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎች መማር በሚፈልጉት ትምህርት ዙሪያ በመወያየት የተማሩትን እንዲከልሱ ማድረግ፡፡<br>ከሰንጠረዥ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ መግለጽ ተማሪዎች ሰንጠረዡን በማየት ስለምን እንደሚገልጽ፣ምንምን ጉዳዮችን እንደሚያካትት ወዘተ..ትልም በመንደፍ ዋናዋና ክስተቶችን በመሰነድ እንዲጽፉ ማድረግ፡፡<br>ስዕላዊ መግለጫን በመጠቀምሁለት ነገሮችን ያወዳድራሉ፡፡<br>ለምሳሌ መጽሃፎችን፣ባህሪዎችን፣ ወቅቶችን፣ስራዎችን፣ወዘተ..የአንድን ነገር ምክኒያትና ውጤት ይገልጻሉ፡፡ | ➢ ተማሪዎች በመልሶቻቸው ላይ ከተወያዩ በኋላ መልሶቻቸውን አጠገባቸው ላሉ ሌሎች ተማሪዎች በማጋራት ይወያያሉ፡፡<br>➢ መምህሩ የተማሪዎቹንመሻሻል ለማየት በመሀከላቸው ይዘዋወራል፡፡<br>➢ ተማሪዎቹ ምእራፉን ሲያጠቃልሉ ሁለት ቦታ ክፍሎ በተሻለ ደረጃ የተረዱትንና ያልተረዱትን መለየት፡፡<br>➢ በቀጣይ የጽሁፍ የቤት ስራ በመስጠት ትምህርቱን ማጠቃለል፡፡ |

**ምዕራፍ ስምንት፡-በኢትዮጵያ የሚገኙ የዱር እንስሳት (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ውስበስብ ቃላት በምእላድ እንዴት እንደሚከፋፍሉ ይገልጻሉ፡፡
- ውስበስብ ቃላትን ያነባሉ፡፡
- አወዳዳሪና አነጻጻሪ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን ይጠቀማሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የማስተማሪያ ስልቶችና መረጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-<br>➢ አዳምጠው አዳዲስ ስሞችንይዘረዝራሉ፡፡<br>➢ ጽሁፉን አንብበው ከህይወታቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡<br>➢ አወዳዳሪና አነጻጻሪ አንቀጽይጽፋሉ፡፡<br>➢ ለቃላትተመሳሳይፍቺ ይሰጣሉ፡፡<br>➢ ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን ይለያሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | የተለያዩ የቃላት ክፍሎችን በማቅረብ እንዲተረጉሙ ማድረግ<br>አንድን ቃል በመስጠት ቦታ እያቀያሩ ቃላት እንዲመሰርቱ ማድረግ፡፡<br>ለተማሪዎችስዕል በማቅረብ ሊገልጹ የሚችሉ ቃላትን እየፈለጉ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡<br>ለተማሪዎች የቃለት መዋቅርና የፊደል ቅረጽ በመስጠት የተለመዱና ያልተለመዱ ተሻጋሪና ማይሻገሩ ቃላትን እንዲለዩ ማድረግ ፡፡ | ➢ የተማሪዎችን መሻሻል ለመገምገም በክፍል ውስጥ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም፡፡<br>➢ መምህራን በክፍል ውስጥ በመዘዋወር የትኞቹ ተማሪዎች እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸውና የትኞቹ እንደማያስፈልጋቸው ይለያሉ፡፡ |

**ምዕራፍ ዘጠኝ ፡-ባህላዊ ጨዋታዎች(18 ክፍለ ግዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ባህላዊ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ።
- የስርአተ ነጥብ አገባብንና ትርጉማቸውን ተረድተው ይጠቀማሉ።
- ባለብዙ ቀለም ቃላትን ያጣምራሉ።
- ደብዳቤ ይጽፋሉ።
- የአሁን ግዜን ግስን ይጠቀማሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው በባህላዊ ጨዋታዎች ውስጥ ይሳተፋሉ።<br>➢ ስለተለያዩ ጨዋታዎች አንብበው ዘገባ ያቀርባሉ።<br>➢ ደብዳቤ ይጽፋሉ።<br>➢ በዓረፍተ ነገር ምስረታ ውስጥ ያሁን ግዜን ግስን ይጠቀማሉ። | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | የተለመዱናያልተለመዱ አገላለጾችን እያወዳደሩ ቀደም ሲል በምሳሌነት የተማሩዋቸውን ቃላት በመጠቀም ቃላትን እንዲያዋቅሩ ማድረግ።<br>ቃላትን በምሳሌነት በቀረበላቸው አሰዳደር መሰረት እንዲዘረዝሩ ማድረግ።<br>ቅረጻቸውን መሰረት በማድረግ ተመሳሳይ ቅረጽ ያላቸውን ቃላት አንድ ላይ እንዲመድቡ ማድረግ።<br>ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ተጨማሪ ቃላት እንዲዘረዝሩ ማድረግ። | ➢ መምህራን በክፍል ውስጥ በመዘዋወር የትኞቹ ተማሪዎች እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸውና የትኞቹ እንደማያስፈልጋቸው መለየት።<br>➢ ተማሪዎች ስራቸውን ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ በማድረግ ትምህርቱን ምን ያህል እንደተረዱ መከታተል።<br>➢ ተማሪዎች ከሰሙት፣ካነበቡትና ከልምዳቸው የተገነዘቡትን በማጠቃለያ መልክ እንዲያንጸባርቁ ማድረግ። |

**ምዕራፍ አስር ፡- ስነቃል (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምእራፍትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ➢ የስነቃልን ምንነት ይገልጻሉ፡፡
- ➢ ልምምድ በማድረግ አንድን ነገር ይገልጻሉ፡፡
- ➢ አፈታሪክ በማንበብ ታሪኩን ይገልጻሉ፡፡
- ➢ የራሳቸውን ህይወት ታሪክ ይጽፋሉ፡፡
- ➢ የስነጽሁፍ አላባውያንን ይገልጻሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ ካዳመጡትና ከራሳቸው ልምድ በመነሳት ታሪኮችን ይናገራሉ፡፡<br>➢ ታሪኮችን በማንበብ በቃል ይተርካሉ፡፡<br>➢ ቀለሞችን በማጣመርና በመነጠል ይገልጻሉ፡፡<br>➢ ቀጥተኛ የሆኑና ያልሆኑ ነገሮችን ይገልጻሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥ እና መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | ጥቂት ቡድኖች የተውኔት ጽሁፎችን በግላቸው ለታዳሚዎቻቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡<br>ጥቂት ቡድኖች ወይም በተናጠል የአንድን ጽሁፍ የተለያየ ክፍል እንዲለማመዱማድረግ፡፡ይህ ልምምድ ተማሪዎች አንድን ነገር የመግለጽና በትክክል የማንበብ ችሎታ እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል፡፡<br>አንድን ጽሁፍ ደጋግመው እንዲያነቡ በማድረግ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የተገለጹ ነገሮችን እንዲገልጹ ማድረግ፡፡ | ➢ **አቅርቦት**፡-በዚህ ወቅት ለተማሪዎች እድል በመስጠትና እያዳመጡ ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ በማድረግ ብቃታቸውን መመዘን፡፡<br>➢ **የብጤ አርማት፡-** ተማሪዎች በግል የተሰጣቸውን ተግባር እንዲያጠቃልሉ በማድረግ ስራቸውን እየተለዋወጡ እንዲተራረሙ እድል መስጠት በመጨረሻም መምህሩ ስራቸውን ተቀብሎ መገምገም፡፡ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | | ➢ **የግል** ስራ፡-ተማሪዎች አንድን ሀሳብ ለመቃወምና አስተያየት ለመስጠት የሚያስችሉ ምክንያታዊና ግልጽየሆኑ እውነታዎችን ከጽሁፉ ውስጥ እንዲለዩ ማድረግ፡፡ |

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

### የመምህር መምሪያ መጽሐፍ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ